ثواب لوالديها / مبارك عبدالعزيز الحساوي رحمه الله، ووالدتها / بدرية محمد الخشتي حفظها الله

وقف لله، لا يجوز بيعه

በነፃ የሚታደል የወቅፍ እትም

دار الامل الخيرية

# ይህ ነው እስልምና

## هذا هو الإسلام

### ሶስቱ የቀብር ጥያቄዎች ማብራሪያ

شرح أسئلة القبر الثلاثة

### የአራቱ መሰረታዊ ህጎች ማብራሪያ

شرح القواعد الأربع

### ከእስልምና የሚያስወጡ ነገሮች ማብራሪያና ማስጠንቀቅያ

تحذير أهل الإيمان بأشياء تخرج المسلم من الإسلام



በአማረኛ ቋንቋ የተተረጎመ

مترجم باللغة الأمهرية

شرح فضيلة الشيخ

هيثم بن محمد جميل سرحان

የክቡር ሸይኽ ሀይሰም ብን ሙሀመድ ጀሚል ሰርሀን ማብራሪያ

هيثم سرحان

الموقع الرسمي الشيخ

www.alsarhaan.com

ይህ ነው እስልምና

የክቡር ሸይኽ ሀይሰም ብን ሙሀመድ ጀሚል ሰርሀን ማብራሪያ

دار الامل

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩኅ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው**

ምስጋና ባጠቃላይ ለአላህ ይገባው፤ እናመሰግነዋለን፣ እገዛውን እንጠይቀዋለን፣ መሃርታውን እንለምነዋለን፣ ከነፍሳችን ክፋትና ከክፉ ስራዎቻችን በአላህ እንጠበቃለን፤ አላህ የመራውን የሚያጠም የለውም፤ ያጠመመውንም የሚመራ የለውም፤ ከአላህ ውጭ (በእውነት) የሚመለክ እንደሌለ ብቸኛና ተጋሪ የሌለው መሆኑንና ሙሐመድም ﷺ ባርያውና መልዕክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ። በመቀጠል፡

# የትንታኔው መግቢያ

## የዚህ ፅሁፍ ደራሲ

ሸይኹል ኢስላም፤ የተውሒድ ጥሪ የተሃድሶ መሪ(ሙጀዲድ)፤ ኢማም ሙሓመድ ቢን

ዓብዱል ወሃብ ቢን ሱለይማን አት-ተሚሚይ፤ በቅፅል ስማቸው አቡ-ል-ሑሰይን (ይባላሉ)።

በዑየይና መንደር በ1115 ዓ. ሒ. ተወልደው በ1206 ዓ. ሒ. ሞቱ።

## ለምንድን ነው ተውሒድ የምንማረው?

| | |
|---|---|
| ምክንያቱም አሏህ እኛን የፈጠረበት ምክንያት ስለሆነ | በሱው ቢሆን እንጅ አላህ ስራን ስለማይቀበል |
| ተውሒድ ያለው ካልሆነ በቀር ጀነት ስለማይገባ | ምንዳን ለማብዛት ምክንያት ስለሆነ |
| ኃጢአትን ለማሰረዝ ምክንያት ስለሆነ | ለመመራትና ለተረጋጋ ደህንነት ምክንያት ስለሆነ |
| ለውስጣዊ መረጋጋት ምክንያት ስለሆነ | የነብዩን ﷺ አማላጅነት ለማግኘት ምክንያት ስለሆነ |

## በመጀመርያውኑ ይህንን ትምህርት ለማስተማር የተመረጠበት ምክንያት

የደጋግ ቀደምቶቻችን እና ሌሎች የአህሉ ሱና ወልጀማዓህ ሙሁራኖቻችን በዚህ ታላቅ ፅሁፍ ትኩረት የሰጡበት ምክንያት ካለው ጥቅምና የጎላ ፋይዳው አኳያ ነው። ይህች አንድ እውቀት ፈላጊ የሆነ ሰው መስመሩ አድርጎ ሊጓዝ የሚችልባትና ሸሪዓዊ እውቀቱንም የሚገነባበት መርሆ ነች። እኛም በዚሁ አካሄዳቸው አርአያ አድርገን እንይዛቸዋለን ኮቴያቸውንም እንከተላቸዋለን።

## ይህ ኪታብ *(በጥቅሉ የሸይኹ ኪታቦች)* ከተከታዮቹ ምክንያቶች አንፃር ይለያል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ግልፅና ቀላልነቱ | (ከፅሁፉ የምንረዳቸውን) ቁምነገሮችን ከማስረጃቸው ጋር በመጥቀስ | ቁምነገሮችን በቅደም ተከተላቸውና ቁጥር ካስቀመጠላቸው በኃላ ትንታኔ በመስጠቱ | ፅሁፎቹን ለሚያነብም ሆነ ለሚያዳምጥ ሰው ዱዓ በማብዛቱ |

## የሶስቱ መሰረቶች ፍች

ሶስቱ መሰረቶች አጠር ባለ መልኩ ሶስቱ የቀብር ጥያቄዎች ማለት ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ጌታህ ማን ነው? | ሃይማኖትህ ምንድን ነው ? | ነብይህ ማን ነው? |

## ሶስቱን መሰረቶች በመማራችን የምናገኘው ፍሬ ምንድን ነው?

አንተኮ ሶስቱን መሰረቶች ከተማርክ፣ ከዚያም በስራ ላይ ካዋልካቸው፣ ከዚያም ወደነሱው ጥሪ ካደረግክ፤ ከዚያም በእወቀቱ፣ በስራው ላይና ጥሪ በማድረጉ ላይ ትእግስትን ከተላበስክ ለቀብር ጥያቄዎች -በአላህ ፍቃድ- ምላሽ ትሰጣለህ።

## የሶስቱ መሰረቶች ፅሁፍ (ጥቅል) ማውጫ
## ይህ ፅሁፍ ወደ አምስት ክፍሎች ይከፈላል። እነሱም

1.አራቱ ቁምነገሮች (ሱረቱ-ል ዓስር)

2 .ሶስቱ ቁምነገሮች (የተውሒድ ክፍሎች)

3. ተውሒድን የማስተማር አሳሳቢነት

4. ሶስቱ መሰረቶች (የቀብር ጥያቄዎች)

5. መደምደሚያ

## 1.አራቱ ቁምነገሮች

- እውቀት
- በሱው መስራት
- ወደሱው ጥሪ ማድረግ
- በዛው ላይ ለሚያጋጥም ጫና መታገስ

## 2.ሶስቱ ቁምነገሮች

- 1.[አላህ] በጌትነቱና በስምና ባህርያቱ ያለው አሃዳዊነት
- 2. በአምላክነቱ ያለው አሃዳዊነት
- 3. ከሽርክ እና ከሽርክ ሰዎች (በልቦና፣ በአንደበትና በአካል) መጥራራት

## 3.ተውሒድን የመማር አሳሳቢነት

ተውሒድን ለምን እንማራለን? በሚለው ጥያቄ ላይ ምላሽ የተሰጠበት።

## 4. ሶስቱ መሰረቶች

ሶስቱ መሰረቶች አጠር ባለ መልኩ ሶስቱ የቀብር ጥያቄዎች ናቸው።

- ጌታህ ማን ነው?
- ሃይማኖትህ ምንድን
- ነብይህ ማን ነው?

## 5. ማጠቃለያ

የሸይኹ “ሰዎች ከሞቱ በኃላ ይቀሰቀሳሉ” ከሚለው እስከመጨረሻው።

# በመጀመሪያ: አራቱ ቁምነገሮች

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩኅ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው (1)
**እወቅ**–አላህ ይዘንልህና- (2) እነሆ አራት ቁመነገሮችን መማር ግዴታ ነው:
**በመጀመርያ እውቀት**: ያም አላህን ማወቅ፣ ነብዩን ﷺ ማወቅና ዲነል ኢስላምን በማስረጃ ማወቅ ነው።

ሁለተኛ: በሱው መስራት (3)".

**(1) ሸይኹ ፅሁፋን በቢስሚላህ የጀመሩበት ምክንያት**

- በአላህ መፅሃፍና በነብያቶች (ዓለይሂሙ ሰላም) ከመመራት አንፃር
- ከሱ በፊት ፅሁፎቻቸውን በቢስሚላህ መጀመር ልምዳቸው በነበሩ ቀደምትና ዑለሞች ከመከተል አንፃር
- በተከበረው የአላህ ስም በረካን ከመሻት አንፃር

(2) ቀደም ብለን እንደጠቆምነው ከአዘጋጁ ልምድ አንፃር ለእውቀት ፈላጊዎች ዱዓእ ማድረጉን መጀመሩ ነው። ይህ ደሞ የሚከተሉትን ጥቆማዎች ይሰጣል:

- የአህለ ሱና ወልጀማዓህ ዑለሞች በተማሪዎቻቸው ላይ ያላቸው እዝነት
- ዲነል ኢስላም በመሰረቱ በእዝነት ላይ የተገነባ ስለመሆኑ

**እውቀት:** ሲባል እውነትን በማስረጃው ማወቅ ማለት ነው፤ ተቃራኒው አላዋቂነት ነው።

**(3)** በእውቀትና በተግባሩ መካከል ስላለው ቁርኝት የሚከተለው ተብሏል: “እውቀት ተግባርን ጥሪ ያደርግለታል፤ ምላሽ ከሰጠው ይቀጥላል፤ አለበለዚያ ግን ይተወዋል።” ተግባር ያልተቆራኘው እውቀት ፋይዳቢስ ነው። ካወቀ ሊሰራ ግድ ይለዋል አለበለዚያ ግን የአይሁዶች ተመሳሳይነት አለበት። ምክንያቱም አይሁዶች እወቀቱም ቢኖራቸው ተግባሩ የላቸውምና {ወንዶች ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ (ሙሐመድን) ያውቁታል።} (አል በቀራህ 146)

አስቀድሞ እሳት የምትቀጣጠልባቸው ሶስት ናቸው። ከነሱም ተምሮ እውቀት ያካበተ ዓሊም ሆኖ በሱም ያልሰራበት:

*እውቀት ኖሮት በእውቀቱ ያልሰራበት ከጣኦት አምላኪ በፊት ቅጣቱ አለበት*

[ወደ አላህ ለሚደረግ] ጥሪ የሚቆምበት ግዴታ የሆኑ መሰረቶችና ቅድመ መስፈርቶች አሉት፤ አሳሳቢ ከሚባሉትም:

- ጥሪው ጥርት ባለ መልኩ የአላህን ፊት ብቻ ተፈልጎበት ሊሆን ይገባዋል
- ጥሪው ሸሪዓዊ እውቀት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባዋል
- ጥሪው በጥበብ እና በትእግስ ት ሊሆን ይገባዋል
- ጥሪ የሚደረግላ ቸውን ሰዎች ሁኔታ አሟልቶ የጠበቀ ሊሆን ይገባዋል

**ሶስተኛ:**
ወደሱው ጥሪ ማድረግ

**ለነዚህ ቅድመ መስፈርቶች ማስረጃው...**

ከፍ ያለው አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል: **{«ይህች መንገዴ ናት። ወደ አላህ እጠራለሁ። እኔም የተከተለኝም ሰው በግልጽ ማስረጃ ላይ ነን። ጥራትም ለአላህ ይገባው። እኔም ከአጋሪዎቹ አይደለሁም» በል።} (ዩሱፍ-108)**

**«ይህች መንገዴ ናት... »** ጥቆማው ነብዩ ﷺ ይዘውት የመጡትን ሸሪዓ የሚያመለክት ነው። "السبيل" ሲባል መንገዱን ነው።

**«... ወደ አላህ እጠራለሁ... »** ወደ አላህ ጥሪ የሚያደርግ ሰው ሲባል ጥርት ባለ መልኩ የአላህን ፊት ፈልጎ ሰዎችን ወደ አላህ ለማድረስ የሚጣራው ነው።

**«... በግልጽ ማስረጃ ላይ... »** "በሲራ" ሲባል እውቀት ማለት ነው። እዚጋ የሚከተሉትን ማወቅን ያካትታል:

ወደተፈለገበት የሚያደርሰውን አካሄድ

የተጠረውን ሁኔታ

ሸሪዓውን

ሸይኹ እንዲህ ለማለት የፈለጉ ይመስላል፤ አውቀህ የምትሰራ ከሆንክ ነብዩ ﷺ ፣ ሶሓቦችና ቀደምት ደጋግ አበው በነበሩበት ልትጓዝ ይገባሃል፤ አላህ ያለው **{«ይህች መንገዴ ናት። ወደ አላህ እጠራለሁ። እኔም የተከተለኝም ሰው በግልጽ ማስረጃ ላይ ነን።}** ነውና። ስለዚህም ጥሪ (ዳዕዋ) ማድረግ የግድ ነው።

**አራተኛ:** በዛው ላይ ለሚያጋጥም ጫና መታገስ: (1) ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **« {በጊዜያቱ እምላለሁ። (1) ሰው ሁሉ በእርግጥ በከሳራ ውስጥ ነው። (2) እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን የሠሩት፣ በእውነትም አደራ የተባባሉት፣ በመታገስም አደራ የተባባሉት ብቻ ሲቀሩ። (3) » } » (አል ዓስር:1-3)** (2)

**(1)** ሸይኹ አላህ ይዘንለትና «ልክ ለነብያቶችና ለሩሱሎች እንደተከሰተባቸው ሁሉ ይህንን መንገድ ለሚከተልም አንዳንድ ጉዳዮች ይከሰቱበታልና ትእግስት የግድ ነው።» ለማለት የፈለገ ይመስል ከዳዕዋ (ወደ አላህ ጥሪ ማድረግ) በኃላ ትእግስትን ጠቀሰ።

**ትዕግስት**

በቋንቋ ደረጃ: ማቀብ

በሸሪዓ ደረጃ: ነፍስን በታመነባቸው ነገራቶች ላይ እና ከአላስፈላጊ ነገራቶች ያዝ ማድረግ

**ኢብኑል ቀይም አላህ ይዘንለትና ሶብርን (ትእግስትን) ወደ ሶስት ይከፍለዋል**

1. የአላህ ትእዛዝ ተፈፃሚ እስኪሆን ድረስ በትእዛዙ ላይ መታገስ
2. ክልክላቶችን እስከቀመታቀብ ድረስ አላህን ከማመፅ መታገስ
3. አሳማሚ በሆኑ የአላህ ውሳኔዎች ላይ መታገስ

**(2)** ሸይኹ አራቱን ቁምነገሮች ከጠቀሰ በኃላ ማስረጃቸውን ከቁርአን ጠቀሰ፤ ያም ሱረቱል ዓስር ነው። ሸይኹ አላህ ይዘንለትና ቁመነገርን ባወሳ ቁጥር ማስረጃውንም አቆራኝቶ ያመጣል። **ለምን?**

| | | |
|---|---|---|
| እውቀት ፈላጊን ከተጎታችነት ይልቅ (በማስረጃ) ተከታይነት ላይ ከመኮትኮት አንፃር | ተማሪው በተቃራኒዎቹ ላይ የሚመልስበት ማስረጃ ይኖረው ዘንድ | ተማሪው ሕግጋቶችን ከመሰረታዊ ማስረጃቸው ከማውጣጣት (ኢስቲንባጥ ከማድረግ) አንፃር ችሎታ ይኖረው ዘንድ |

**(1)** አላህ ይዘንለትና ሃሳቡ ይህች ሱራ ብቻዋን ለፍጡራን ያውቁ፣ ይተገብሩ፣ ጥሪ ሊያደርጉና ሊታገሱ ዘንድ በቂ የሆነች ማሰረጃ ነች ነው።

እንዴት ነው ታድያ ከዚህ ሁሉ ሱራ ጋ ሲሆንስ? ቁርአን በሙሉው (ዑዝር የማያሰጥ) ማስረጃ ነው።

**(2)** በሓዲሥ ዘርፍ የሙእሚኖች መሪ በሶሒሐል ቡኻሪይ ኪታቡ ላይ “ባብ: እውቀት ከንግግርም ከተግባርም ቀዳሚ ስለመሆኑ” ብሎ ርእስ ቋጠረለትና ማስረጃውንም ጠቀሰ። ስለዚህ ከንግግርም ከተግባርም በፊት እውቀት ቀዳሚ መሆኑ የማያወላዳ ነው።

ያለእውቀት መስራት ትክክል ሊሆን አይችልም፤ አለበለዚያ ከክርስትያኖች ጋር የሚመሳሰልበት ሆነ ማለት ነው።

ኢማሙ ሻፊዕይ -አላህ ይዘንላቸውና- እንዲህ ይላሉ: “አላህ በፍጡራኖቹ ላይ ከዚች ሱራ ውጭ ማስረጃን ባያወርድ ኖሮ (ለተልዕኮው) በቂያቸው በሆነች ነበር።” (1)

**ኢማሙል ቡኻሪይም** -አላህ ይዘንላቸውና- እንዲህ ይላሉ: “ባብ: እውቀት ከንግግርም ከተግባርም ቀዳሚ ስለመሆኑ” ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«እነሆ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩንም ዕወቅ። ስለ ስህተትህም ለምእመናንም ምሕረትን ለምን። »** (ሱረቱል ሙሓመድ 19) ከንግግርም ከተግባርም እውቀትን አስቀደመ። (2).

# ሁለተኛ: ሶስቱ ነጥቦች

አላህ ይዘንልህና እወቅ: እነሆ እነኝህን ሶስቱን ነጥቦች አወቆ በነሱው መስራት በሁሉም ወንድም ሆነ ሴት ሙስሊም ላይ ግዴታ ነው። (1)

(1) ሸይኹ አላህ ይዘንላትና ይህን የፅሁፉን ክፍል ለተማሪው ዱዓ በማድረግ ጀመረው። ሸይኹ አላህ ይዘንላትና በኡሱሉ ሠላሣህ ኪታቡ ለተማሪው ሶስት ጊዜ ዱዓእ ያደርግላታል፤ በመጀመሪያ በአራቱ ቁምነገሮች መንደርደሪያ፣ ከዚያም እዚሁ ሶስቱን ነጥቦች ሲጠቅስ፣ ሶስተኛው ደሞ በሚከተለው አረፍተ ነገር ውስጥ፤ "እወቅ: አላህን ለመታዘዝ ቅኑን ይምራህና፤ ቀና የሆነችዋ የኢብራሂም መንገድ እኮ..."

## ሶስቱን ነጥቦች ከማብራራታችን በፊት መንደርደሪያ

### ተውሒድ

**ከቋንቋ አንፃር:** ወሐደ፣ ዩወሒዱ፣ ተውሒደን ከሚል ስርወ ቃል የመጣ ሲሆን፤ "ወሐደ-ሸይእ" ሲባል ብቸኛ ማድረግን የሚጠቁም ቃል ነው።

**ከሸሪዓ አንፃር:** አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላን ብቸኛ በሆነባቸው በጌትነቱ፣ በአምልኮት እና በስምና ባህርያቱ መነጠል ማለት ነው።

### ተውሒድ ወደ ሶስት ይከፈላል

**ተውሒደ ሩቡቢያ (የጌትነት አሃዳዊነቱ):** አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላን በድርጊቶቹ ብቸኛ ማድረግ። ወይም አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላን በመፍጠሩ፣ በንግስናውና በማስተናበሩ ብቸኛ ማድረግ ማለት ነው።

**ተውሒደል ኡሉሂያ (በአምልኮ አሃዳዊነቱ):** አሏህ ሱብሓነሁ ወተዓላን በአምልኮ ብቸኛ ማድረግ።

**ተውሒዱል አስማኢ ወሲፋት (በስምና ባህርያቱ ያለው አሃዳዊነቱ):** አሏህ ሱብሓነሁ ወተዓላን ራሱን በኪታቡ ወይም በነብዩ ﷺ እንደበት በሰየመበትና በገለፀበት መልኩ ብቸኛ ማድረግ። ይህም ከተሕሪፍ (ማዛባት)፣ ከተዕጢል (ውድቅ ማድረግ) ፣ ከተክይፍ (ዝርዝር ሁኔታ ሳንሰጥ) እና ከማመሳሰል ውጭ በሆነ መልኩ ለራሱ ያፀደቀውን በማፅደቅ፣ ከራሱ ያወገዘውን በማውገዝ ነው።

*ስምና ባህርያቱን በማስመልከት በቁርአንና በሓዲሡ በመጣው የምንገደብበት ተውቂፍይ (እገዳ የተጣለበት) ነው። ይህም የሚሆነው:

አሏህ ሱብሓነሁ ወተዓላን ራሱን በኪታቡ ወይም ነብዩ ﷺ ለአላህ ያፀደቁትን በማፅደቅ እና...

አሏህ ሱብሓነሁ ወተዓላ በኪታቡ ከራሱ ያወገዘውን ወይም ነብዩ ﷺ ከአላህ ያወገዙትን በማውገዝ ነው። ለምሳሌ: « {... ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም።...} (አል-በቀራህ 255) {... ድካምም ምንም አልነካንም።...} (ቃፍ 38) »

ይህም ከተሕሪፍ (ማዛባት)፣ ከተዕጢል (ውድቅ ማድረግ) ፣ ከተክይፍ (ዝርዝር ሁኔታ መስጠት) እና ከማመሳሰል ውጭ በሆነ መልኩ ነው።

**የመጀመሪያው ነጥብ**: አላህ እኛን ፈጠረን፣ ሲሳይም ለገሰንና እንዲሁ በከንቱ አልተወንም፤ ይልቅ መልእክተኛ ላከልን፤ እሱን የታዘዘ ጀነት ገባ፤ እሱን ያመፀውም ጀሀነም ገባ። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: « **{እኛ በእናንተ ላይ መስካሪ መልዕክተኛን ወደእናንተ ላክን። ወደ ፈርዖን መልዕክተኛን እንደላክን። (15) ፈርዖንም መልክተኛውን አመጸ፤ ብርቱ መያዝንም ያዝነው። (16)}** » (**አል-ሙዘሚል 15-16**). (1)

## “የሶስቱ ነጥቦች” ማጠቃለያ

| አንደኛው ቁምነገር: ተውሒዱ ሩቡቢያ (የጌትነት አሃዳዊነቱ) እና ተውሒዱል አስማኢ ወሲፋት (የስምና ባህርይ አሃዳዊነቱ) | ሁለተኛው ቁምነገር: ተውሒዱል ኡሉሂያ (አምልኳዊ አሃዳዊነቱ) | ሶስተኛው ቁምነገር: ከሽርክ እና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት |
|---|---|---|

(1) ሸይኹ አላህ ይዘንለትና በመጀመርያዋ ቁምነገር የጌትነት አሃዳዊነቱንና የስምና ባህርይ አሃዳዊነቱን (በሚከተለው መልኩ) አፀናባት፤ “አላህ እኛን ፈጠረን፣...” ሲል አል-ኻሊቅ (ፈጣሪ መሆኑን) ፤ “ሲሳይም ለገሰን” ሲል አር-ረዛቅ (ሲሳይ ለጋሽ) ፤ “እንዲሁ በከንቱ አልተወንም...” ትእዛዝና ክልከላ የሌለባቸው ከንቱዎች (አላደረገንም)፤ “ይልቅ መልእክተኛ ላከልን” ።

## አላህ መልዕክተኞችን (ዓለይሂሙ ሰላም) የመላኩ አላማ

| በፍጡራኖች ላይ ሑጃ [ተልዕኳዊ ማስረጃ] ከማቆም አንፃር፤ «{መልዕክተኛንም እስከምንልክ ድረስ የምንቀጣ አይደለንም።}» (አል-ኢስራእ 15) | ከርህራሄ አንፃር: « (ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም።:) » (አል-አንቢያእ 107) |
|---|---|

**ሁለተኛው ነጥብ**: አላህ ከአምልኮ አንፃር ማንም እንዲጋራው አይፈልግም፤ ቅርብ መላኢካም ሆነ የተላከ ነብይም እንኳ ቢሆን (እንዲጋራው አይፈልግም)፤ ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **« {እነሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው። (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ። } »** (አል-ጅን 18)

በሁለተኛዋ ቁምነገር አምላክነትን ለአሏህ ማፅደቅን ይዛለች:

ሸይኹ አላህ ይዘንለትና "አላህ ከአምልኮ አንፃር ማንም እንዲጋራው አይፈልግም" ፤ ይህ አገላለፅ በዓረብኛው ያለው የቃላት አሰካክ በዓረብኛው የስዋሰዋዊ ህግ መሰረት እያንዳንዱን ከሱ ውጭ ያለውን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው። ነብይ፣ ወልይ፣ ጅንይ፣ መላኢካ፣ ደግ ሰው፣ ሌላ ሌላም የሆነ ይሁን (የሚያጠቃልል ነው) ።

ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **« {እነሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው። (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ (ማለትም)።} »** (አል-ጅን 18)

**"...الْمَسَاجِدَ..."ወይም "... መስጊዶችም... " የተባለውን በማስመልከት ሶስት የተለያየ ግን ማስማማት የሚቻል (የ ዑለሞች) ቃል አለ:**

| | | |
|---|---|---|
| አላህ እንዲመለክበት በሚል የተገነቡ መስጅዶች | የሱጁድ አካላቶች | መሬት ; "መሬት (በሙሉ) መስጅድና ንፁህ ተደረገችልኝ" (ቡኻሪይ) |

{... የአላህ ብቻ ናቸው። (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ (ማለትም)።}(አል-ጅን 18) "...አንድንም..." ወይም "...أَحَدًا" ሲል ይህም አገላለፅ በዓረብኛው ያለው የቃላት አሰካክ በዓረብኛው የስዋሰዋዊ ህግ መሰረት ከሱ ውጭ ያለውን በሙሉ እያንዳንዱን የሚያካትት ነው። ለዚህም ነው ኢማሙ አላህ ይዘንላቸውና በሁለተኛዋ ቁምነገር መንደርደርያ "አላህ ከአምልኮ አንፃር ማንም እንዲጋራው አይፈልግም" ያለው። ማለትም ማንም ይሁን: ነብይም፣ ወልይም፣ ጅንይም ይሁን ሷሊሕ።

ሶስተኛዋ ቁምነገር ላይ አላህ ይዘንለትና ሸይኹ ከሽርክም ሆነ ከሽርክ ሰዎች መጥራራት ግዴታነቱን ግልፅ አደረገ።

**ከሽርክ እና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት የሚሆነው:**

- በልቦና
- በአንደበት
- በተግባር

1. **በልቦና**: ካፊሮችን፣ በዓላቸውንም ሆነ ሌሎች ዝግጅቶቻቸውን በተለይም እነሱ ዘንድ የሚገኙ ሽርክና ቢድዓዎቻቸውን ልትጠላ ነው።

2. **በአንደበት**: **{«እኔ ከምትግገዙት ሁሉ ንጹሕ ነኝ፡፡»} (ዙኽሩፍ 26)**

**{በላቸው «እናንተ ከሓዲዎች ሆይ! (1)«ያንን የምትግገዙትን (ጣዖት አሁን) አልግገዛም፡፡(2) «እናንተም እኔ የምግገዛውን (አምላክም አሁን) ተገዢዎች አይደላችሁም፡፡(3) «እኔም ያንን የተገዛችሁትን (ወደፊት) ተገዢ አይደለሁም፡፡(4) «እናንተም እኔ የምግገዛውን (ወደፊት) ተገዢዎች አይደላችሁም፡፡(5) «ለእናንተ ሃይማኖታችሁ አልላችሁ፡፡ ለእኔም ሃይማኖቴ አለኝ፡፡(6)}» (አል-ካፊሩን 1-6)**

3. **በተግባር**: የእምነት መገለጫቸው በሆኑ ክብረ በአላቶቻቸውም ይሁን ሀይማኖታዊ ስነስርአቶቻቸው ወይም በአለባበሳቸው ባለመጋራት የሚሆን ነው።

**ሶስተኛው ነጥብ**: መልእክተኛውን ﷺ የታዘዘና የአላህን አሃዳዊነት ያፀደቀ ሰው አላህንና መልእክተኛውን ﷺ የሚከራከሩትን ሰዎች የቅርብ ቅርብ እንኳ ቢሆኑ ሊወዳጅ አይፈቀድለትም። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው:

**«በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምኑትን ሕዝቦች አላህንና መልክተኛውን የሚከራከሩትን ሰዎች፤ አባቶቻቸው፣ ወይም ልጆቻቸው፣ ወይም ወንድሞቻቸው፣ ወይም ዘመዶቻቸው ቢኾኑም እንኳ የሚወዳጁ ኾነው አታገኛቸውም፡፡ እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ እምነትን ጽፏል፡፡ ከእርሱም በኾነ መንፈስ ደግፏቸዋል፡፡ ከሥሮቻቸውም ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲኾኑ ያገባቸዋል፡፡ አላህ ከእነርሱ ወዷል፡፡ ከእርሱም ወደዋል፡፡ እነዚያ የአላህ ሕዝቦች ናቸው፡፡ ንቁ! የአላህ ሕዝቦቸ እነርሱ ምኞታቸውን የሚያገኙ ናቸው።»** (አል-ሙጃደላህ 22)

# ሶስተኛ: ተውሒድን የመማር አሳሳቢነት

አላህ ለታዛዥነቱ ቀናውን ይምራህና እወቅ ሐኒፍ የሆነችዋ የኢብራሂም መንገድ እኮ:

አምልኮህን ጥርት አድርገህ አላህን ልትገዛው ነው፤ አሏህ የሰው ልጆችን በሙሉ ያዘዘበትና የፈጠረበት አላማም ለዚሁ ነው። ልክ አላህ በሚከተለው መልኩ እንዳለው: **«{ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም። }»** **(ዛርያት 56) (1)** "لِيَعْبُدُونِ" ወይም **"ሊግገዙኝ"** ሲል (በአምልኮ) ብቸኛ ሊያደርጉኝ ማለት ነው። (2)

አላህ ያዘዘበት ትልቁ ጉዳይ ተውሒድ ሲሆን ያም አላህን በአምልኮ ብቸኝነቱን ማረጋገጥ ነው። **(3)** አላህ የከለከለው ትልቁ ጉዳይ ደግሞ ሽርክ ነው፤ ያም አንዳች ነገር ከአላህ ጋ መጣራት ማለት ነው።

## ሐኒፊያ

**ከቋንቋ አንፃር:** "الحنف" ወይም "አል-ሐነፍ" ከሚለው የመጣ ሲሆን ትርጉሙም መዘንበል ማለት ነው።

**ከሸሪዓ አንፃር:** ከሸሪዓ አንፃር ደግሞ ሽሪካ ከማድረግ ይልቅ ወደ ኢኽላስ፣ ተውሒድና ኢማን ያዘነበለች መንገድ ናት። **«...ለአላህ ታዛዥ ወደ ቀጥተኛ ሃይማኖት ተዘንባይ...»** (ነሕል 120) ማለትም ወደ አላህ ተቅጣጮቶ ለሽርክ ጀርባውን የሰጠ ማለት ነው። "الحنيف" ሁልጊዜም ወደ ተውሒድ እየተመለሰ ከሽርክ የሚርቅ ነው።

**(3)** እዚጋ ሸይኹ አላህ ይዘንላትና ተውሒድን ለምን እንደምንማር ያብራራልናል፤ አሳሳቢነቱንም ቀደም ብለን ጠቅሰናል።

## ቀደም ብለን በመግቢያው ላይ እንደጠቀስነው የተውሒድ ፍች

**ከቋንቋ አንፃር**: ወሐደ፣ ዩወሒዱ፣ ተውሒደን ከሚል ስርወ ቃል የመጣ ሲሆን፤ "ወሐደ-ሸይአ" ሲባል ብቸኛ ማድረግን የሚጠቀም ቃል ነው።

**ከሸሪዓ አንፃር**: ከሸሪዓ አንፃር: አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላን ብቸኛ በሆነባቸው በጌትነቱ፣ በአምልኮት እና በስምና ባህርያቱ መነጠል ማለት ነው።

ሸይኹ አላህ ይዘንለትና « لِيَعْبُدُونِ ወይም "ሊግገዙኝ"» ሲል (በአምልኮ) ብቸኛ ሊያደርጉኝ ማለት ነው።" ይላል፤ ይህ ደሞ ኢብኑ ዓባስ ረድየሏሁ ዓንሁማ እንደሚከተለው ያሉት ንግግር ነው። "አምልኮ ሁሉ በቁርአን ትርጉሙ ተውሒድ ነው።" "اعبدوا الله"(النساء ٣٦) "... አላህን አምልኩ..."(አን-ኒሳእ 36) ማለትም "... ብቸኛ አድርጉት..." "እናንተ ሰዎች ሆይ!... ጌታችሁን ተገዙ" (አል-በቀራ 21) "... እናንተ ሰዎች ሆይ! ...በብቸኝነት ተገዙ" ማለት ነው።

## አራተኛ: ሶስቱ መሰረታዊ መርሆዎች

**(1)** ሸይኹ አላህ ይዘንለትና ሶስት የቀብር ጥያቄ ይዘት ያላቸውን ሶስቱን መሰረታዊ መርሆዎች በመግለፅ ጀመረ፤ (አስቀድሞ) የአድማጭን ወይም የአንባቢን ትኩረት በጥያቄ ካነቃቃ በኃላ ምላሹን ሰጠ።

**(2)** ሸይኹ አላህ ይዘንለትና አምልኮ የሚገባው ጌታ አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ መሆኑን በመግለፅ የመጀመርያውን መሰረት አብራራ፤ ማስረጃውንም ተከታዩን የቁርአን አንቀፅ ጠቀሰ: «ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለኾነው፤» (አል-ፋቲሓ 1) የሚመለከው ደሞ ጌታ ነው።

"የሰው ልጅ ሊያውቃቸው ግድ የሚሉ ሶስቱ መሰረታዊ መርሆዎች ምንና ምን ናቸው?" ከተባልክ እንዲህ በል፡
"አንድ ባርያ ጌታውን፣ ዲኑንና ነብዩ ሙሓመድን ﷺ ማወቁ ነው።" **(1)**
«ጌታህ ማን ነው? » ከተባልክ "ጌታየ ያ በፀጋው እኔንም የተንከባከበኝ መላው አለምንም የሚንከባከበው አሏህ ነው፤ እሱኑ ነው የማመልከው ሌላ የማመልከው የለኝም።" በል። ማስረጃውም ከፍ ያለው አላህ በሚከተለው መልኩ ያለው ነው: «ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለኾነው፤» (አል-ፋቲሓ 1) **(2)**
ከአላህ ውጭ ያለው ሁሉ (በአንቀፁ ላይ በተገለፀው) ዓለም (ውስጥ የሚካተት) ነው። እኔም የዚህ አለም አንዱ ነኝ። **(3)**.

«ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለኾነው፤» (አል-ፋቲሓ 1)

ይህች አንቀፅ ሶስቱንም የተውሒድ አይነቶችን አካታለች

«"الحمد""ምስጋና" ...» ተውሒዱል አስማእ ወሲፋትን(በስምና ባህርያቱ ያለውን አሃዳዊነት) ይዟል

« "لله" "ለአላህ ይገባው"...» ተውሒዱል ኡሉሂያ (በአምልኮ አሃዳዊነቱ)ን ይዟል

«"رب" "የዓለማት ጌታ ለሆነው"...» ተውሒዱ ሩቡቢያ (የጌትነት አሃዳዊነቱን) ይዟል

**(3)** ማለትም ከአላህ ውጭ ያለው ሁሉ ፍጡር ነው፤ ፍጡር እስከሆንኩ ድረስ ደሞ ጥራት ይገባውና በጎ የዋለልኝን ፈጣሪ ምስጋና ላቀርብለት የግድ ነው።

"ጌታህን በምን አወቅክ?" ብትባል "በምልክቶቹና በፍጥረታቱ" በል። ከምልክቶቹም ሌሊትና ቀን፤ ፀሀይና ጨረቃ፤ ከፍጥረታቱ ደሞ ሰባቱ ሰማያት፣ ሰባቱ ምድሮች በውስጣቸውም ያለው በመካከላቸውም ያለው ይገኝበታል።
ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው።: «ሌሊትና ቀንም ፀሐይና ጨረቃም ከምልክቶቹ ናቸው፡፡ ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ፡፡ ለእዚያም ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ፡፡ እርሱን ብቻ የምትግገዙ እንደ ኾናችሁ (ለሌላ አትስገዱ)።» (ፉሲለት 37) እንዲሁም ተከታዩ ቃሉ: «ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው፡፡ ከዚያም በዐርሹ ላይ ተደላደለ፡፡ (አላህ) ሌሊትን በቀን ፈጥኖ የሚፈልገው ሲኾን ይሸፍናል፡፡ ፀሐይንና ጨረቃንም ከዋክብትንም በትእዛዙ የተገሩ ሲኾኑ (ፈጠራቸው)፡፡ ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ብቻ ነው፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ፡፡» (አል አዕራፍ 54) **(1)**.
የሚመለከው ጌታ ነው፤ ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡(21) (እርሱ) ያ ለናንተ ምድርን ምንጣፍ ሰማይንም ጣራ ያደረገ ነው፤ ከሰማይም (ከደመና) ውሃን ያወረደ በርሱም ከፍሬዎች ለናንተ ሲሳይን ያወጣ ነው፡፡ እናንተም (ፈጣሪነቱን) የምታውቁ ስትኾኑ ለአላህ ባላንጣዎችን አታድርጉ፡፡» (አል በቀራህ 22) **(2)**.
ኢብኑ ከሢር አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ይላሉ "እነኝህን የፈጠረ ለአምልኮ ተገቢ የሆነው እሱው ነው።" **(3)**.

**(1)** ሸይኹ አላህ ይዘንለትና ወደ አምላክ ህልውና ጠቋሚ የሆኑ አለማዊ ምልክቶችንና ፍጥረታትን ማውሳት ጀመረ፤ ከአላህ ውጭ ጌታ፣ ፈጣሪም ተመላኪም እንደሌለ የሚያፀኑ ምልክቶችን። ቀደም ብለን በመግቢያው ላይ እንዳወሳነው ለነዚህም ከቁርአን ማስረጃዎችን አጣቀሰ።
እያንዳንዱ ፍጥረት ጥራት ይገባውና ከፍ ወዳለው አምላክ ህልውና ጠቋሚ የሆነ ምልክት ነው። ነገር ግን ሸይኹል ኢስላም ሙሐመድ ቢን ዓብዱል ወሃብ አላህ ይዘንለትና በፍጥረታትና በ(ተአምራዊ) ምልክቶች መካከል ልዩነትን በሚጠቁም መልኩ ገለፃቸው፤ ምክንያቱም ልክ እንደ ቀንና ሌሊት መፈራረቅ አይነት "አል-አያህ (ተአምራዊ ምልክቶች)" ይለዋወጣሉና ነው፤ የሚለዋወጥ ደሞ ከማይለዋወጠው በላይ የበረታ ጥቆማ ሰጭ ነው።
**(2)** ይህች አንቀፅ ሱረቱል በቀራህ ላይ የምትገኝ አንቀፅ ነች፤ ስለዝች አንቀፅ አንዳንድ ዑለሞች በቁርአን የመጀመርያው ጥሪ «እናንተ የሰው ልጆች ሆይ! …» የሚለው እንዲሁም የመጀመርያው ድርጊታዊ ትእዛዝ «…ተገዙ…» ማለትም "ብቸኛ አድርጉ" የሚለው በአንቀጿ ላይ እንዳለ ያፀናሉ። «(…እናንተም (ፈጣሪነቱን) የምታውቁ ስትኾኑ ለአላህ ባላንጣዎችን አታድርጉ፡፡» በሚል ከሽርክ የሚከለክለው የመጀመሪያው ክልከላም በአንቀፁ ላይ እንዳለ ሁሉ።

**(3)** በጌትነቱ አሃዳዊነት የፀደቀለት በአመልኮም አሃዳዊነቱ ሊፀድቅለት ይገባል።

ሸይኹ ከኢብኑ ከሢር ቃል በኃላ ልቦናዊና አካላዊ የሆኑ የአምልኮ አይነቶችን ለእያንዳንዱ ተግባር በሚከተለው መልኩ ከማስረጃዎቻቸው ጋ በማውሳት አስከተለ፤

**ዱዓእ**

**ለሁለት ይከፈላል**

የአምልኮ ዱዓእ: ይህ ሲባል ዱዓነቱ በተዘዋዋሪ የሆነ ማለት ነው፤ እንደሶላት፣ እንደፆምና እንደሓጅ አይነቱ ማለት ነው።

የመለመን ዱዓእ: ይህ ደሞ በቀጥታ ዱዓእ የምንለው ነው፤ “መሀርታህን ለግሰኝ” “እዝነትህን ለግሰኝ” እንደምንለው አይነት ማለት ነው።

ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ መስጠቱ ትልቁ ሽርክ ውስጥ ይመደባል።

የሚሰጥበት ፍርድ ዝርዝር የሚያስፈልገውና ወደኃላ እንደምንጠቅሰው ሁለት አይነትም ነው።

አላህ ያዘዘባቸው የሆኑ የአምልኮ አይነቶች (1) እንደ ኢስላም፣ ኢማን(እምነት)፣ ኢሕሳን፣ እንዲሁም ዱዓእ፣ ፍርሃት(ኸውፍ)፣ ተስፈኝነት፣ መመካት፣ መከጀል(አር-ረግባህ)፣ መሸሽ የታከለበት ስጋት (አር-ረህባህ)፣ መተናነስን ያዘለ ፍርሃት(አል-ኹሹዕ)፣ እውቀት ላይ የተመረኮዘ ፍርሃት(አል-ኸሽየህ)፣ ተፀፅቶ መመለስ፣ እገዛን መሻት፣ ጥበቃን መሻት፣ ከጭንቅ ገላጋይን መሻት፣ እርድ ማቅረብ፣ ስለትና ሌሎችም አላህ ያዘዘባቸው የሆኑ የአምልኮ አይነቶች ሁሉ ለአለማት ጌታ ለአላህ የሚገቡ ናቸው። ማስረጃውም፡ **«እነሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው፡፡ (በውስጣቸው) ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ (ማለትም)፡፡»** (አል-ጅን 18).

ከነዚህም አንዲትስ`ኳ ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ የሰጠ ሙሽሪክና ካፊር ነው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **« {ከአላህም ጋር ሌላን አምላክ ለእርሱ በእርሱ ማስረጃ የሌለውን የሚገዛ ሰው ምርመራው እጌታው ዘንድ ብቻ ነው፡፡ እነሆ ከሓዲዎች አይድኑም፡፡} »** (አል-ሙእሚኑን 117) በሓዲሥም “ዱዓእ የአምልኮ አስኳል ነው። ” የሚል ይገኝበታል።ከፍ ያለው አላህም እንዲህ ይላል: **«{ጌታችሁም አለ «ለምኑኝ፤ እቀበላችኋለሁና፡፡ እነዚያ እኔን ከመግገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ኾነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ፡፡}»** (**ቓፊር 60**)




ይህ ተጠሪ በፍጥረተ አለሙ ላይ ድብቅ እንቅስቃሴ እንዳለው፣ ጥቅምን ሊያመጣ ወይም ከፋትን ሊያስቀር የሚችል ተደርጎ የሚታመን ከሆነ ግን ይህ ሽርክ ይሆናል።

**ል. በ:** እየተማርን ያለነው ፍርድ ስለድርጊቱ ነው እንጅ በድርጊቱ ፈፃሚ ላይ ስላለው ፍርድ ግን ሑጃ (ማስረጃ) ሊቆምለትና (ፍርዱን ከመስጠት) የሚያቅብ ነገር ሊወገድ ይገባዋል።

ድርጊት ፈፃሚው ላይ አማኝ ነው ካፊር የሚለውን ፍርድ መስጠት የሚችሉት ዑለሞች ናቸው።

## ሰበቦችን በማስመልከት ሰዎች ያላቸው እምነት ወደ ሶስት ይከፈላል

ጥራት ይገባውና አላህ ሰበብ ያደረገውን ነገር እንደሰበብነቱ የሚያምኑም እንደሰበብም አድርገው የሚይዙት፤ ይህ **ትክክለኛው** ነው።

ጥራት ይገባውና አላህ ሰበብ ያላደረገውን ነገር እንደሰበብ የሚያምኑና እንደሰበብም አድርገው የሚይዙት፤ ይህ **ትንሹ ሽርክ** ነው።

ሰበብን በራሱ ተፅዕኖ መፍጠር የሚችልና ጥቅም መምጣቱም ክፋት መወገዱም በሱው እንደሆነ አድርገው የሚያምኑ፤ ይህ **ትልቁ ሽርክ** ነው።

### ሸሪዓዊ ሰበቦች

ሸሪዓውን የጠበቀ ሩቃን ይመስል፤ አሏህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ህመምን ለማስወገድ ሩቃን ሸሪዓዊ ሰበብ አድርጎታል።

### ግኡዝ ሰበቦች:

መድኃኒቶች አሏህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ለፈውስ ሰበብ አድርጎታል።

“ዱዓእ የአምልኮ አስኳል ነው።” የሚለው ሓዲሥ ዶዒፍ ቢሆንም “ዱዓእ ራሱ አምልኮ ነው።” የሚል ሌላ የነብዩ ﷺ ሶሒሕ ሓዲሥ አለ።

## ዱዓእ ራሱ አምልኮ እንዴት ሊሆን ይችላል?

**«{ጌታችሁም አለ «ለምኑኝ፤ እቀበላችኋለሁና፡፡ እነዚያ እኔን ከመግገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ኾነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ፡፡}»** **(ቓፊር 60)** የሚለው አንቀፅም ለዚህ ጥቆማ ይሰጣል። ጥራት ይገባውና **«…መግገዛት…»** ብሎ ነው የጠራው፤ ይህ ደሞ የዱዓእን ዒባዳነት ጠቋሚ ነው።

ለኸውፍ (ፍርሃት/ዒባዳ መሆን) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «...አትፍሩዋቸውም:: ምእምናንም እንደኾናችሁ ፍሩኝ። » (አሊ ዒምራን 175) **(1)**.

ለተስፈኝነት (ዒባዳ መሆን) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «...የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ሥራን ይሥራ:: በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ» በላቸው::» (አልከህፍ 110) **(2)**.

**(1) ፍርሃት (ኸውፍ):** ሊያጠፉ ወይም ሊጎዳ የሚችል ነገር ይከሰታል በሚል ስጋት የሚመጣ ስሜት ነው።

ጥራት ይገባውና አሏህ የሸይጧን ጓዶችን መፍራት ከልክሎ እሱን ብቻ እንድንፈራው አዟል።

**ፍርሃት (ኸውፍ) ወደ ሶስት ይከፈላል**

| አምልኳዊ የሆነ፣ ማላቅ የታከለበት ውስጣዊ ፍርሃት: | ተፈጥሯዊ የሆነ ፍርሃት: | የተከለከለው ፍርሃት: |
|---|---|---|
| አንድ ባርያ አምላኩን በሚፈራበት መልኩ ሲሆን ራስን ማዋረድ፣ መተናነስና አምላክን ማላቅን የሚያካትት ነው። ይህ ዓይነቱ ፍርሃት ለአላህ የሚገባ ሲሆን ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ መስጠቱ ትልቅ ሽርክ ነው። | አንድ ሰው እሳትን፣ ጠላትን፣ አውሬ የሆነ እንስሳንና መሰል መፍራቱ ሲሆን የተፈቀደ ነው። | በአላህ ላይ ተስፋ መቁረጥና ፈጣሪን በማመፅ ላይ ፍጡርን መታዘዝ (የሚያደርስ አይነት) ፍርሃት። ይህ የተከለከለ ነው |

**(2) ረጃእ (ተስፈኝነት):** ለማግኘቱ ቅርብ የሆነን ወይም ሩቅም ቢሆን የቅርቡን ያክል ቦታ ለሚሰጠው ነገር ያለ ልባዊ ፍላጎት።

መተናነስና ራስን ማዋረድን የታከለበት ተስፋ ጥራት ይገባውና ለአላህ እንጅ አይገባም፤ ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ መስጠቱ ሽርኩን አከበር ላይ የሚመደብ ነው።

የሚወደስ የሆነ ተስፋ የሚጣልበትም ለአላህ ትእዛዝ ታዛዥ ሆኖ ምንዳውን ተስፋ ላደረገ አልያም ከወንጀሉ ተፀፅቶ ተመልሶ መፀፀቱን ተቀባይነት ማግኘቱን ተስፋ ላደረገ ነው። ስራ ያልታከለበት ተስፋ ግን ራስን መሸንገልና ከንቱ ምኞት ነው።

## (1) የ "ተውኩል ፍች"

**እንደቋንቋ:**

በአንዳች ነገር መደገፍ ማለት ነው።

**እንደሸሪዓ:**

ሸሪዓዊ የሆኑ ሰበቦችን በማድረስ እውነታኛ የሆነ በአላህ ተማምኖ መደገፍ ማለት ነው።

**ተወኩል ሲባል ሶስት ነገሮችን ሊያሟላ ይገባዋል**

| | | |
|---|---|---|
| **እውነተኛነት**: ጥራት ይገባውና በአላህ ላይ መደገፉ እውነተኛነት | ጥራት ይገባውና አላህ ቃሉን ፈፃሚ መሆኑን **መተማመን** | **ሸሪዓዊ የሆኑ ሰበቦችን ማድረስ** |

ለተወኩል (መመካት/ዒባዳ መሆን) ማስረጃው: **«ምእመናንም እንደኾናችሁ በአላህ ላይ ተመኩ»** (አል-ማኢዳህ 23) እንዲሁም: **«በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው እርሱ በቂው ነው።»** (ጦላቅ 3) **(1)**.

ለ አር-ረግባህ (መከጀል)፣ **(2)** መሸሸ የታከለበት ስጋት (አር-ረህባህ) እና **(3)** ራስን ማዋረድን ያዘለ ፍርሃት(አል-ኹሹዕ) **(4)** ማስረጃቸው: **«{…እነርሱ በበጎ ሥራዎች የሚቻኮሉ ከጃዮችና ፈሪዎች ኾነው የሚለምኑንም ነበሩ። ለእኛ ተዋራጆችም ነበሩ።»** (**አል-አንቢያእ** 90) (2)

**(2) መከጀል (አር-ረግባህ):** ተወዳጅ ወደሆነው ነገር ለመድረስ መውደድ

**(3) መሸሸ የታከለበት ስጋት (አር-ረህባህ):** ከድርጊት ጋ የተቆራኘ ከሚፈራው ነገር የሚያርቅ ፍርሃት ነው።

**(4) ራስን ማዋረድን ያዘለ ፍርሃት(አል-ኹሹዕ):** ለአላህ ሸሪዓዊም ይሁን ዓለማዊ ለሆነ ፍርዱ እጅን በሰጠ መልኩ ለአላህ ልቅና ማንበደድና መዋራድ ማለት ነው።

◆ ወደ አላህ መንገድ የገባ ሰው በሚያጠፋው መልኩ አንዱን ካንዱ ሳያስበልጥ ፍርሃትንና ተስፋን ሊሰንቅ ይገባዋል፣ ፍርሃትም ተስፋም እንደ ሁለት ክንፍ ሁነው እሱ ዘንድ ሊኖሩ ግድ ነው።

አል-ኸሽየህ (ዒባዳ ስለመሆኑ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «…አትፍሯቸውም፤ፍሩኝም…» (አል-በቀራህ 150) **(1)** (ወደ አላህ ተፀፆቶ) መመለስ (ዒባዳ ስለመሆኑ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «…ወደ ጌታችሁ (በመጸጸት) ተመለሱ። ለእርሱም ታዘዙ።» (አል-ዙመር 54) **(2).** እገዛ መሻት (ዒባዳ ለመሆኑ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «{አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን፡፡» (አል-ፋቲሓ 5) በሐዲሥም ተከታዩን እናገኛለን "እገዛን ከፈለግክ በአላህ ታገዝ።" (ቲርሚዚይ)**(3)** ጥበቃ መሻት (ዒባዳ ለመሆኑ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «{በል «በተፈልቃቂው ጎህ ጌታ እጠበቃለሁ።» (አል-ፈለቅ 1) እንዲሁም «በል «በሰዎች ፈጣሪ እጠበቃለሁ።» (አን-ናስ 1) **(4)** *ኢስቲቓሣ (ከጭንቅ ገላጋይን መሻት/ዒባዳ ለመሆኑ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው:* «ከጌታችሁ እርዳታን በፈለጋችሁ ጊዜ… ለናንተ የተቀበላችሁን (አስታውሱ)።»(አል-አንፋል 9) **(5)** ለእርድ (ዒባዳ መሆን) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው:: ««ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው» በል። (162«ለእርሱ ተጋሪ የለውም። በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ። እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ» (በል)።» (አል-አንዓም 162-163). *ከሓዲሥም* **"ከአላህ ውጭ ላለ አካል(ታላቅነት ብሎ) ያረደ በአላህ ተረግሟል።"** (*ሙስሊም*) **(6).**

**(1) አልኸሽየህ (እውቀት ላይ የተመሰረተ ፍርሃት):** የሚፈራውን አካል ታላቅነትና የስልጣን ሙሉነት በማስመልከት እውቀት ላይ የተመረኮዘ ፍርሃት ነው።

**(2) (ወደ አላህ) መመለስ:** ትእዛዛቱን በመፈፀምና ክልከላውን በመቆጠብ ወደ አላህ መመለስ፤ «...وَأَنِيبُوا» «**...ተመለሱ...**» «…ወደ ጌታችሁ (በመጸጸት) ተመለሱ። ለእርሱም ታዘዙ።» (አል-ዙመር 54) ማለትም ጉዳይህን ለአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ በመስጠት፤ ምክንያቱም ባርያ ነህና ባርያ ደሞ ለጌታው (እጅ እግሩን) ሊሰጥ ግድ ነው። ጌታው ደሞ አላህ ነው። ልክ ነብዩ ﷺ በሚከተለው መልኩ እንዳሉት "ጌታ አላህ ነው።"

**(3) እገዛን መሻት(አል-ኢስቲዓናህ):** እገዛ መፈለግ ማለት ነው። « {አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን።» (አል-ፋቲሓ 5) በዚህ አንቀፅ የዓረብኛው አገላለፅ በሰዋሰዋዊ ህጉ መሰረት ገደብ የሚያስቀምጥ አገላለፅ ነው **{تقديم ما حقه التأخير يفيد الحصر}** እንደሚባለው ማለት ነው። ማለትም አንገዛም አንተን ቢሆን እንጅ፤ እርዳታን አንለምንም አንተን ቢሆን እንጅ ማለት ነው።

**(4) ጥበቃን መሻት:** መጠበቅን መፈለግ ማለት ነው። ያ ማለት ከሚሸሽ ነገር ከለላ መፈለግ «أعوذ» «**አዑዙ**» ማለት "እጠበቃለሁ፣ እከለላለሁ" ማለት ነው።

**(5) አል-ኢስቲቓሣህ (ከጭንቅ የሚገላገልን መሻት):** ከጭንቅና ከውድመት መዳንን መፈለግ ማለት ነው።

✪ አራቱን: እገዛን መሻት፣ ጥበቃን መሻት፣ ከጭንቅ ገላጋይን መሻትና አማላጅነት(ሽምግልና) አራት መስፈርቶች ከተሟሉባቸው ከፍጡራኖች መፈለግ የተፈቀዱ ናቸው፤ በህይወት ካለ ሊሆን ይገባል፣ ያለና የቀረበ ሊሆን ይገባል፣ ቻይ ሊሆን ይገባዋል እና ሰበብ ተደርጎ ሊያዝ ይገባዋል።

**(6) እርድ ማቅረብ:** ለየት ባለ መልኩ ደም በማፍሰስ ህይወት መቅጠፍ።

**እርድ (ማቅረብ) ወደ ሶስት ይከፈላል**

| ለአላህ (ታላቅነት) ብሎ ማረድ | ከአላህ ውጪ ላለ አካል ብሎ ማላቅና ውዴታ በታከለበት መልኩ ማረድ | የተፈቀደ እርድ |
|---|---|---|
| ሀድይ፣ ኡዱሒያና ምፅዋትን ይመስል | ለጅን እና ለቀብር ባለቤቶች ብሎ ማረድ፤ ይህ ትልቁ ሽርክ ነው። | እንግዳን ለማክበር፣ ለንግድም ይሁን ለሌላ ስጋውን ፈልጎ በግ/ፍየል ማረድ። |

ስለት (ዒባዳ ለመሆኑ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «(ዛሬ) **በስለታቸው ይሞላሉ። መከራው ተሰራጪ የኾነንም ቀን ይፈራሉ።»** (አል-ኢንሳን 7)

**ል. በ.:** እርድን በማስመልከት ተጨማሪ ማብራሪያ በአላህ ፍቃድ ኪታቡ ተውሒድ ላይ ይመጣል።

**(1) የስለት ፍች**

| እንደሸሪዓ: | እንደቋንቋ: |
|---|---|
| ግዴታ ባልሆነበት ነገር አንድ ሰው ራሱን ግዳጅ ውስጥ ማስገባቱ ማለት | ቃል መግባትና ግዳጅ ውስጥ መግባት ማለት ነው። |

**ል. በ.:** ስለት ዝርዝሩ በአላህ ፍቃድ ወደኃላ ኪታቡ ተውሒድ ላይ የሚመጣለት የሆነ ዓይነት፣ ቅድመ መስፈርቶችና ማሰረዣ(ከፋራ) አለው።

**የስለት ዓይነቶች**

| ለአላህ የሚደረግ ስለት | ከአላህ ውጭ ላለ አካል የሚደረግ ስለት |
|---|---|

ሸይኹ እነኝህን የዒባዳ አይነቶች መጥቀሱ ከመገደብ አንፃር ሳይሆን እንደምሳሌ ነው ምክንያቱም ያልተወሱ በርካታ የዒባዳ አይነቶች አሉና። ጭብጡ ሃሳብ ከነዚህ ዒባዳዎች መካከል አንዳች ነገር ለሌላ አካል አሳልፎ የሰጠ በርግጥም ትልቁን ሽርክ ፈፅሟል ነው።

**ሁለተኛው መሰረታዊ መርሆ:** ዲነል ኢስላምን በማስረጃ ማወቅ (ነው)። ያም ለአላህ በተውሒድ እጅ እግርን መስጠት፣ በታዛዥነት ለሱ ተገታች መሆን፣ ከሽርክ እና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት።

ሶስት እርከኖች አሉት: ኢስላም፣ ኢማንና ኢሕሳን፤ እያንዳንዱ እርከንም ማእዘን አለው።

**የመጀመርያው እርከን:** ኢስላም **(1)**

የእስልምና ማእዘናት አምስት ናቸው። የ "ላ ኢላሀ ኢለሏህ ሙሓመዱን ረሱለሏህ" የምስክርነት ቃል **(2)** ፣ ሶላትን ስርአቷን አሟልቶ መስገድ፣ ዘካን ማውጣት፣ ረመዷንን መፆምና የአላህን ቤት ሓጅ ማድረግ ናቸው።

**(1)** ሸይኹ ሁለተኛው መሰረት ላይ ወጣ፣ ያም አንድ ባርያ ዲኑን ማወቁ ነው። በሚከተለው መልኩ ዲነል ኢስላምን ማስተዋወቅን ጀመረ:

## የመጀመርያው እርከን ኢስላም

ያም ለአላህ በተውሒድ እጅ እግርን መስጠት፣ በታዛዥነት ለሱ ተገታች መሆን፣ ከሽርክ እና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት።

"ኢስላም" ለሚለው ቃል ፍቺ ይህ ነው፤ ጉዳይህን ለአላህ ልትሰጥ ማለት ነው። ምክንያቱም ባርያ ነህና ባርያ ደሞ ለጌታው (እጅ እግሩን) ሊሰጥ ግድ ነው። ጌታውም አላህ ነው። ልክ ነብዩ ﷺ "ጌታ አላህ ነው።" እንዳሉት ማለት ነው።

ከዚያም ዲንን ወደ ሶስት እርከን ከፈሉት:




**(2)** የእስልምና ማእዘናት አምስት ናቸው። የመጀመሪያው

የ "ላ ኢላሀ ኢለሏህ ሙሓመዱን ረሱለሏህ" የምስክርነት ቃል ነው።

ሸይኹ አላህ ይዘንለትና "ላ ኢላሀ ኢለሏህ" ን የምስክርነት ቃል ማስረጃ አድርጎ ጠቀሰ፤ ትርጉሙንም አብራራ። ያም: "ከአላህ ውጭ በእውነት የሚመለክ የለም" ማለት ነው።

**የኢኽላስ ምስክርነት ተከታዮቹን ልታካትት ግድ ነው**

ማውገዝ | ማፅደቅ

"ላ ኢላሀ" በሚለው ቃል "ነፍይ" የምንለው ወይም ደሞ ማውገዝ ይገኝበታል

"ኢለሏህ" በሚለው ቃል ደሞ "ኢሥባት" የምንለው ወይም ደሞ ማፅደቅ ይገኝበታል

ይህ አይነቱ አገላለፅ መገደብንና ማፅደቅን ይጠቁማል። ምክንያቱም ዒባዳን በተገደበ መልኩ ለአላህ ብቻ በማፅደቅ ከሌላው የሚያጠራ አገላለፅ ነውና።

ለዚህም ነው ሸይኹ አላህ ይዘንለትና "ግልፅ የሚያደርጋት ማብራሪያዋ በማለት (ቀጣዩን አንቀፅ ያስከተሉት): **«ኢብራሂምም ለአባቱና ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)። «እኔ ከምትግገዙት ሁሉ ንጹሕ ነኝ።»** (26) **«ከዚያ ከፈጠረኝ በስተቀር (አልግገዛም)።...»**

**«...ከምትግገዙት ሁሉ ንጹሕ ነኝ።...»** "ላኢላሀ" ማለት ሲሆን

**«...ከዚያ ከፈጠረኝ በስተቀር...»** ማለት ደሞ "ኢለሏህ" ማለት ነው።

ለሸሃዳህ (የምስክርነት ቃል) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«አላህ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ) ሲኾን ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መኾኑን መሰከረ። መላእክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም (እንደዚሁ መሰከሩ)። ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። አሸናፊው ጥበበኛው ነው።።»** (አሊ ዒምራን 18)

ትርጉሙም: "ከአላህ ውጭ በእውነት የሚመለክ የለም።"

"ላ ኢላሀ": ከአላህ ውጭ የሚመለከውን በሙሉ ታወግዛለች፤

"ኢለሏህ": አምልኮን ለአላህ ብቻ በአምልኮ ተጋሪ በሌለው መልኩ ያፀድቃል፤ በንግስናውም ተጋሪ እንደሌለው ሁሉ።

ግልፅ የሚያደርጋት ማብራሪያዋ ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«{ኢብራሂምም ለአባቱና ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)። «እኔ ከምትግገዙት ሁሉ ንጹሕ ነኝ።»**(26) **«ከዚያ ከፈጠረኝ በስተቀር (አልግገዛም)። እርሱ በእርግጥ ይመራኛልና።»** (27) **በዝርዮቹም ውስጥ ይመለሱ ዘንድ (ባንድ አምላክ ማመንን) ቀሪ ቃል አደረጋት።** (28)»(ዙኽሩፍ 26-27)

እንዲሁም: «የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ፡፡ (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤ በላቸው፡፡ እምቢ ቢሉም፡- እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክሩ በሏቸው፡፡» (አሊ-ዒምራን 64) (1)

የሆነ ሰው "የ 'ላኢላሀ ኢለሏህ' ትርጉም 'ላ መዕቡደ ኢለሏህ/ከአላህ ውጭ የሚመለክ የለም' ማለት ነው።" ቢልስ? እኛም እንለዋለን "ይህ አገላለፅ ስህተት ነው።" እንለዋለን። ምክንያቱም በዚህ አገላለፁ መሰረት ከአላህ ውጭ የሚመለከውን በሙሉ ትክክል እያደረገ ነውና። ነገር ግን "...በእውነት የሚመለክ..." በሚለው አገላለፅ ከአላህ ውጭ በሚመለኩት እንደካደ እና ከአላህም ውጭ **በእውነት** የሚመለክ እንደሌለ ግልፅ ያደርጋል።

"የ 'ላኢላሀ ኢለሏህ' ትርጉም 'ከአላህ ውጭ በእውነት ጌታ የለም' ማለት ነው።" ቢልስ?

እኛም እንለዋለን "ይህ ንግግር ትክክል ነው፤ ነገር ግን የ 'ላኢላሀ ኢለሏህ' ትርጉም አይደለም። ይህ ተውሒዱ ሩቡቢያ ነው፤ ይህ ደሞ ነብዩ ﷺ የተላኩባቸው ሙሽሪኮች የሚያፀድቁት ግን ደሞ እስልምና ውስጥ ያላስገባቸው አቋም ነው።"

(1) «የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ፡፡...» አንቀፁ በሃይማኖቶች መካከል ማስማማት የሚባለው ውድቅ እንደሆነ ያስይዘናል።

**(1)** ሸይኹ አላህ ይዘንላትና ይህን አንቀፅ ሙሓመድ የአላህ መልእክተኛ ለመሆናቸው ማስረጃ አድርጎ ጠቀሰ፤ በአንቀፁ ላይ አላህ መልእክተኝነታቸውን በቋንቋዊ ህጉ መሰረት ሶስት ማጠናከሪያ ሊባል በሚችል አገላለፅ ነው ያፀናላቸው።

**(2)** ሸይኹ አላህ ይዘንላትና የ "ሙሓመደን ረሱሉሏህ" የምስክርነት ቃል ትርጉም አብራራ: ይህ የምስክርነት ቃል ትክክለኛ ይሆን ዘንድ በእያንዳንዱ ወንድም ሆነ ሴት ሙስሊም ተከታዮቹ ነጥቦች ግዴታ ናቸው:

መልእክተኛው ﷺ ባዘዙበት መታዘዝ፣ የተናገሩበት እውነት ብሎ መቀበል፣ ካስጠነቀቁትና ከከለከሉት መራቅና እሳቸው በደነገጉት መልኩ እንጅ አላህ ላይመለክ የአላህ ሶለዋት እና ሰላም ይስፈንባቸውና።

ሙሓመድ የአላህ መልእክተኛ ለመሆናቸው ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«ከነፍሳችሁ የሆነ ችግራችሁ በእርሱ ላይ ጽኑ የሆነ፣ በእናንተ (እምነት) ላይ የሚጓጓ፣ በምእምናን (ላይ) ርኅሩኅ አዛኝ የኾነ መልክተኛ በእርግጥ መጣላችሁ።»** (አት-ተውባህ 128) **(1)**

"ሙሓመድ የአላህ መልእክተኛ ነው" የሚለው የምስክርነት ቃል ትርጉም: ባዘዙት መታዘዝ፣ የተናገሩትን እውነት ብሎ መቀበል፣ ካስጠነቀቁትና ከከለከሉት መራቅ እና እሳቸው በደነገጉት መልኩ እንጅ አላህ ላይመለክ ማለት ነው። **(2)**

**ሙሓመድ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን መመስከር "የሚመለኩ ሳይሆን የሚያመልኩ ባርያ እና የማያስተባብሏቸው መልእክተኛ ናቸው " ብሎ ማመን ነው ይህ ሲባል:**

| | | | |
|---|---|---|---|
| የአላህ ሶለዋት እና ሰላም ይስፈንባቸውና ባዘዙት ሁሉ ልንታዘዛቸው፤ ምክንያቱም ከአላህ የሚያደርሱ ልኡክ ናቸው | የአላህ ሶለዋት እና ሰላም ይስፈንባቸውና የተናገሩትን እውነት ብሎ መቀበል፤ እውነተኛና እውነት የሚባሉ ናቸው | ያስጠነቀቁትንና የከለከሉትን መራቅ፤ ነብዩ ﷺ የከለከሉትን በአንድ በኩል አድርገህ አንተ በሌላኛው በኩል ልትሆን | ጥራት ይገባውና አላህ ላይመለክ ነው ከነብዩ ﷺ በመጣው መልኩ ቢሆን እንጅ፤ በዚህ ደሞ ለሙብተዲዖች ረድ (አፀፋዊ ምላሽ) አለበት። |

ለሶላትና ለዘካት እንዲሁም የተውሒድ ተፍሲር ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«አላህን ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ ቀጥተኞች ኾነው ሊግገዙት፣ ሶላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ ዘካንም ሊሰጡ እንጅ ያልታዘዙ ሲኾኑ (ተለያዩ)። ይህም የቀጥተኛይቱ (ሃይማኖት) ድንጋጌ ነው።»** (አል-በይናህ 5) (1)

ለፆም ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«እናንተ ያመናችሁ ሆይ ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡»**(አል-በቀራህ 183) (2)

ለሓጅ ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«...ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው። የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው።»** (አል-ዒምራን 97) **(3)**

**(1) ሶላት ሁለተኛው ማአዘን:**

ያም በተክቢር (አሏሁ አክበር) ተጀምሮ በተስሊም (አሰላሙ ዓለይኩም) የሚያልቅና አላህን (ለየት ባሉ) ንግግሮችና ተግባሮች ማምለክ ማለት ነው። የዲን መሰረት ነች፤ የተደነገገችውም ቀጥታ ከአላህ ለነብዩ ነው። ይህም የሆነው ነብዩ ﷺ ወደ ሰማይ አርገው በነሩበት ጊዜ ነው።

**ዘካ ሶስተኛው ማአዘን:**

በቋንቋ ደረጃ: መጨመርና መጥራራት ማለት ነው።

ሁለት አይነት ነች: የአካል ዘካ እና የገንዘብ ዘካ

**(2) ፆም አራተኛው ማአዘን:**

**በቋንቋ ደረጃ**: መታቀብ ማለት ሲሆን

**በሸሪዓ ደረጃ**: ፀሃይ ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ በመፆም ኒያ ፀሃይ እስከምትጠልቅበት ሰዓት ድረስ ከሚያስፈጥሩ ነገራቶች በመታቀብ ለአላህ መገዛት ማለት ነው። ፆም ሶስቱንም የሶብር አይነቶች አቅፎ የያዘ በመሆኑ በላጭ ከሚባሉ የአምልኮ አይነቶች የሚመደብ ነው፤ የፆመኛን ምንዳ አላህ ወደራሱ አስጠግቶ መግለፁ ደሞ ጉዳዩን ከፍ ከሚያደርጉልን ነጥቦች መካከል ነው።

**(3) ሓጅ አምስተኛው ማአዘን:**

**በቋንቋ ደረጃ**: ማሰብ ማለት ሲሆን

**በሸሪዓ ደረጃ**: ደግሞ ከነብዩ ﷺ ፈለግ በመጣበት መልኩ የሓጅ ስርዓቶችን በመፈፀም ለአላህ መገዛት ማለት ነው።

ያም ከእድሜ ልክ አንዴ ግዜ ሓጅ ማድረግ (በሚችል) ሙስሊም ላይ ሁሉ ላይ ግዴታ ነው።

## ሁለተኛዋ እርከን: ኢማን

**በቋንቋ ደረጃ፡** አምኖ መቀበል
**በሸሪዓ ደረጃ**: በሸሪዓ ደረጃ: በአንደበት የሚባል፣ በልብ እምነት ተደርጎ የሚያዝ፣ በአካልና በልብም የሚተገበር በታዛዥነት የሚጨምርና በአመፅ የሚቀንስ ነው።

እምነት እንደሸሪዓው አምስት ነገራቶችን ሊያሟላ ግድ ነው። ከነዚህ ነገራቶች አንዳች ነገር ከጎደለ አህሉ ሱና ወልጀማዓ ዘንድ ኢማን ከሚለው ጥቅል ፍች ይወጣል።

ለነኝህ ጥቅል ፍቹ ላይ ለተጠቀሱት አምስት ነገራቶች ማስረጃቸው ምንድን ነው? የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ብለዋል: "ከፍተኛው 'ላኢላሀ ኢለሏህ' የሚለው ቃል ሲሆን..." በሚለው ሓዲሥ መሰረት ንግግር ኢማን ውስጥ እንደሚካተት ይጠቁመናል።

"ዝቅተኛው ደሞ አስቸጋሪን ነገር ከመንገድ ማስወገድ ነው።" በሚለው መሰረት ደሞ ተግባርም ኢማን ውስጥ እንደሚካተት ይጠቁማል።

"ሓያእም..." የሚለው ደሞ የልብን ተግባር የሚገልፅ ነው።

**ሁለተኛዋ እርከን: ኢማን**

ሰባ ምናምን ደረጃ ያለው ሲሆን ከፍተኛው ***ላኢላሀ ኢለሏህ*** ዝቅተኛው ደግሞ ከመንገድ የሚያሰናክልን ነገር ማስወገድ ነው፤ ሓያእም የኢማን ቅርንጫፍ ነው።

ስድስት ማአዘኖች አሉት:

በአላህ፣ በመላእክቶቹ፣ በኪታቦቹ፣ በመልእክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀንና ልታምን እንዲሁም በቀደር በክፉውም በደጉም ልታምን ነው።

ለነዚህ ስድስት ማአዘኖች ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም። ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም፣ ያመነ ሰው...»** (አል-በቀራህ 177).

ለቀደር ማስረጃው ደግሞ ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«እኛ ሁሉን ነገር በልክ ፈጠርነው።»** (አል-ቀመር 49).

ከፍ ያለው አላህ (ስለ ሙናፊቆች) እንዲህ ይላል: **«ማንኛችሁ ነው ይህች (ምዕራፍ) እምነትን የጨመረችለት የሚል ሰው አልለ»** (አት-ተውባ 124) ይህ ደሞ ኢማን እንደሚጨምር ጥቆማ የሚሰጥ ሲሆን እንደሚጨምር ከፀና (በተቃራኒው) መቀነሱ የግድ ነው። ስለዲን መቀነስ በግልፅ ከነብዩ ﷺ ተከታዩ ሓዲሥ መጥቷል "**የዲንም የአዕምሮም ጉድለት ኑሮባት... አላየሁም።**" ስለዚህ ዲን ይቀንሳል።

## ስድስቱ የኢማን ማአዘናት

- በ**አላህ** ማመን
- በ**መላ እክቶች** ማመን
- በ**ኪታበ ች** ማመን
- በ**መልእ ክተኞች** ማመን
- በ**መጨ ረሻው ቀን** ማመን
- በክፉም በደጉም **ቀደር** ማመን

## የመጀመሪያው ማአዘን በአላህ ማመን አራት ነገራቶችን ግድ ያስብላል

- ጥራት ይገባውና በአላህ ህልውና ማመን: በአራቱም መልኩ የተረጋገጠ ነው
- በ(ተውሒደል ሩቡቢያህ)ጌትነ ት አሃዳዊነቱ ማመን
- በ(ተውሒደል ኡሉሂያህ)አምላ ክነት አሃዳዊነቱ ማመን
- በ(ተውሒደል አስማኢ ወሲፋት )ስምና ባህርያት አሃዳዊነቱ ማመን

**በአዕምሮ**
ፍጥረት ያለ ፈጣሪ ሊገኝ መቻሉን አዕምሮ አይቀበለውም« ወይስ ያለ አንዳች (ፈጣሪ) ተፈጠሩን? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን?» (አል-ጡር 35)

**በተጨባጩ**
በችግርና በመከራ ጊዜ እጅህን ወደላይ ከፍ አድርገህ "ያ ረብ! (ጌታየ ሆይ!)" ብትል ችግርህ በአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ፍቃድ ተቀርፎልህ ታገኘዋለህ።

**በተፈጥሮአዊ ማንነት**
"ተወላጅ ሁሉ የሚወለደው በተፈጥሮአዊ ማንነቱ (በኢስላም ላይ) ሆኖ ነው፤ ወላጆቹ ናቸው አይሁድ ወይም ክርስትያን ወይም ደሞ እሳት አምላኪ የሚያደርጉት።" (ቡኻሪይና ሙስሊም)

**በሸሪዓዊ እይታ**
ኢብኑል ቀይም አላህ ይዘንለትና "በቁርአን ምንም አይነት አንቀፅ የለም ወደ አላህ አሃዳዊነት የሚጠቁም ቢሆን እንጅ።"

## ሁለተኛው ማአዘን በመላእክቶች ማመን

መላእክቶች: የማይታየው አለም ላይ ያሉ፤ አላህ ከብርሃን የፈጠራቸው፤ አላህን የማያምፁ ታዛዦች፤ መንፈስ (ህይወት) አላቸው «ቅዱሱ መንፈስ» (አል-ነሕል 87) አካልም «... መላእክትን ባለ ሁለት ሁለት፣ ባለ ሶስት ሶስትም፣ ባለ አራት አራትም ክንፎች የኾኑ መልክተኞች አድራጊ ለኾነው አላህ ይገባው። በፍጥረቱ ውስጥ የሚሻውን ይጨምራል።...» (ፋጢር 1) አዕምሮም ልቦናም አላቸው «ከልቦቻቸው ላይ ድንጋጤው በተገለጸም ጊዜ ጌታችሁ ምን አለ?» ይላሉ» (ሰባእ 23) በነሱው (ህልውና) እናምናለን፤ ከነሱ መካከል ስሞቻቸውን ባሳወቀንም ጅብሪል፣ ሚካኤልንና ኢስራፊልን ይመስል፤ ባህርያቸውንም «...አላህን ያዘዛቸውን ነገር (በመጣስ) አያምጹም። የሚታዘዙትንም ሁሉ ይሠራሉ።» (አት-ተሕሪም 6) በድርጊቶቻቸውም የዓርሽ ተሸካሚዎችን ይመስል፤ እነሱን በማስመልከት በጥቅሉም ይሁን በዝርዝር የመጣውን ሁሉ እናምናለን።

## ሶስተኛው ማአዘን በመፃህፍቶች ማመን

አላህ በዘይቤያዊ አነጋገር ሳይሆን በግልፅ የተናገረበት መሆኑን እናምናለን፤ ከሱ የወረዱ እንጅ ፍጥረታት አለመሆናቸውን፤ ከመልዕክተኞቹ ጋ ሁሉ መፃህፍትን እንዳወረደላቸውም፤ በኪታቦቹም እናምናለን አላህ ስለ ኪታቦቹ በነገረን ስም፣ መረጃና ህግጋት እስካልተሻረ ድረስ በጥቅሉም በዝርዝርም እናምናለን። ቁርአንም ከሱ በፊት የወረዱትን ተውራት፣ ኢንጅል፣ ዘቡር፣ የኢብራሂምና የሙሳ (ዓለይሂማ ሰላም) ሱሑፍንም ሁሉ እንደሻረ እናምናለን።

## አራተኛው ማአዘን በመልእክተኞች ማመን

ከጌትነት መገለጫ እንዳችም ነገር የሌላቸው የሰው ልጆች መሆናቸውን፤ አምላኪ ባርያዎች እንጅ የማይመለኩ መሆናቸውን፤ አላህ የላካቸውና መልእክቱን ያስተላለፈላቸው እንዲሁም በተአምራቶች ያጠናከራቸው ናቸው፤ እነሱም አደራቸውን ተወጥተው ህዝቦቻቸውንም መክረው ተልእኳቸውንም አድርሰዋል፤ በአላህም መንገድ እውነተኛውን ትግል ያደረጉ መሆናቸውን ማመናችን ግዴታ ነው፤ በነሱም (ህልውና) እናምናለን፡ አላህ እነሱን በማስመልከት ስለስሞቻቸውም፣ ሥለባህሪዎቻቸውም ጥቅል በሆነ መልኩም ይሁን በዝርዝርም የነገረንን ሁሉ እናምናለን። የነብያቶች መጀመርያ አደም፤ የመልእክተኞች መጀመርያ ኑሕና የነብያቶችም ይሁን የመልእክተኞች መደምደምያ ሙሓመድ ሰለሏሁ ዓለይሂሙ ሰላም መሆናቸውን እንዲሁም ቀደምት ሸሪዓዎች በሙሉ ነብዩ ሙሓመድ ﷺ ይዘውት በመጡት እንደተሻረ እናምናለን። የቆራጥነት ባለቤት የሚባሉትም አላህ ቁርአኑ ላይ በሁለት ቦታዎች በሱረቱ ሹራ እና በሱረቱል አሕዛብ ጠቅሷቸዋል፤ እነሱም: ሙሓመድ ﷺ ፣ ኑሕ ዓለይሂ ሰላም፣ ኢብራሂም ዓለይሂ ሰላም፣ ሙሳ ዓለይሂ ሰላም፣ ዒሳ ዓለይሂ ሰላም ናቸው።

## አምስተኛው ማአዘን በመጨረሻው ቀን ማመን

ነብዩ ﷺ ከሞት በኃላ ስላለው በተናገሩት ሁሉ ማመንን የሚያጠቃልል ነው። የቀብር ፈተና፣ በጥሩምባ መነፋቱ፣ ሰዎች ከቀብራቸው መቀስቀሳቸው፣ በሚዛን፣ በመዝገብ፣ በሲራጥ፣ በሓውድ (የነብዩ ወንዝ) ፣ በምልጃ (ሸፋዓ)፣ በጀነት፣ በጀሃነም፣ ከሞት በኃላ ጀነትም ውስጥ አማኞች ጌታቸውን ማየታቸው እና በሌሎችም የሩቅ ሚስጥሮች (እናምናለን)።

## ስድስተኛው ማአዘን በበጎውም በመጥፎውም ቀደር ማመን

## (ይህ ማአዘን አራት ነገራቶችን ሊያካትት ግድ ይለዋል)

**እውቀት:** ጥራት ይገባውና አላህ ሁሉንም ነገር በጥቅሉም በዝርዝርም እንደሚያውቅ ማመን

**መፃፉ:** አላህ ሁሉም ነገር እስከዕለተ ፍፃሜ ድረስ ያለውን ክንውን ሁሉ እንደፃፈው ማመን

**መሻት:** አላህ የሻው እንደሚሆን አላህ ያልሻው ደሞ እንደማይሆንና ባርያም የራሱ ነፃ ፍላጎት እንዳለው ነገር ግን ከአላህ መሻት ስር መ|የኑን ማመን

**መፍጠር:** የሰው ልጆችም ሌላውም ከድርጊቶቹ ጋ አላህ የፈጠረው መሆኑ፤ ማስረጃውም: «…አላህ የሁሉም ፈጣሪ…» (አል-አንዓም 101) «አላህ እናንተንም የምትሠሩትንም የፈጠረ ሲኾን።» (አስ-ሷፋት 96)

ማወቅም መፃፉ መፍለግና መፍጠሩ

እሱው ነው ክንውኑ ሂደት የፍጡሩ

በሚለው ስንኝ አራቱም እርከኖች ይገኛሉ።

## ሶስተኛው ደረጃ ኢሕሳን ከፍተኛው የዲን እርከን ሲሆን፤ አንድ ማአዘን ያለውና ከስሩ ሁለት

**የተጣደ አምልኮ (ዒባደቱል ሙሻሀዳህ)**

(አምልኮውን ከማጣጣም ጋ) አላህ ዘንድ ላለው ወዶ፣ ከጅሎና ናፍቆ የሚደረግ አምልኮ ነው፤ የነብያቶችና የመልእክተኞች ዓለይሂሙ ሰላም አምልኮ ሲሆን ሌሎችም ሊደርሱበት የሚችሉት ደረጃ ነው።

**የቁጥጥር አምልኮ (ዒባደቱል ሙራቀባህ)**

(የሚቆጣጠር እንዳለ አስቦ) በፍርሃትና በስጋት የሚደረግ አምልኮ ሲሆን የትኛውም ሙስሊም ከዚህ ደረጃ አይወጣም።

**ሶስተኛው ደረጃ**: ኢሕሳን አንድ ማአዘን ነው ያለው "**አላህን ልክ እንደምታየው ሆነህ ልታመልከው ነው፤ አንተ ባታየውም እሱ ያይሃልና።**" ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **«{አላህ ከእነዚያ ከሚፈሩትና ከእነዚያም እነሱ መልካም ሠሪዎች ከኾኑት ጋር ነውና፡፡»** (አል-ነሕል 128) እንዲሁም: **«አሸናፊ አዛኝ በኾነው (ጌታህ) ላይም ተጠጋ። ۝ በዚያ ለሶላት በምትቆም ጊዜ በሚያይህ። ۝ በሰጋጆች ውስጥ መዘዋወርህንም (በሚያየው ጌታህ ላይ ተጠጋ)። ۝ እነሆ እርሱ ሰሚው ዐዋቂው ነውና። ۝»** (አሽ-ሹዐራእ 217-220) እንዲሁም: **«(ሙሐመድ ሆይ!) በማንኛውም ነገር ላይ አትሆንም፣ ከርሱም ከቁርኣን አታነብም፣ ማንኛውንም ሥራ (አንተም ሰዎቹም) አትሠሩም በገባችሁበት ጊዜ በናንተ ላይ ተጠባባቂዎች ብንሆን እንጂ።»** (ዩኑስ 61) ከሓዲሥ ማስረጃውም: የተሰራጨው ከዑመር ረድየሏሁ ዓንሁ የተዘገበው የጅብሪል ሓዲሥ፡

**ማብራሪያ:** በዚህ ደረጃ ላይ ያለ ባርያ ለአላህ ውዴታ ኖሮት ምንም ያህል ፍርሃት ሳይኖረው ማለት አይደለም፤ ነገር ግን በዚህ ደረጃ ላይ ላለ ባርያ ለአምልኮ ከፍተኛ ግፊቱ የሚመነጨው ለአላህ ካለው ውዴታ ነው፤ ነብዩ ﷺ ም "ታድያ አመስጋኝ ባርያ አልሆንምን!" ማለታቸውም እዚሁ የሚመደብ ነው።

«ከእለታት አንድ ቀን የአላህ መልእክተኛ ﷺ ጋ ሳለን ልብሱ በጣም ነጭ ፀጉሩ በጣም ጥቁር የሆነ ሰው ብቅ አለ። የመንገደኛ ምልክትም አይታይበትም ከኛ መካከልም የሚያውቀው ሰው የለም። ወደ ነብዩ ﷺ ተጠግቶ ጉልበቱን ከጉልበታቸው አስደግፎ ተቀመጠ። እጁንም ታፋው ላይ አደረገና "አንተ ሙሐመድ ሆይ! እስኪ ስለ ኢስላም ንገረኝ?" አላቸው። የአላህ መልዕክተኛም ﷺ **"ኢስላም `ማ በ'ላኢላሀ ኢለሏህ ሙሓመደን ረሱሉሏህ' የምስክርነት ቃልህን ልትሰጥ፣ ሶላት (ስርአቱን አሟልተህ) ልትሰግድ፣ ዘካን ልታወጣ፣ ረመዷንን ልትፆም፣ መንገዱን ከቻልክ ደሞ ሓጅ ልታደርግ ነው።"** አሉት። "እውነት ብለሃል" አላቸው። "ይጠይቀውና 'ትክክል ነህ' ይላቸዋል። ተገረምን!"» ይላል። «"ስለኢማንስ ንገረኝ እስኪ!" አላቸው። እሳቸውም **"በአላህ፣ በመላእክቶቹ፣ በኪታቦቹ፣ በመልእክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀንና ልታምንና በቀደርም ክፉውም ሆነ ደጉን ልታምን ነው።"** አሉት። "እውነት ብለሃል!" አላቸው። "እስኪ ደሞ ስለ ኢሕሳን ንገረኝ!" አላቸው። እሳቸውም **"አላህን ልክ እንደምታየው ሆነህ ልታመልከው ነው፤ አንተ ባታየውም እሱ ያይሃልና።"** "ስለ ሰዓቲቱስ ንገረኝ እስኪ!" አላቸው። እሳቸውም **"ተጠያቂው ከጠያቂው በተሻለ የሚያውቀው ነገር የለም።"** አሉት። "ታድያ እስኪ ስለምልክቶቹ ንገረኝ!" አላቸው። እሳቸውም **"ሴት ባርያ ጌታዋን(አለቃዋን) መውለዷ፣ ጫማና ልብስ የሌላቸው ሰዎች እረኞች በህንፃ ሲወዳደሩ ታያለህ"** አሉትና ሄደ። ከዚያም ለተወሰነ ጊዜ ቆየን የአላህ መልዕክተኛም ﷺ **"ዑመር ሆይ! ጠያቂው ማን እንደሆነ ታውቃለህ?"** አሉ። እኔም "አሏህና መልዕክተኛው ﷺ ይበልጥ ያውቃሉ" አልኩኝ። እሳቸውም **"ጅብሪል ነው! የዲናችሁን ጉዳይ ሊያስተምራችሁ መጥቶ(ነው)።"** (ሙስሊም)

ይህ ሓዲሥ ለኢስላም፣ ለኢማንና ለኢሕሳን ማእዘናት ማስረጃ ነው። **"ተጠያቂው ከጠያቂው በተሻለ የሚያውቀው ነገር የለም።"** የሚለው ከአላህ ውጭ ሰዓቲቱ መች እንደምትቆም የሚያውቅ እንደሌለ አመላካች ነው።

**የአላህ መልእክተኛ ﷺ "እንዲት ባርያ ጌታዋን መውለዷ" ማለታቸው**

ማለትም: ከ(ልጆች) ጨቋኝነት ብዛት (አንፃር)

ወይም: የባርነት ብዛት

ወይም: የነገራቶች መቀያየር

ወይም ደሞ፡ ንጉስ (አለቃዋ) ባርያን ያገባትና ልጅ ትወልድለታለች ከዛም ከአባቱ ሞት በኃላ ልጅየው ንጉስና የእናቱ አሳዳሪ ይሆናል።

"ጫማና ልብስ የሌላቸው ሰዎች ነባር ድሃ እረኞች በህንፃ ሲወዳደሩ ታያለህ"

"العالة" ማለትም ድሆች ማለት ነው።

*ማለት ሁኔታዎች ተቀይረው ይህ ድህነትም ተቀይሮ ሃብትና መዝረክረክ ይሆናል።*

## ከጅብሪል (ዓለይሂ ሰላም) ሓዲሥ የምንረዳቸው ቁምነገሮች

**(1)** በአንድ ተማሪ ላይ ስድስት መብቶች አሉበት: የራሱ ሓቅ፣ የአስተማሪዎቹ መብት፣ የተማረበት ቦታ መብት፣ የባልደረቦቹ መብት፣ የመፃህፍቱ መብትና ለተማረው እውቀት ሓቅ ናቸው።

**የራሱ** ሓቅ: እውቀት አምልኮ በመሆኑ [ኢኽላስ እና ተከታይነት] ፤ የምር ሰለፎችን ተከታይ ሁን፤ በእውቀት የተመረኮዘ ፍርሃት፣ አሏህ ያየኛል ባይነት፣ የመተናነስ ክንፍን ዝቅ ማድረግ ኩራትን ማስወገድ ይኑርህ።

መብቃቃት እና ዙህድን መላበስ: በዒልም ነፀብራቅ ማሸብረቅ፤ የተሟላ ስብእናን መላበስ፣ የወንድነት መገለጫዎችን መተግበር መንደላቀቅን መተውና ከዛዛታ መቀማመጦች መራቅ፣ ርህራሄን፣ የፅናትና የማረጋገጥ ስብእናን ተላበስ።

(እውቀትን) በማደንም በኩል ጥልቅ ሃሳብ እና ከፍተኛ ጉጉት፣ እውቀቱን ነጥሎ ማውጣት፣ ሃላፊነትን መጠባበቅ፣ መንቀሳቀስ፣ የተማርከውን በፅሁፍና በሽምደዳ ጠብቆ ማቆየት፣

ቅርንጫፋዊ እውነትን ከመሰረታዊው ለይቶ እያወጡ ግንዛቤን ማስፋት፤ በአላህ ላይ መመካት፤ የእውቀት አደራን መጠበቅና እውነተኛ መሆን ይኖርብሃል።

የዒልም ፈላጊ ጋሻው "አላውቅም" ማለቱ፤ መዋእለ ንዋዩ(ጊዜ)ን በአግባቡ መጠቀም፣ ራስን ሰብሰብ ማድረግ (በጠቅላላ እውቀት)፣ (ዓረብኛውን) አስተካክሎ ማንበብ፣ ፈር ማስያዝ፣ በሂደት ደሞ ረዣዥም ኪታቦችን መላመድ።

ተገቢ ጥያቄን ስርአት ባለው መልኩ መጠየቅ፣ ለተባለው ማዳመጥ መገንዘብና መስራት፣ ያለጭቅጭቅ መወያየት፣ እውቀትን መከለስ፣ በቁርአንና በሓዲሥ መጠመድ፣ የየትምህርቱ መሰረታዊ ጭብጥ ማጥናት።

(በተማርከው) መስራት: ከፍ ብሎ ለመታየት ፍላጎትን፣ ዝናንና የዱንያ ፍቅርን መሸሽ፤

ስለራስ (እንዳጎደሉ) በመጥፎ መጠርጠር፣ ስለሌሎች (ይሻላሉ በሚል) በበጎ ጥርጣሬ ላይ መሆን፤

የእውቀት ዘካን አትዘንጋ: እውነት ላይ ደፋር፣ በመልካም አዛዥ ከመጥፎ ከልካይ፣ ጥቅም እና ጉዳትን ማመዛዘን፣ እውቀትን እያሰራጩ ሌሎችን መጥቀምን ማሰብ፣ ያለህን ደረጃ ተጠቅመህ በሙስሊሞች መካከል ማስተካከልና እውነትን ማሰራጨት ነው።

ተከባብረህ መኖር፣ እውቀትን መጠበቅ፣ ለእውነት ብለህ ዱንያን እጣ እንጅ ለዱንያ ብለህ መስለህ አለመኖር፣ ብቁ ከመሆንህ በፊት አስተማሪነትንና ደረጃን ተው።

ለዓሊም ማንዳለጥና ለዑለሞች የሃሳብ ልዩነት ያለህን አቋም አስተውል።

ወዳጅነትና ጠላትነት የምትመሰርትበት ቡድንተኝነትና ጎጠኝነት ሳይኖርብህ አወዛጋቢ ነጥቦችን አስወግድ፤

**<u>ለሸይኹ ያለው ሓቅ (መብት):</u>** ይህን ርእስ በማስመልከት ሁለት ጠርዘኞች እና አንድ መካከለኛ አቋም አለ፤ በምድር ላይ የተከሰተው የመጀመርያው ሽርክ ደጋግ ሰዎችን በማስመልከት ሰዎች ድንበር ማለፋቸው ነው። ደጋግ ሰዎችን በማስመልከት ድንበርም ሳይታለፍ ተገቢውንም ባለማስቀረት መካከለኛ አቋም ሊኖር ይገባል።

**ለሚማርበት ቦታ** ሓቅ(አለው)።

ለ**ቁርአት ጓደኞቹ** ያለው ሓቅ: ጥራት ይገባውና አላህ እንዲህ ይላል: {ለሰዎች ከተገለጸች ሕዝብ ሁሉ በላጬ ኾናችሁ…}(አሊ-ዒምራን 110) የአላህ መልዕክተኛም ﷺ "**አንዳችሁ ለራሱ የሚወደውን ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ አላመነም።**" ብለዋል።

**ለኪታቡ** ያለው ሓቅ: መፅሃፉን ተጠባብቆ ሊይዘው ይገባል፤ ምክንያቱም ጥራት ይገባውና አላህ እነኝህን ኪታቦች በመስጠቱ ፀጋውን ውሎልናልና ተጠባብቆ መያዙ የግድ ነው።

ለእውቀቱ ያለው ሓቅ: ሁልጊዜም ቢሆን አስረግጦ በመያዝና በክለሳ መጠባበቅ፣ በሱው መስራት፣ ምክንያቱም ያወቀ ሰው የመስራት ግዴታው አለበትና። ከዚህ በኋላ ወደዚህ እውቀት ጥሪ ያደርጋል፤ ምክንያቱም ፀጋ ነውና ይህንን ፀጋ ማመስገን ደሞ ግዴታ ነው።

(2) ከጥያቄ ስርአቶች መካከል የጎላ ጥቅምና ፋይዳ ይኖረዋል ተብሎ የሚታሰበውን ማስቀደም

(3) አንድ ተማሪ የራሱን ውበት መጠበቅ ይኖርበታል።

(4) ነብዩ ﷺ ከሞቱ በኋላ ግን "አላህና መልእክተኛው ይበልጡን ያውቃሉ" አይባልም።

**ሶስተኛው መሰረታዊ መርሆ:** ነብያችሁን ሙሓመድን ﷺ ማወቅ።

እሱም: **ሙሓመድ** ኢብኑ **ዓብዲላህ** ብኒ **ዓብዲል ሙጦሊብ** ብኒ **ሃሽም**፤ ሃሺም ከቁረይሽ ጎሳ ሲሆን ቁረይሽ ደሞ ከዓረብ፤ ዓረብም ደሞ ከኢስማዒል ኢብኒ ኢብራሂም አልኸሊል ዝርያ ነው። በሳቸውም በነብያችንም በላጭ የሆነው ሶለዋትና ሰላም ይስፈንባቸውና ዕድሜያቸው ስሳ ሶስት አመት ነበሩ። ከዚህም አርባውን ከነብይነታቸው በፊት ሃያ ሶስቱን የአላህ መልእክተኛና ነብይ ሆነው።

“ኢቅራእ” ሲወርድ ነብይ ሆነው “አል-ሙዘሚል” ሲወርድ ረሱልነትን አገኙ።

አገራቸው “መካ” ሲሆን ሂጅራ አድርገው ወደ “መዲና” የተሰደቱት።

ይህች አንቀፅ ስለነብዩ ﷺ ታሪክ አጠር ባለ መልኩ ትገልፃለች፤ ስማቸውን ዘራቸውንና ዕድሜያቸውን እንዲሁም ጥቂት ስለዳዕዋቸው ትዳስሳለች።

**ስለ ነብዩ ﷺ አንዳንድ ነገራቶችን ማወቅ ግድ ይለናል፤ ከነዚህም:**

**ስምና ዘራቸውን:** ስምና የዘር ግንዳቸውን: ሙሓመድ ኢብኑ ዓብዲላህ ብኒ ዓብዲል ሙጦሊብ ብኒ ሃሺም፤ ሃሺም ከቁረይሽ ጎሳ ሲሆን ቁረይሽ ደሞ ከዓረብ፤ ዓረብም ደሞ ከኢስማዒል ኢብኒ ኢብራሂም አልኸሊል ዝርያ ነው። በሳቸውም ሶለላሁ ዓለይሀም ወሰለም

**ዕድሜያቸውን:** ዕድሜያቸው ስሳ ሶስት አመት ነበሩ። ከዚህም አርባውን ከነብይነታቸው በፊት ሃያ ሶስቱን የአላህ መልእክተኛና ነብይ ሆነው።

**የመልእክተኝነት ቆይታቸው ወደ ሁለት ይከፈላል**

- የመካ ቆይታ: ለአስራ ሶስት አመታት የዘለቀች
- የመዲና ቆይታ: ለአስር አመታት የዘለቀች

እሳቸው ነብይ (ብቻ) ናቸው? ወይስ ረሱልም?

ነብይም ረሱልም ናቸው። ነብይ የሆኑት “ኢቅራእ” ሲወርድ ሲሆን መልእክተኝነትን ያገኙት ደሞ በሱረቱ ል ሙደሢር ነው።

## ከታሪካቸው ﷺ ቅንጭብ (በጨረፍታ)

በመካ ቆይታቸው የዳዕዋው ይዘት በተውሒድ ዙርያና ከሽርክ ርቆ አምልኮን ለአላህ ብቻ ጥርት ማድረግ ላይ ነበር። በዚህ ዳዕዋ ለአስራ ሶስት አመታት ቀጠሉ።

ከዚያም ወደመዲና ሂጅራ ማድረግን ታዘዙ። ዳዕዋው ግን ሌሎቹ የአምልኮ፣ የመስተጋብርና ሌላው የህይወት ዘርፍ ህግጋቶች ከመውረዳቸው አንፃር አሁንም በተውሒድ ላይ ነው የቀጠለው።

ይሁን እንጅ የነብዩን ﷺ የዳዕዋ ታሪክ ለተመለከተ ሰው የነብዩ ﷺ ወደ ተውሒድ ዳዕዋ ማድረግ እስከህልፈተ ህይወታቸው ድረስ እንደቀጠለ ነው። በዚህ ላይ ደሞ ሠዎችን ተውሒድን ከመማር ችላ በሚያስብሉና "ተውሒድን ለመማር የሆነ ያክል ደቂቃ በቂው ነው" ብለው በሚሞግቱ ሰዎች ላይ ግልፅና ጉልህ የሆነ አፀፋዊ ምላሽ (ረድ) አለበት።

አላህ ከሽርክ እንዲያስጠነቅቁና ወደ ተውሒድ ጥሪ እንዲያደርጉ ላካቸው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «{አንተ (ልብስህን) ደራቢው ሆይ! ۝ ተነሳ አስጠንቅቅም።۝ ጌታህንም አክብር۝ ልብስህንም አጥራ።۝ ጣዖትንም ራቅ።۝ ማብዛትንም የምትፈልግ ኾነህ፤ (በረከትን) አትለግስለለ።۝ለጌታህም (ትዕዛዝ) ታገሥ።(7)» (አል-ሙደሢር 1-7)

**(ተነሳ አስጠንቅቅም።)** ማለትም ከሽርክ ሊያስጠነቅቅና ወደ ተውሒድ ሊጣራ ማለት ነው። **(ጌታህንም አክብር።)** በተውሒድ አልቀው። **(ልብስህንም አጥራ።)** ስራህን ከሽርክ አፅዳው

**(ጣዖትንም ራቅ።)** ጣኦትን መራቁ ማለትም መተውና ከሽርኩም ከሽርክ ሰዎችም መጥራራት ማለት ነው። በዚህ መልኩ ወደ ተውሒድ ጥሪ እያደረጉ ለአስር አመታት ቆዩ። ከአስር አመት በኃላ ወደ ሰማይ አረጉ አምስት ሶላቶችም ተደነገጉ፤ ሶስት አመታትን መካ ላይ እንደሰገዱ ወደ መዲና ሂጅራ እንዲያደርጉ ታዘዙ።

"ወደ ሰማይ አረጉ" ከሚለው ንግግር (ጋ በተያያዘ) ተከታዮቹን ቁምነገሮች እናገኛለን

(1) ነብዩ ﷺ ስለሩቅ ሚስጥር በተናገሩበት አምነናል፣ እውነት ብለን ተቀብለናል እጃችንን ሰጥተናል እንላለን

(2) የአምስቱ ሶላቶች አሳሳቢነት፤ ምክንያቱም አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ የደነገጋቸው ሰማይ ላይ ነውና።

ሂጅራ ማለት ከሽርክ ሃገር ወደ ተውሒድ ሃገር መሰደት ማለት ነው። ከሽርክ አገር ወደ ተውሒድ ሃገር ሂጅራ ማድረግ በዚህ ኡማ ላይ ግዴታ ነው። እስከሰዓቲቱ መቆም ድረስም ቀጣይ ነች።

ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: «እነዚያ (ለእምነት ባለመሰደድ) ነፍሶቻቸውን በዳዮች ኾነው መላእክት (በበድር) የገደሉዋቸው (መላእክት ለነርሱ) «በምን ነገር ላይ ነበራችሁ» አሏቸው። «በምድር ውስጥ ደካሞች ነበርን» አሉ። «የአላህ ምድር ትሰደዱባት ዘንድ ሰፊ አልነበረችምን» አሉዋቸው። እነዚያም መኖሪያቸው ገሀነም ናት። በመመለሻነትም ከፋች!(97) ግን ከወንዶችና ከሴቶች ከሕፃኖችም ሲኾኑ (ለመውጣት) መላን የማይችሉና መንገድንም የማይምመሩ ደካሞች (ቅጣት የለባቸውም) (98) እነዚያም አላህ ከእነርሱ ይቅርታ ሊያደርግ ይሻል። አላህም ይቅር ባይ መሓሪ ነው።(99)» (አን-ኒሳእ 97-99).

እንዲሁም «እናንተ ያመናችሁ ባሮቼ ሆይ! ምድሬ በእርግጥ ሰፊ ናት፤ (ብትቸገሩ ተሰደዱ)። እኔንም ብቻ ተገዙኝ።» (አል-ዓንከቡት 29:56) አልበቐውይ አላህ ይዘንለትና እንዲህ ይላል: የዚች አንቀፅ መውረድ ምክንያት በመካ የነበሩ ሂጅራ ያልወጡ ሰዎች ነው። አላህም በኢማን ስያሜ ጠራቸው።

ለሂጅራ ከሓዲሥ ማስረጃው ተከታዩ የአላህ መልእክተኛ ﷺ ቃል ነው: **“ሂጅራ አትቋረጥም ተውባ እስክትቋረጥ ድረስ፤ ተውባም አትቋረጥም ፀሃይ በመግቢያዋ እስክትወጣ ድረስ።”** (አቡ ዳውድ)

**ሂጅራ ወደ ሶስት ይከፈላል:**

| | | |
|---|---|---|
| አላህ እንድንተዋ ግዴታ ያደረገውን ሁሉ ሂጅራ ማድረግ (መተው)፤ ስራም ይሁን ሰሪ ወይም ጊዜም ይሁን ቦታ። | ከመካ ወደ መዲና የሚደረግ ሂጅራ፤ ይህ በመካ መከፈት የተቋረጠ ነው። | ከኩፍር ሃገር ወደ ኢስላም አገር መሰደት ፤ ፍርዱ ግዴታ ነው። |

- ስራ: ጥራት ይገባውና አላህ የከለከለው ሁሉ፤ ከምንም በላይ ሽርክ። ሰሪ: ካፊርና ሙናፊቆች እንዲሁም ሌሎችም። ጊዜ: ካፊሮች በአል አድርገው የሚይዟቸው ጊዜያት። ቦታ: ካፊሮች በአል አድርገው የሚይዙባቸው ቦታዎች።

**ተውባ የሚቋረጠው ከሁለት በአንዱ ነው:**

(1) ፀሃይ በመግቢያዋ በመውጣቷ

(2) ወይም ሞት አፋፍ ላይ ሲኮን: {ጸጸትንም መቀበል ለእነዚያ ኀጢአቶችን ለሚሠሩ አንዳቸውንም ሞት በመጣበት ጊዜ «እኔ አሁን ተጸጸትኩ» ለሚልና ለነዚያም እነርሱ ከሓዲዎች ኾነው ለሚሞቱ አይደለችም። እነዚያ ለእነሱ አሳማሚን ቅጣት አዘጋጅተናል።}

**የነብዩ ﷺ “ከ(መካ) መከፈት በኃላ ሂጅራ የለም።”** ማለት ከመካ ወደ መዲና ለማለት ነው። እዚህጋ ከነብዩ ﷺ የሆነ ጥቆማ የሚሰጠን ነገር አለ: “መካ” ተመልሳ የኩፍር አገር እንደማትሆን ነው ።

መዲና ላይ በተረጋጉ ጊዜ በተቀሩት የዲነል ኢስላም ድንጋጌዎች ታዘዙ፤ እንደ ዘካ (1) ፣ ፆም፣ ሓጅ፣ ጅሀድ፣ አዛን፣ በመልካም ማዘዝ ከመጥፎ መከልከል፣ እና በሌሎችም የእስልምና ድንጋጌዎች ታዘዙ።

በዚህ መልኩ አስር አመት አሳለፉ፤ ከዛ በኋላ ህይወታቸው አለፈ የአላህ ሶለዋት እና ሰላም ይስፈንባቸውና። (2) ዲናቸው ቀሪ ሲሆን፤ ይህውና ዲናቸው። አንዳች ኸይር ነገር የለም ህዝባቸውን ያዘዙ ቢሆን እንጅ፤ ክፉ ነገርም የለም ከሷው ያስጠነቀቁ ቢሆን እንጅ። እሳቸው የጠቆሙት መልካም ነገር "ተውሒድ" እና አጠቃላይ አላህ የሚወደውና የሚያስደስተው ሁሉ። እሳቸው ያስጠነቀቁበት ክፉ ነገር ሽርክ እና አጠቃላይ አላህ የሚጠላውና የሚቃወመው ሁሉ። (3)

(1) ሸይኽ ኢብኑ ዑሠይሚንን አላህ ይዘንላቸውና የሚከተለውን ብለዋል "ዘካ መጀመርያ በመካ ነበር የተደነገገችው፤ ነገር ግን የኒሷቡ (የዘካ ግዴታ ማውጫ ዝቅተኛ ገደብ) መጠንም ሆነ የግዴታው ለከት አልተቀመጠለትም ነበር። መዲና ከገቡ በኋላ ግን ኒሷቡም ተቀመጠለት ግዴታውም ተገደበለት።"

(2) ነብዩ ﷺ ከሂጅራ በኋላ በአስረኛው አመት ሙተው በዓኢሻ (ረድየሏሁ ዓንሃ) ቤት ተቀበሩ።

(3) ምንም አይነት በጎ ነገር የለም ኡማውን ያመላከተ ቢሆን እንጅ፤ መጥፎ ነገርም የለም ከሱ ያስጠነቀቀ ቢሆን እንጅ። አደራውን መወጣታቸው፣ ተልዕኳቸውን ማድረሳቸው፣ ለኡማውን ተገቢውን ምክር ማስተላለፋቸው፣ በአላህም መንገድ ላይ ተገቢውን ትግል ማድረጋቸው፣ ጠፊ ካልሆን በማይሰሳትበት በነጣ ማስረጃ ላይ ትተውን (መሄዳቸው) መመስከር ግድ ነው።

**ከባባዶቹ ክልከላዎች**

- **ትልቁ ሽርክ**: ከ(እስልምና) መንገድ ያስወጣል
- **ትንሹ ሽርክ**: ከ(እስልምና) መንገድ አያስወጣም
- **ከባባድ ወንጀሎች**: ለየት ባለ መልኩ መቀጣጫ የመጣበት ሁሉ
- **ትናንሽ ወንጀሎች**: ለየት ባለ መልኩ መቀጣጫ ያልመጣበት ክልከላ ሁሉ

አላህ ለሰው ልጆች በመላ ላካቸው፤ በሁለቱ ከባባዶች የሰው ልጆችና አጋንንቶች ሁሉ ላይም መታዘዙን ግዴታ አደረገ።

ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው:- «እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ።}** (አል-አዕራፍ 158) (1)

አላህም ዲኑን በሱ አሟላ: ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{...ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ። ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ።...}**(አል-ማኢዳህ 3)(3)

ለመሞታቸው ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{አንተ ሟች ነህ፤ እነርሱም ሟቾች ናቸው።(30) ከዚያም እናንተ በትንሣኤ ቀን እጌታችሁ ዘንድ ትከራከራላችሁ።(31)}** (አዝ-ዙመር 30-31)

(1) ነብዩ ﷺ ወደሰው ልጆች በመላ ተላኩ። በዚህም ከሱ በፊት የነበሩት ህግጋት በሙሉ ተሻሩ። አይሁድም ይሁን ክርስትያን በነብዩ ﷺ ጊዜ ወይም ባለንበት ጊዜ (የእስልምና) ጥሪ ደርሷቸው ወደ ዲኑ ካልገቡ ካፊሮች ናቸው። የአላህ ሰላም ይስፈንባቸውና ሙሳና ዒሳ በነበሩበት አቋም ላይ እንኳ ቢሆኑ፤

(1) ማስረጃውም: **{የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ። (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣}** (አሊ-ዒምራን 64)

(2) እንዲሁም ተከታዩ ቃል: *{ከእነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና... ተዋጉዋቸው።}* (ተውባ 29)

(3) የአላህ መልእክተኛ ﷺ ቃል *“ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታየ እምላለሁ፤ አንድም አይሁዳዊ ወይም ክርስትያን ስለኔ አይሰማም ከዚያም በኔ ሳያምን አይቀርም የእሳት ሰው ቢሆን እንጅ።”*

**2.** ይህች አንቀፅ በካፊሮች ላይ “ረድ” አለባት።

# አምስተኛ: መደምደምያ

(1) ሰዎች ሁሉ ያለጥርጥር ሞትን ቀማሽ ናቸው። ለታላቁ ቀን ለትንሳኤ ቀንም ተቀስቃሾች ናቸው። የዚያኔ ይተሳሰባሉ ሁሉም እንደየስራቸው ይመነዳሉም።

(2) ከሞት በኃላ በመቀስቀስና (አላህ ፊት) በመተሳሰብ ያስተባበለ ክዷል ምክንያቱ ከኢማን ማእዘናት አንዱን አውግዟልና።

(3) ኑሕ ዓለይሂ ሰላም የመጀመርያውም መልእክተኛ ነው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ቃል ነው: **{እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነቢያት እንዳወረድን ወደ አንተም አወረድን።...}** (አን-ኒሳእ 163)

የነብያቶች መጀመርያ ደሞ አደም ነው። ማስረጃውም «ነብዩ ﷺ ስለ አደም ነብይነት ተጠይቀው **"አዎ አላህ ያናገረው ነብይ ነው አሉ።"** »

**የነብያቶችም የመልዕክተኞችም መጨረሻ ደሞ ሙሓመድ ﷺ ናቸው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ቃል ነው: {ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም። ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው።...}** (አል-አሕዛብ **40)**

ከነብዩ ﷺ በኃላ ነብይነትን ወይም መልዕክተኝነትን የሞገተ ውሸታምና ካፊር ነው። ሙግቱን የተቀበለውም እንደሱው ከሃዲ ነው።

የሰው ልጆች ከሞቱ በኃላ ይቀሰቀሳሉ፤ ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው። **{ከእርሷ (ከምድር) ፈጠርናችሁ። በእርሷም ውስጥ እንመልሳችኋለን። ከእርሷም በሌላ ጊዜ እናወጣችኋለን።}**(ጧሀ 55)

እንዲሁም **{አላህም ከምድር ማብቀልን አበቀላችሁ። (17) ከዚያም በውስጧ ይመልሳችኋል። ማውጣትንም ያወጣችኋል።}** (18)(ኑሕ 17-18)

ከመቀስቀስ በኃላ በስራቸው የሚተሳሰቡ እና የሚመነዱ ናቸው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{በሰማያት ያለውና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነው። እነዚያን ያጠፉትን በሠሩት ሊቀጣ እነዚያን ያሳመሩትንም በመልካሚቱ (ገነት) ሊመነዳ (የጠመመውንና የቀናውን ያውቃል)። }**(አን-ነጅም 31) (1)

ሞቶ በመቀስቀስ ያስተባበለ (በእስልምና)ክዷል። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{እነዚያ የካዱትን በፍጹም የማይቀሰቁ መኾናቸውን አሰቡ። «አይደለም በጌታዬ እምላለሁ። በእርግጥ ትቀሰቀሳላችሁ። ከዚያም በሠራችሁት ሁሉ ትነገራላችሁ። ይህም በአላህ ላይ ቀላል ነው።» በላቸው።}** (አት-ተጋቡን 7) (2)

አላህ መልእክተኞችን በሙሉ አብሳሪ እና አስጠንቃቂ አድርጎ ነው የላካቸው፤ ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{...አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የኾኑን መልክተኞች (ላክን)}** (አል-ኒሳእ 165)

የመጀመርያቸው ኑሕ ዓለይሂ ሰላም ሲሆን የመጨረሻቸው ሙሓመድ ﷺ ነው። የነብያት መደምደምያም እሱው ነው።

የመጀመርያቸው ኑሕ ዓለይሂ ሰላም ለመሆኑ ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነቢያት እንዳወረድን ወደ አንተም አወረድን።...}** (አን-ኒሳእ 163) (3)

በባርያዎች ሁሉ በጣኦት መካድንና በአላህ ማመንን ግዴታ አድርጎባቸዋል። ኢብኑል ቀይም አላህ ይዘንለትና እንዲህ ይላል: “ጧጉት” ማለት አንድ ባርያ በአምልኮትም ይሁን በመከተል አልያም በመታዘዝ በኩል ወሰኑን ያለፈበት ማለት ነው።
ለሁሉም ህዝብ ከኑሕ ጀምሮ እስከ ሙሓመድ ድረስ አንዱን አላህን ብቻ በማምለክ የሚያዘዛቸውና ጧጉትን ከማምለክ የሚከለክላቸው መልዕክተኛ ተልኳል።
ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ «አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ» በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል።…}** (አል-ነሕል 36)
ጧጉቶች ብዙ (አይነት) ናቸው። ዋና ዋናዎቹ ግን አምስት ናቸው። በአላህ የተረገመው ኢብሊስ፣ እየወደደ የተመለከ፣ ሰዎች እንዲያመልኩት ጥሪ ያደረገ፣ ከሩቅ ሚስጥር አንዳች ነገርን የሞገተ እና አላህ ካወረደው ውጭ በሆነ ህግ የፈረደ ናቸው።
ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{በሃይማኖት ማስገደድ የለም። ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ። በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው…ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ።…}** (አል-በቀራህ 256)
ይህ ነው የ ላኢላሀ ኢለሏህ ትርጉም። በሓዲሡም **“የጉዳዮች ራስ ኢስላም ነው፤ ምሰሶው ሶላት ነው፤ ሻኛው ደሞ በአላህ መንገድ መታገል ነው።”**

አላህ መልእክተኞችንና ነብያቶችን አብሳሪና አስጠንቃቂ አድርጎ ላካቸው። ሁላቸውም ደሞ ወደ ተውሒድ በሚደረግ ጥሪና ጧቑትና ሽርክን በየአይነቱ በመዋጋት በኩል አንድ ናቸው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: **{በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ… መልክተኛን በእርግጥ ልከናል።…}**(አል-ነሕል 36) በእያንዳንዱ ህዝብ ማለት ነው። **{ …اللَّهَ اعبُدُوا أَنِ} {«አላህን ተገዙ፤… በማለት}** ማለትም የአላህን አሃዳዊነት አፅኑ። **{وَاجتَنِبُوا الطّاغوتَ…}[النحل: ٣٦] {…ጣዖትንም ራቁ»}** ማለትም ጣኦታትን በአንድ በኩል አድርጋችሁ እናነተ በሌላኛው በኩል ሁኑ። ይህ በማስጠንቀቅና ከነሱ በማስራቅ በኩል ዲካ የደረሰ እና ከሽርክና ከሽርክ ሰዎች የመጥራራት ፅኑነት ነፀብራቅ ነው።
አላህ በመላ ባርያዎቹ ላይ በጧጉት መካድን እና በአላህ ማመንን ግዴታ አድርጓል። በአላህ ከማመን በፊት በጧጉት መካድ የግድ ነው። **«…በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው…»** (አልበቀራ 256)
**ጧጉት:** ሲባል አንድ ባርያ ወሰኑን የተላፈበት ማለት ነው። በማምለክ ሊሆን ይችላል (ድንጋይና ዛፍን ይመስል) ፣ በተከታይነት ሊሆን ይችላል (ክፉ ምሁራኖች መከተልን ይመስል) ፣ ወይም በመታዘዝም ሊሆን ይችላል (ከአላህ ትእዛዝ የሚያስወጣን ትእዛዝ መታዘዝን) ይመስል።

ጧጉቶች ብዙ (አይነት) ናቸው። ዋና ዋናዎቹ ግን አምስት ናቸው። በአላህ የተረገመው ኢብሊስ [ሸይኹ በመንገር መልክ እየረገሙት ነው] ኢብሊስ፣ እየወደደ የተመለከ፣ ሰዎች እንዲያመልኩት ጥሪ ያደረገ፣ ከሩቅ ሚስጥር አንዳች ነገርን የሞገተ እና አላህ ካወረደው ውጭ በሆነ ህግ የፈረደ ናቸው።

### አላህ ካወረደው ውጭ በሆነ ህግ መፍረድ ሲባል

**ትልቁ ኩፍር**

“የሰው ልጅ ህግ እንደአላህ ህግ ነው” ወይም “ከዛ በላይ ነው” ብሎ የሚያምን ከሆነ

**ትንሹ ኩፍር**

“አላህ ካወረደው ውጭ በሆነ ህግ መፍረድ ውዳቂ ነው” ብሎ እያመነ ነገር ግን በስሜቱ ተታሎ፣ ወይ በስልጣን ፍቅር፣ ወይም ከዚህ ውጭ በሆኑ (መሰል) ምክንያቶች ከሆነ ነው።

### ኢማም ኢብኑል ቀይም አላህ ይዘንላቸውና ጅሃድን ወደ አራት ይከፍሉታል

**ነፍስያን መታገል:**

በማወቅ፣ በመተግበር፣ ዳዕዋ (ጥሪ) በማድረግና በመታገስ የሚሆን ነው።

**ሸይጧንን መታገል:**

ውዥንብሮችን (ሽርክና ቢድዓ) እና ስሜታዊነትን (ትላልቁንም ትናንሹንም) በመተው።

**ካፊሮችንና ሙናፊቆችን መታገል:**

በልብ፣ በአንደበት፣ በገንዘብና በነፍስ የሚሆን ነው።

**የበደል፣ የቢድዓና የዉግዝ ነገራቶች ባላባቶችን መታገል**

በልብ፣ በአንደበት፣ በገንዘብና በነፍስ የሚሆን ነው።

***መደምደምያ***

አስተዋይ ሁሉ ይህንን ታላቅ ፅሁፍ እያንዳንዱ ሰው ቀብሩ ላይ ለሚያስፈልገው ከያዘው ትላልቅ መሰረቶች አንፃር ሊያገናዝበውና እጅግ በጣም ልዩ ትኩረት ሊቸረው ግዴታ ነው።

ይህን (ይመስላል)፣ የአላህ ሶለዋትና ሰላም በሳቸው በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በባልደረቦቻቸውም ላይ ይሁን

# ማጠቃለያ በሰንጠረዥ

<table>
<tr><td rowspan="9">ሶስቱ መሰረቶች (በአጭሩ የቀብር ጥያቄዎች) ና ማስረጃዎቻቸው፡ ለምን ተውሒድ እንማራለን? ለምን ሶስቱን መሰረቶች እንማራለን? ከመማራችን የምናገኘው ፋይዳ ምንድን ነው?</td><td rowspan="6">አራቱ ቁምነገሮችና ማስረጃቸው (ሱረቱል ዓስር)</td><td>እውቀት</td><td>ያም አላህን ማወቅ፣ ነብዩን ﷺ ማወቅና ዲነል ኢስላምን በማስረጃ ማወቅ ነው።<br>(ሶስቱን መሰረቶች)</td></tr>
<tr><td>በሱው መስራት</td><td>“እውቀት ተግባርን ጥሪ ያደርግለታል፤ ምላሽ ከሰጠው (ይቀጥላል) አለበለዚያ ግን ይተወዋል።”<br>እውቀት ኖሮት በእውቀቱ ያልሰራ<br>ከጣኦት አምላኪ በፊት አለለት ኪሳራ</td></tr>
<tr><td rowspan="2">ወደሱ ጥሪ ማድረግ</td><td>የዳዕዋ ቅድመ መስፈርቶች: የአላህን ፊት ብቻ መፈለግ፡ ሸሪዓዊ እውቀት መኖር፡ ዳዕዋ የሚደረግለትን ሰው ሁኔታ ማወቅ፡ ጥበብ መላበስ፡ እና ትእግስት።</td></tr>
<tr><td>አስቀድሞ ዳዕዋ የሚደረግበት ጉዳይ ተውሒድ ነው፡ የነብያቶችና የመልዕክተኞች ፈለግም ዪሀው ነው፡ ትልቁ የዳዕዋ እርከን ወደ ተውሒድ መጣራትና ሽርክን ማውገዝ ነው።</td></tr>
<tr><td rowspan="2">ለሚያጋጥም ጫና መታገስ</td><td>አላህን በመታዘዝ ላይ መታገስ፡ (ሶላትን ይመስል)፡ አላህን ከማመፅ (ወለድን ይመስል)፡ እንዲሁም በአላህ ቀደር ላይ (ድህነትን ይመስል)።</td></tr>
<tr><td>በ እውቀት ላይ መታገስ፡ ከዚያም በመልካም ስራ፡ ከዚያም በዳዕዋ ላይ</td></tr>
<tr><td rowspan="3">ሶስቱ ነጥቦች</td><td colspan="2">የጌትነት አሃዳዊነቱ (በጌትነቱ ብቸኛ የተደረገ የግድ በአምላክነቱም ብቸኛ ሊደረግ ይገባዋል)  እና በስምና ባህሪያት አሃዳዊነቱ</td></tr>
<tr><td colspan="2">የአምልኮ አሃዳዊነቱ(ኢኽላስ)፡ አላህ በአምልኮው ማንም እንዲጋራው አይፈልግም፡ ቅርብ መላኢካም ይሁን የተላከ ነብይ</td></tr>
<tr><td colspan="2">ከሽርክ እና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት; በልቦና (ካፊሮችን መጥላት)፡ በአንደበት (እኔ ከምትገዙት ሁሉ ንፁህ ነኝ)፡ እንዲሁም በተግባር (በበአላቶቻቸውና በስነስርአቶቻቸው ባለመሳተፍና እነሱን ባለመመሳሰል)</td></tr>
</table>

| | | |
|---|---|---|
| ሶስቱ መሰረቶች (በአጭሩ የቀብር ጥያቄዎች) ና ማስረጃዎቻቸው፡ ለምን ተውሒድ እንማራለን? ለምን ሶስቱን መሰረቶች እንማራለን? ከመማራችን የምናገኘው ፋይዳ ምንድን ነው? | ተውሒድን የመማር አስፈላጊነት | (ሓኒፊያህ)፡ ከሽርክ ያዘነበለችና በኢኽላስና በተውሒድ ላይ የተገነባች መንገድ |
| | | **ተውሒድ በቋንቋ ደረጃ፡** ስርወ ቃሉ ወሐደ፡ ዩወሒዱ ተውሒደን ከሚለው የመጣ ሲሆን ብቸኛ አደረገ እንደማለት ነው<br>**እንደሸሪዓ**፡ አላህን በሚነጠልባቸው ነገሮች በጌትነቱ በአምላክነቱ እና በስምና ባህሪያቱ ቢቸኛ ማድረግ ማለት ነው። ሶስት አይነት ነው፡ |
| | | 1. **ተውሒዱ ሩቡቢያ**፡ አላህን በድርጊቶቹ መነጠል፡ እንደመፍጠርና ንግስና እንዲሁም ማስተናበርን ይመስል።<br>2. **ተውሒዱል ኡሉሂያህ**፡ አላህን በአምልኮ መንጠል<br>3. **ተውሒዱል አስማኢ ወሲፋት**፡ አላህን ራሱን በኪታቡ ወይም በመልዕክተኛው ﷺ እንደበት በገለፀበትና በሰየመበት መልኩ ብቸኝነቱን ማፅደቅ ማለት ነው። ይህም ለራሱ ያፀደቀውን በማፅደቅና ከራሱ ያወገዘውን በማውገዝ ያላንዳች ማዛባትና ውድቅ ሳያደርጉ እንዲሁም ያላንዳች ሁኔታ መግለፅ ውስጥ መግባትና ያለማመሳሰል ነው። |
| | | ሽርክ ማለት ከአላህ ጋ ሌላን አካል መጣራት ማለት ሲሆን ምድር ላይ ከሚፈፀሙ ወንጀሎች ከባዱ ነው። |
| | ሶስቱ መሰረቶች | ጥራት ይገባውና አላህን ማወቅ፡ ሲባል ጌታህ ማን ነው? ጌታህን በምን አወቅከው? ጌታ ተመላኪው ነው። የአምልኮ አይነቶች፡ ከአምልኮ አይነቶች አንዳች ነገርን ለሌላ አካል አሳልፎ የሰጠ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው? ከማስረጃ ጋ |
| | | ዲነል ኢስላምን በማስረጃ ማወቅ፡ ሲባል የኢስላም ፍች፡ የዲን እርከኖች፡ የኢስላም ማእዘናት፡ የምስክርነት ቃል(የሸሃዳ) ፍች፡ የኢማን ማእዘኖች እና ቅርንጫፎቹ፡ ኢሕሳን፡ የዲን እርከኖች ማስረጃቸው እንዲሁም የመጨረሻው ቀን ምልክቶች |
| | | መልዕክተኛውን ﷺ ማወቅ፡ ሲባል የዘር ግንዳቸውን፣ የተወለዱበትን ማወቅ፣ ዕድሜያቸውን፣ ነብይና መልዕክተኝነታቸውን፣ አገራቸውን፣ የመላካቸው ጥበብ፣ ለተውሒድ ዳዕዋ ያሳለፉትን ጊዜ፣ ኢስራእ እና ሜዕራጅ፣ ሶላት መቸ የት ተደነገገች? ሂጅራ ማድረግ ፍርዱና ጊዜው፣ ሌላው ዲንጋጌ መች ግዴታ ሆነ? የዳዕዋ ቆይታቸው፣ ህልፈታቸው፣ ይዘውት የመጡት ዲን፣ በጥቅሉ ለሁለቱም ከባባዶች(ሰውና አጋንንት) መላካቸው፣ የዲኑ ሙሉነትና የፀጋ መሟላት ማወቅ ነው። |

**ሶስቱ መሰረቶች (በአጭሩ የቀብር ጥያቄዎች) ና ማስረጃዎቻቸው፡ ለምን ተውሒድ እንማራለን? ለምን ሶስቱን መሰረቶች እንማራለን? ከመማራችን የምናገኘው ፋይዳ ምንድን ነው?**

**ማጠቃለያ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ከሞት በኋላ መቀስቀስና ስራን መተሳሰብ፡ ሞቶ በመቀሰቀስ የሚያስተባብል ከሃዲ መሆኑ፡ የመልዕክተኞች ሃላፊነትና ዳዕዋቸው፡ የመልዕክተኞች መጀመሪያና መደምደሚያ፡ ሁለቱ የተውሒድ ማእዘናትበጧጉት መካድና በአላህ ማመን፡ የጧጊት ፍች፡ የጧጊት ራስ የሚባሉት፡ በጧጊት የመካድ ሁኔታው፡ የላኢላሃ ኢለሏህ ትርጉም፡ ኢስላም የዲኑ የበላይ መሆኑ፡ የዲን ምሰሶ ሶላት፡ የዲኑ ሻኛ ጅሃድ ላይ መሆኑ። | | | |
| **የመፋለም አይነቶች** | **ነፍስያን መታገል** | ሱረቱል ዓስር ላይ በተጠቀሰው መልኩ መታገል (ማወቅ፣ (ባወቁት) መስራት፣ ወደሱው መጥራት፣ መታገስ) | |
| | **ሸይጧንን መታገል** | **ስሜት** | ከባባድ ወንጀሎች (ልዩ መቀጣጫ የመጣባቸው ሁሉ) |
| | | | ትናንሽ ወንጀሎች (ልዩ መቀጣጫ ያልመጣበት ዉጉዝ ነገር ሁሉ) |
| | | **ውዥንብሮች** | ትልቁ ሽርክ (ከእስልምና ያስወጣል) እና ትንሹ ሽርክ |
| | | | ቢዳዓዎች(መጤዎች) |
| | **ካፊሮችን እና ሙናፊቆችን መታገል** | በልቦና፣ በአንደበት፣ በአካልና በገንዘብ የሚሆን ነው | |
| | **የበደል፡ የቢዳዓ እና የተወገዙ ነገራቶች ባላባቶችን መታገል** | በእጅ፣ በአንደበትና በልቦና የሚሆን ነው | |
| **ጧጉት** | ጧቁት: ሲባል አንድ ባርያ ወሰኑን የተላፈበት ማለት ነው። በማምለክ ሊሆን ይችላል (ድንጋይና ዛፍን ይመስል)፣ በተከታይነት ሊሆን ይችላል (ክፉ ምሁራኖች መከተልን ይመስል)፣ ወይም በመታዘዝም ሊሆን ይችላል (ከአላህ ትእዛዝ የሚያስወጣን ትእዛዝ መታዘዝን ይመስል)። | | |

ጧቄቶች ብዙ (አይነት) ናቸው። ዋና ዋናዎቹ ግን አምስት ናቸው። የአላህ እርግማን ይስፈንበትና [ከመንገር አንፃር እየረገሙት ነው]ኢብሊስ፣ እየወደደ የተመለከ፣ ሰዎች እንዲያመልኩት ጥሪ ያደረገ፣ ከሩቅ ሚስጥር አንዳች ነገርን የሞገተ እና አላህ ካወረደው ውጭ በሆነ ህግ የፈረደ ናቸው።

አላሁ አዕለም የአላህ ሶለዋትና ሰላም በሳቸው በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በባልደረቦቻቸውም ላይ ይሁን

# የሶስቱ መሰረቶችና ማስረጃቸው ፈተና

በቅንፉ ወስጥ ካሉት ትክክለኛውን መልስ ምረጥ

(1) የኡሱሉ ሠላሣ / ሶስቱ መሰረቶች ኪታብ ፀሃፊ ስም (ሙሓመደ ቢን ሱለይማን አትተሚሚይ~ሙሓመድ ቢን ዓብዱልወሃብ~የተጠቀሱት ሁሉ)።

(2) ሶስቱ መሰረቶች አጠር ባለ አገላለፅ የቀብር ጥያቄዎች ማለት ነው? (እውነት – ሃሰት).

(3) ሸይኹ ብኡሱሉ ሠላሣ ውስጥ ለሚቀራው ሰው ዱዓ ያደረጉለት (በሁለት ቦታ – በሶስት ቦታ).

(4) የሸይኹ ኪታቦች የሚለዩት (በቀላልነታቸው – ጥቅል በሆነ መልኩ ካስቀመጡ በኋላ ዝርዝር ዉስጥ የሚገቡ በመሆናቸው - ማስረጃቸው ከቁርአን እና ከሓዲሥ በመሆኑ – ለተማሪ በሚያደርጉት ዱዓ – ወቅታዊ ውዥንብሮች ላይ በሚሰጡት ረድ- በትንታኔዎቹ ብዛት – አንገብጋቢ ጥያቄዎችን እያነሱ በሚሰጡት ምላሽ – አላህ በለገሳት ተቀባይነት – ሁሉም).

(5) “አል ኡሱሉ ሠላሣ” ሶስቱ መሰረቶች የሚለውን ኪታብ ወደ 5 ና 6 ምዕራፍ ከፋፍለን ማየት እንችላለን። (እውነት – ሃሰት)

(6) ተውሒድን መማር (ግለሰባዊ ግዴታ/ፈርዱ ዓይን – ማህበራዊ ግዴታ/ፈርዱ ኪፋያ)።

(7) የአራቱ ቁምነገሮች ማስረጃ (ሱረቱል ዓስር – ሱረቱል ኢኽላስ).

(8) አውቆ የማይሰራበት ተመሳሳይነቱ (ከክርስቲያኖች ጋ – ከአይሁዶች ጋ – ሁሉም መልስ ነው).

(9) ትእግስት ወደ (ሁለት – ሶስት) ይከፈላል

(10) ሱረቱል ዓስርን በማስመልከት የኢማም ሻፊዒይ ንግግር መልዕክት: (“ሑጃ” ለማቆም/ ለማስረጃነት በቂ ነች– ከሌሎቹ ሱራዎች ታብቃቃለች)።

(11) ከተውሒድ ክፍሎች አንዱን ብቻ የያዘ ተውሒድን ይዟል ሊባል አይችልም (እውነት – ሃሰት)

(12) ከሽርክና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት የሚሆነው በ (ልቦና፣ በአንደበትና በተግባር – ከስራውና ከሰሪው በመጥራራት – ሁሉም መልስ ነው)

(13) "እነሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው" በአንቀፁ መሰረት “መስጊዶች” በማለት የተፈለገበት (የተገነቡ መስጅዶች – የሱጁድ አካላት – ሱጁድ የሚደረግባቸው ቦታዎች - ሁሉም)

(14) የሰለፎች አካሄድ የሆነው: (ማስረጃን ካስደገፉ በኋላ ማመን – ካመኑ በኋላ ማስረጃን መፈለግ)

(15) ከሙስሊም ዑለሞች ሆኖ የጠመመ ተመሳሳይነቱ ከ (አይሁዶች ጋ – ክርስቲያኖች ጋ).

(16) ከሙስሊም ዓቢዶች መካከል ሆኖ የጠመመ ተመሳሳይነቱ (ከአይሁዶች ጋ – ከክርስቲያኖች ጋ)

(17) ሶስቱ ቁምነገሮች የተባሉት ሶስቱን መሰረቶች ነው (እውነት – ሃሰት).

(18) የዱዓ አይነቶች (የአምልኮ ዱዓና የልመና ዱዓ ፤ የቀጥታ ዱዓ እና ዱዓ በተዘዋዋሪ)

(19) የልመና ዱዓ አይነቶች (ሁለት – አራት)

(20) ሰዎች ሰበብን በማስመልከት አይነታቸው (ሁለት ፅንፈኞችና አንድ ሚዛናዊ – ትልቁ ሽርክ፣ ትንሹ ሽርክና የሚፈቀድ)

(21) ፍጡራንን በጭንቅ ድረሱልኝ ማለት የሚቻለው (በልቁ ያለገደብ – በሚችሉት - ከአራቱ ቅድመ ሁኔታዎች አንፃር የሚችል ከሆነ)

(22) የ "ላኢላሃ ኢለሏህ" ትርጉም (አላህ ከተለምዶ መውጣት የሚችል መሆኑ – ከአላህ ውጭ የሚመለክ የለም - ከአላህ ውጭ በእውነት የሚመለክ የለም – ሁሉም መልስ ነው)

(23) በሃይማኖቶች ማስማማት ማለት (ይፈቀዳል – ከባድ ወንጀል – ክህደት)

(24) ስለ አላህ ህልውና ማስረጃዎች በጥቅሉ (ብዙ ናቸው – አራት ናቸው)

(25) መላኢኮች ልበና አላቸውን? (አዎ – አይ)

(26) በኢማንና በተውሒድ መካከል ያለው ቁርኝት: ኢማን ጥቅል ሲሆን ተውሒድ የሱ ክፋይ ነው (እውነት – ሃሰት)

(27) የኢማን ማእዘናት (5, 6, 8)

(28) ሙሽሪኮች የሆነ ያክል አላህን ያመልካሉ (እውነት – ሃሰት)

(29) ከአላህ ዉጭ ሳይወድ የተመለከ(ጧጉት – ጧጉት አይደለም)

(30) በማስተናበርና ዝናብ በመልቀቅ አላህን መነጠል ተውሒዱል… (ኡሉሂያ/አምልኳዊ – ሩቡቢያ/የጌትነት – አስማኢ ወሲፋት/ስምና ባህሪያት).

(31) የተውሒድን መሰረት ከሚንዱ መካከል (ትልቁ ሽርክ - ትንሹ ሽርክ – ቢድዓ)

(32) የግዴታዎች ሁሉ ግዴታ ለወላጆች መልካም መዋል ነው። (እውነት – ሃሰት)

(33) ከሓራም ነገራቶች ሁሉ የከፋው ዝሙትና አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ መግደል ነው (እውነት – ሃሰት)

(34) ሚዕራጅ ማለት ነበዩ ሶለሏሁ ዓለይሂ ውሰለም ከመካ ወደ በይተል መቅዲስ ያደረጉት ጉዞ ነው (እውነት – ሃሰት)

(35) ነብዩ ﷺ የተላኩት (ውደ ህዝባቸው ብቻ – ወደ ሰው ልጆችና አጋንንቶች)

(36) ነብዩ ﷺ (ሙተዋል – ነብያቶች አይሞቱም)

(37) ሞቶ በመቀስቀስ ያስተባበለ ሰው ክህደቱ (ትልቁን ክህደት – ትንሹን ክህደት)

(38) የነብያቶች ዲን (አንድ ነው – ለእያንዳንዱ ነብይ ዲን አለው)

(39) ሂጅራ(ስደት ማድረግ) (ከመካ መከፈት በኋላ ተቋርጧል – እስከመጨረሻው ቀን ድረስ ይቀጥላል)

(40) ሂጅራ ማለት (ከኩፍር አገር ወደተውሒድ አገር መሰደት ነው – አላህ ሓራም ያደረገውን መተው ነው)

(41) ዲነል ኢስላም ተሟልቷል ከደጋጎች ህልም በሚመጣ ካልሆነ በቀር (እውነት – ሃሰት)

(42) አምልኮን ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ መስጠት ሽርክነቱ (ትልቁ – ትንሹ)

(43) በድርጊቱ ላይ ፍርድ መስጠትና በድርጊቱ ፈፃሚ ላይ ፍርድ መስጠት ልዩነት የለውም (እውነት –ሃሰት)

(44) የነብያቶች መጀመሪያ (ኑሕ ዓለይሂ ሰላም– አደም ዓለይሂ ሰላም)

(45) ነብያችን ﷺ (ነብይ ናቸው - መልዕክተኛ ናቸው)

## በ ‘ሀ’ ረድፍ ላሉት በ’ለ’ ረድፍ ካሉት የሚዛመዳቸውን ፈልግ

| ረድፍ ‘ሀ’ | መልስ | ተራ ቁጥር | ረድፍ ’ለ’ |
|---|---|---|---|
| ተውሒድ በቋንቋ ደረጃ | | 1 | የኢማም አሕመድ “ካፊርን ባየሁ ጊዜ የአላህን ጠላት ላለማየት ብየ አይኖቸን እጨፍናለሁ።” |
| ተውሒድ በሸሪዓ ደረጃ | | 2 | ከሞት በኋላ በሚሆነው ሁሉ ማምንን ያካትታል |
| ተውሒዱል ኡሉሂያ (የአምልኮ አሃዳዊነቱ) | | 3 | በአንደበት የሚባል ቃል፣ በልብ አምኖ በልብም በአካልም መስራት፣ በታዛዥነት ይጨምራል በማመፅ ይቀንሳል |
| ተውሒዱ ሩቡቢያ (የጌትነት አሃዳዊነቱ) | | 4 | ኢስላም፣ ኢማንና ኢሕሳን |
| ተውሒዱል አስማኢ ወሲፋት (የስምና ባህሪያቱ አሃዳዊነት) | | 5 | ለአላህም ከአላህ ዉጭ ላለ አካልም |
| ሓኒፊያ | | 6 | ግዴታ የሆነ፣ የሚፈቀድና የተከለከለ |
| በቁርአን ላይ የመጀመሪያው ትእዛዝና ጥሪ | | 7 | ሸሪዓዊና ተጨባጩ |
| ብጤ | | 8 | የቀብር ጥያቄዎች |
| ኸሸየህ | | 9 | ማወቅ፣ መተግበር፣ መጣራትና መታገስ |
| ተወኩል | | 10 | የአላህን ፊት ብቻ መፈለግና ሱናን መግጠሙ |
| አምልኮ ተቀባይነት ያገኝ ዘንድ መሟላት ያለባቸው ሁለቱ ቅድመ መስፈርቶች | | 11 | ሰበቦችን እያደረሱ በአላህ ላይ ተማምኖ እሱ ላይ እውነተኛ መደገፍ ማለት ነው |
| የአራቱ ቁምነገሮች በአጭሩ | | 12 | የሚፈራውን አካል ታላቅነትና ልዕለ ሃያልነት በማስመልከት እውቀት ላይ ተመርኩዞ መፍራት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሶስቱ ነጥቦች በአጭሩ | | 13 | አምሳያ፣ እኩያ፣ ምሳሌ |
| ሶስቱ መሰረቶች በአጭሩ | | 14 | ሱረቱል በቀራህ |
| የሰበብ አይነቶች | | 15 | ከሽርክ ያዘነበለችና በኢኽላስና በተውሒድ ላይ የተገነባች መንገድ |
| የስለት አይነቶች | | 16 | አላህን ራሱን በኪታቡ ወይም በመልዕክተኛው ﷺ አንደበት በገለፀበትና በሰየመበት መልኩ ብቸኝነቱን ማፅደቅ ማለት ነው። ይህም ለራሱ ያፀደቀውን በማፅደቅና ከራሱ ያወገዘውን በማውገዝ ያላንዳች ማዛባትና ውድቅ ማድረግ እንዲሁም ያላንዳች ሁኔታ መግለፅ ውስጥ መግባትና ያለማመሳሰል ነው። |
| የእርድ አይነቶች | | 17 | አላህን በአምልኮ መነጠል |
| የኸውፍ አይነቶች | | 18 | አላህን በመፍጠር፣ በንግስናውና በአስተናባሪነቱ መነጠል |
| ኢስላም | | 19 | አላህን በሚነጠልበት ብቸኛ ማድረግ ማለት ነው |
| የዲን እርከኖች | | 20 | ስርወ ቃሉ ‘ወሐደ’ የሚል ሲሆን መነጠል ማለት ነው |
| ኢማን | | 21 | ፀሃይ በመግቢያዋ መውጣቷና ሞት አፋፍ ላይ መሆን |
| በመጨረሻው ቀን ማመን የሚያካተው | | 22 | ሲባል አንድ ባርያ ወሰኑን ያለፈበት ማለት ነው። በማምለክ ወይም በተከታይነት አልያም በመታዘዝ ሊሆን ይችላል |
| ከሽርክ ሰዎች መጥራራት ፅኑነት አንፃር | | 23 | ተውሒዱ ሩቡቢያ እና ተውሂዱል አስማኢ ወሲፋት፣ ተውሒዱል ኡሉሂያ እንዲሁም ከሽርክና ክሽርክ ሰዎች መጥራራት |
| ተውባ የሚቋረጥበት ገዜ | | 24 | ራስን ለአላህ በተውሒድ ማስገዛት፣ በታዛዥነት ለሱ መጎትተ ከሽርክና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት |
| ጧጉት | | 25 | ቅርፅ ኖሮት ከአላህ ውጭ የተመለከ |

# አራቱ መርሆዎች

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩኅ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው**

ምስጋና ባጠቃላይ ለአላህ ይገባው፤ እናመሰግነዋለን፣ እገዛውን እንጠይቀዋለን፣ መሃርታውን እንለምነዋለን፣ ከነፍሳችን ክፋትና ከክፉ ስራዎቻችን በአላህ እንጠበቃለን፤ አላህ የመራውን የሚያጠም የለውም፤ ያጠመመውንም የሚመራ የለውም፤ ከአላህ ውጭ (በእውነት) የሚመለክ እንደሌለ ብቸኛና ተጋሪ የሌለው መሆኑንና ሙሓመድም ﷺ ባርያውና መልዕክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ። በመቀጠል፡

# የትንታኔው መግቢያ

## የዚህ ፅሁፍ ደራሲ

ሸይኹል ኢስላም፤ የተውሒድ ጥሪ የተሃድሶ መሪ(ሙጀዲድ)፤ ኢማም ሙሓመድ ቢን

ዓብዱል ወሃብ ቢን ሱለይማን አት-ተሚሚይ፤ በቅፅል ስማቸው አቡ-ል-ሑሰይን (ይባላሉ)።

በውየይና መንደር በ1115 ዓ. ሒ. ተወልደው በ1206 ዓ. ሒ. ሞቱ።

**«አራቱ መርሆዎች» ከተከታታይ የተማሪዎች ትምህርት ሁለተኛዋ ነች፤ ይህ ፅሁፍ ትኩረት የተቸረበት በርከት ያሉ ምክንያቶች አሉት: ከነሱም:**

- ዑለሞች እንድንማረው በመምከራቸው
- በደጋግ ቀደምት አበው (ሰለፍ) ዑለሞች ከመመራት አንፃር
- በወቅታዊ ሙሽሪኮች ውዥንብር ላይ መልስ ስላለበት
- የከሽፉ-ሽ-ሹቡሃት አጭር ጭብጥ ከመሆኑ አንፃር
- ከሽፉ-ሽ-ሹቡሃትን ከማስተማራችን በፊት ተማሪው ላይ ውዥንብር እንዳይቀርበት በዚህ እንጀምራለን

## የአራቱ መርሆዎች ማውጫ

ይህ ፅሁፍ ወደ ሶስት ይከፈላል፤ እነሱም:

- (1) መግቢያ (የስኬት ርእስ)
- (2) ተውሒድን የመማር አንገብጋቢነት
- (3) መርሆዎቹ

መጀመርያ: መግቢያ (የስኬት ርእሶች)

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩኅ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው (1)**
**ቸሩ አላህን የታላቁ ዓርሽ ጌታን በዱንያም በአኼራም ይወዳጅህ ዘንድ (2) የትም ብትሆን የተባረክ ያደርግህ ዘንድ እለምነዋለሁ።** (3)

(1) ሸይኹ ፅሁፉ በቢስሚላህ የጀመሩበት ምክንያት

{1} በአላህ መፅሃፍና በነብያቶች (ዓለይሂሙ ሰላም) ከመመራት አንፃር

{2} ከሱ በፊት ፅሁፎቻቸውን በቢስሚላህ መጀመር ልምዳቸው በነበሩ ቀደምትና ዑለሞች ከመከተል አንፃር

{3} በተከበረው የአላህ ስም በረካን ከመሻት አንፃር

ሸይኹል ኢስላም ኢብኑ ተይሚያ አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ይላሉ “አላህን የሚፈራ ሙእሚን (ሁሉ) የአላህ ወዳጅ (ወልይ) ነው።” ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: { ﴿أَلا إِنَّ أَولِياءَ اللَّهِ لا خَوفٌ عَلَيهِم وَلا هُم يَحزَنونَ۝الَّذينَ آمَنوا وَكانوا يَتَّقونَ﴾[يونس: ٦٢-٦٣]} {ንቁ! የአላህ ወዳጆች በእነሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነሱም አያዝኑም።(62) (እነሱም) እነዚያ ያመኑትና ይፈሩት የነበሩ ናቸው።}(ዩኑስ 62-63)

በረካ: መፋፋትና መጨመር ማለት ነው

ተበሩክ: መፋፋትንና መጨመርን መፈለግ

ሙባረክ: የትም ሆኖ በዛው(በበረካው) የሚጠቀም

ተበሩክ ለሁለት ይከፈላል

የተደነገገ ተበሩክ:

- ተጨባጭ: እውቀትና ዱዓን የመሰሉ፤ አንድ ሰው በእውቀቱ በረካ ሊገኝ ይችላል፣ ወደ መልካም ነገር በሚያደርገው ጥሪ ሊሆን ይችላል። የዚህኔ በረካ ይሆናል። ምክንያቱም ብዙ መልካም ነገርን አግኝተንበታልና። እንደሸይኹል ኢስላም ኪታብና መሰል አላህ በረካንና ኸይርን በኪታቦቻቸው ላይ ያሰፈነባቸው እንዲሁም ኡማው የተጠቀመባቸው ዑለሞች።
- ሸሪዓዊ: በመስጅደል ሓራም ወይም በመስጅደ ነበውይ መስገድን ይመስል

የተከለከለ ተበሩክ: በተጨባጭም ይሁን በሸሪዓው ያልፀና ሲሆን ከትንሹ ሽርክ አይነቶች የሚመደብ ነው።

**...ሲሰጡ ከሚያመሰግኑ ያደርግህ ዘንድ...** (1)

(1) ፀጋም ፈተና ነው፤ በርካታ ማስረጃ ያለው ሲሆን ከነዚህም: { ﴿...وَنَبلوكُم بِالشَّرِّ وَالخَيرِ فِتنَةً وَإِلَينا تُرجَعونَ﴾[الأنبياء: ٣٥]} {...ለመፈተንም በክፉም በበጎም እንሞክራችኋለን። ወደኛም ትመለሳላችሁ።}(አል-አንቢያእ 35) { ﴿...فَلَمّا رَآهُ مُستَقِرًّا عِندَهُ قالَ هذا مِن فَضلِ رَبّي لِيَبلُوَني أَأَشكُرُ أَم أَكفُرُ وَمَن شَكَرَ فَإِنَّما يَشكُرُ لِنَفسِهِ وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ رَبّي غَنِيٌّ كَريمٌ﴾[النمل: ٤٠]} {...እርሱ ዘንድ ረግቶ ባየውም ጊዜ «ይህ ከጌታዬ ችሮታ ነው። የማመሰግን ወይም የምክድ መኾኔንሊሞክረኝ (ቸረልኝ)። ያመሰገነም ሰው የሚያመሰግነው ለራሱ ነው። የካደም ሰው ጌታዬ ከእርሱ ተብቃቂ ቸር ነው» አለ።}(አል-ነምል 40) { ﴿فَأَمَّا الإِنسانُ إِذا مَا ابتَلاهُ رَبُّهُ فَأَكرَمَهُ وَنَعَّمَهُ فَيَقولُ رَبّي أَكرَمَنِ﴾[الفجر: ١٥]} {ሰውማ ጌታው በሞከረው ጊዜ፣ ባከበረውና ባጣቀመውም (ጊዜ) «ጌታዬ አከበረኝ (አበለጠኝ)» ይላል።}(አል-ፈጅር 15)

በሓዲሥም: «ከበኒ እስራኢሎች የሆኑ ሶስት ሰዎችን አላህ ሊፈትናቸው…»
ፀጋ ከተውሒደል ሩቡቢያና ከተውሒደል ኡሉሂያ ጋ የተቆራኘ ሲሆን ሹክርም ደሞ ሁለት አይነት ነው:
ከፀጋ በፊት ከአላህ ጋ ተሳሰር

- ይህ አይነቱ ከባርያ ፀጋን የሚለግሰው አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ መሆኑን ቁርጥ ያለ እምነት ይጠይቃል። ልቦናው ከአላህ ውጭ ባለ አካል አይንጠለጠልም፤ ኸይርንም ከሱ ቢሆን እንጅ አይከጅልም።

ባለቤቱ እሱ በመሆኑ ጀነት የምትፈለገው ከሱ እንደሆነው ሁሉ ሲሳይም ከአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ እንጅ ሊፈለግ አይገባውም።
{﴿وَتَوَكَّل عَلَى الحَيِّ الَّذي لا يَموتُ...﴾ [الفرقان: ٥٨]} {በዚያም በማይሞተው ሕያው አምላክ ላይ ተመካ።…} (አል-ፉርቃን 58)
{﴿...إِنَّ الَّذينَ تَعبُدونَ مِن دونِ اللَّهِ لا يَملِكونَ لَكُم رِزقًا فَابتَغوا عِندَ اللَّهِ الرِّزقَ...﴾ [العنكبوت: ١٧]}
{…እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትግገዙዋቸው ለእናንተ ሲሳይን ሊሰጧችሁ አይችሉም። …} (አል-ዓንከቡት 17) ማለትም ሲሳይ ከሌላ ሳይሆን ከሱ (ፈልጉ) {﴿...وَاعبُدوهُ وَاشكُروا لَهُ إِلَيهِ تُرجَعونَ...﴾ [العنكبوت: ١٧]} {…ስለዚህ ሲሳይን ከአላህ ዘንድ ብቻ ፈልጉ፡ ፡…} (አል-ዓንከቡት 17)
ፀጋው ከተከሰተ በኃላ ሹክር (ማድረግ) ይህም:

- በልቦና: ሲሳይ ለጋሹ ባለውለታ አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ መሆኑን እውነተኛ በሆነ እምነትና ሙሉ በሆነ መማረክ ነው። በአንድ ባርያ ላይ ያለው ፀጋ ሁሉ ከአሏሁ ሱብሓነሁ ወተዓላ መሆኑን አምኖ መቀበል።
- በአንደበት: የአላህን ፀጋ በማመስገንና ስለፀጋው በማውራት፣ በማወደስ ነው። አላህ በቁርአኑ የሚከተለውን ስላለ: {﴿وَأَمّا بِنِعمَةِ رَبِّكَ فَحَدِّث﴾ [الضحى: ١١]} {በጌታህም ጸጋ አውራ፤ (ግለጻት)።} (አል-ዱሓ 11)
- በአካል: ፀጋውን አላህ ሱብሓነሁ ወተዓላን በሚያስደስተው ላይ ማዋል። ወደሱ ከመቅረብ አንፃር ታዛዥነትን አስታኮ እና ትእዛዙን በመከተል አመፁን ርቆ ማለት ነው።

**… ሲፈተን ታጋሽ…** (1)

ትእግስት በመላ ህዝብ መሰረት ግዴታ ስለሆነ ነው።
ሰዎች ዱንያ ላይ መከራ ሲያጋጥማቸው (ከሚያስተናግዱበት አንፃር) ለአራት ይከፈላሉ፤ እነሱም
ብስጩ
ታጋሽ
ደስተኛ
አመስጋኝ

(1) ብስጭት: ሓራም ነው፤ ከትላልቅ ወንጀሎች አንዱ ነው። እንዲሁም
በልቦና
በአንደበትና
በአካል የሚገለፅ ነው።
በልቦና መበሳጨት: ኢብኑል ቀይም አልጀውዝያህ አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ይላሉ[መልእክቱ]: “…አንዳንድ ጊዜ ሰው በአንደበቱ የማይለው ጉዳይ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን እሱ ዘንድ ያለችው ነፍሱ ግን ጌታውን በማስመልከት ያለውን መጥፎ ጥርጣሬ ታጋልጥበታለች። በውስጡ ‘ጌታየ በድሎኛል!’ ‘ጌታየ ከልክሎኝ ነው!’ ‘ጌታየ ነው ያቀበኝ!’ ይብዛም ይነስም ሌላም ሌላም ይላል።” ነፍስህን ፈትሻት ከዚህ ነፃ ነህ? ከሷ ከዳንክ በርግጥም ከከባድ ተርፈሃል።
በአንደበት መበሳጨት: ይህ በጩሀት፣ በሙሾ፣ ‘ወይኔ’ ወይም ‘ወዮው!’ በማለት፣ በመራገም፣ በመሳደብ የሚገለፅ ነው።
መበሳጨት በአካል: ደረትን በመደለቅ፣ አንገትያ (ልብስን) በመቅደድ፤ ፀጉርን በመንጨት የሚገለፅ ነው።
(2) ትእግስት: ፍርዱ በመላ ህዝብ ስምምነት መሰረት ግዴታ ነው። በልቦና፣ በአንደበቱና በአካሉ ትእግስትን መላበስ ግዴታው ነው። ኢማም አሕመድ እንዲህ ይላሉ “ትእግስት በቁርአን ወደ ዘጠና ጊዜ አካባቢ መጥቷል፤ የኢማን ግማሽ ነው። ኢማን ሲባል ሁለት ነውና: ግማሹ ትእግስት ግማሹ ደሞ ምስጋና ነው።” (መዳሪጁ ሳሊኪን ኢብኑል ቀይም)
(3) ደስተኛነት: ኢስላማዊ ፍርዱ “ሙስተሓብ” (የተወደደ) ሲሆን ከትእግስት ከፍ ያለ ደረጃ አለው።
(4) አመስጋኝነት: ኢስላማዊ ፍርዱ “ሙስተሓብ” ሲሆን በላጩና የተሟላው ደረጃ ነው።

ሁለተኛ: አራቱ መርሆዎች

***አላህ እሱን ለመታዘዝ ይግጠምህና እወቅ! ሓኒፍ (ወደ እውነት የተዘነበለች) የሆነችዋ የኢብራሂም መንገድ “አላህን በብቸኝነት ጥርት አድርገህ ማምለክ ነው።” አላህ የሰው ልጆችን በሙሉ ያዘዘውም በዚሁ ነው። ለሷም ነው የፈጠራቸው: ልክ ከፍ ያለው አላህ በተከታዩ አንቀፅ እንዳለው: {﴿وَما خَلَقتُ الجِنَّ وَالإِنسَ إِلّا لِيَعبُدونِ﴾ [الذاريات: ٥٦]} {ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።}(ዛርያት 56)(1)***

*አላህ የፈጠረህ እሱን ልታመልከው መሆኑን ከተረዳህ አምልኮ ከተውሒድ ጋ ካልሆነ አምልኮ እንደማይባልም እወቅ። ልክ ሶላት ከጡሀራ ውጭ ሶላት ልትባል እንደማትችለው ሁሉ። አምልኮ (ዒባዳ) ላይ ሽርክ ከገባበት ይበላሻል ነጃሳ እንዳረፈበት ጡሀራ ማለት ነው። አምልኮ ላይ ሽርክ ከታከለበት እንደሚያበላሻት፣ ስራን እንደሚያጠፋና ባለቤቱንም እሳት ላይ ዘውታሪ እንደሚያደርገው ካወቅክ ይበልጥ የሚያሳስብህ ጉዳይ ጉዳዩን ማወቅ መሆኑን ተረዳህ ማለት ነው። ምናልባት አላህ ከዚህ ሽርክ ከሚባለው ሰንሰለት ቢያተርፍህ፤ ያን በማስመልከት አላህ ተከታዩ አንቀፅ ያስተላለፈበትን: {﴿إِنَّ اللَّهَ لا يَغفِرُ أَن يُشرَكَ بِهِ وَيَغفِرُ ما دونَ ذٰلِكَ لِمَن يَشاءُ...﴾[النساء: ٤٨]} {አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም። ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል። ...}(አል-ኒሳእ 48)*

**ይህም አላህ በቁርአን የጠቀሳቸውን አራት መርሆዎችን በመረዳት ነው።**

***የመጀመርያው መርህ: እነዚያ የአላህ መልዕክተኛ የተፋለሟቸው ከሀዲያን አላህ ፈጣሪና አስተናባሪ መሆኑን የሚያፀኑ ሆነው ሳለ ወደ ኢስላም አላስገባቸውም። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {﴿قُل مَن يَرزُقُكُم مِنَ السَّماءِ وَالأَرضِ أَمَّن يَملِكُ السَّمعَ وَالأَبصارَ وَمَن يُخرِجُ الحَيَّ مِنَ المَيِّتِ وَيُخرِجُ المَيِّتَ مِنَ الحَيِّ وَمَن يُدَبِّرُ الأَمرَ فَسَيَقولونَ اللَّهُ فَقُل أَفَلا تَتَّقونَ﴾ [يونس: ٣١]} {«ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማን ነው መስሚያዎችንና ማያዎችንስ የፈጠረ ማን ነው ከሙትም ሕያውን የሚያወጣ ከሕያውም ሙትን የሚያወጣስ ማን ነው ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብርስ ማን ነው» በላቸው። «በእርግጥም አላህ ነው» ይሉሃል። «ታዲያ (ለምን ታጋራላችሁ) አትፈሩትምን» በላቸው።} (የኑስ 31) (2)***

(1) አላህ ይዘንለትና ሸይኹ ለምን ተውሒድ እንደምንማር እያብራሩ ነው።

(2) እነዚያ ነብዩ ከመሃላቸው የተላኩባቸው ህዝቦች በተውሒዱ ሩቡቢያ ያፀኑ ነበር፤ ይህ ከመሆኑም ጋ ግን የአላህ መልእክተኛ ﷺ ተፋለሟቸው። በነሱና በረሱል ﷺ መካከል የነበረው አለመግባባት ነጥብ ተውሒዱል ኡሉሂያን በማስመልከት ነበር። ከዒባዳ አንዳችንም ቢሆን ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ የሰጠ መሽሪክ ከሃዲ ነው።

***ሁለተኛው መርሆ: እነሱ የሚሉት "ወደነሱ የተቅጣጨንበትና እነሱን የለመንበት ምክንያት መቅረብንና ሸፈዓን ብቻ ፈልገን ነው።"***

***መቅረብን ፍላጎታቸው እንደሚያደርጉ ማስረጃው: {﴿...وَالَّذينَ اتَّخَذوا مِن دونِهِ أَولِياءَ ما نَعبُدُهُم إِلّا لِيُقَرِّبونا إِلَى اللَّهِ زُلفى إِنَّ اللَّهَ يَحكُمُ بَينَهُم في ما هُم فيهِ يَختَلِفونَ إِنَّ اللَّهَ لا يَهدي مَن هُوَ كاذِبٌ كَفّارٌ﴾[الزمر: ٣]} {...እነዚያም ከእርሱ ሌላ (ጣዖታትን) ረዳቶች የያዙት «ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቀርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም» (ይላሉ)። አላህ በዚያ እነርሱ በእርሱ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው ይፈርዳል። አላህ እርሱ ውሸታም ከሓዲ የኾነን ሰው አያቀናም።}(አልዙመር 3)(1)***

***ሸፋዐ (ምልጃ) ሁለት አይነት ነው: የፀና ሸፋዓ እና የተወገዘ ሸፋዓ ናቸው። ⑵***

⑴ የሽርክና የክህደት ሰዎች ውድቅ የሆኑ አማልክቶቻቸውን አይጣሩ፤ ወደነሱ አልተቅጣጩ (ወደ አላህ) መቀራረብንና ምልጃን ፈልገው ቢሆን እንጅ። በዚህም ነብዩ ﷺ ዘንድ ካፊሮች ሊሆኑና ሊፋለሟቸው ተገባቸው።
⑵ ሸፋዓ: በ(ዓረብኛ)ቋንቋ ደረጃ ነጠላን ጥንድ ማድረግ ማለት ሲሆን እንደሸሪዓው ለሌሎች ጥቅም ለማምጣት ወይም ክፋት ለመመከት አማካኝ መሆን ማለት ነው።

## የምልጃ (ሸፋዓ) አይነቶች

**የተወገዘ:** ቁርአን ያወገዛት አይነት ሸፋዓህ። ከአላህ ውጭ በማይችለው ጉዳይ ከሌላ አካል መፈለግ ነው። ኢስላማዊ ፍርዱ: ትልቁ ሽርክ

**ፍጡራኖች በሚችሉት:** አራት መስፈርቶች ከተሟሉ ይቻላል

- ያለ (ቅርብ)
- በሕይወት ያለ
- የሚችል
- ሰበብ (ተደርጎ ሊያዝ) ይገባል

**የፀናች:** ይህች ከአላህ የምተፈለገዋ ነች። እንደቅድመ መስፈርትም

- ለሸፋዓው አላህ ሊፈቅድ ይገባል
- ሸፋዓ አድራጊውን አላህ ሊወድለት(እውቅና ሊሰጠው)
- ሸፋዓ ለሚደረግለትም (ሊወድለት) ይገባል።

**{በሰማያት ውስጥ ካለ መልአክም ብዙዎች (ሊማለዱለት) ለሚሻውና ለሚወደው ሰው ከፈቀደ በኋላ ቢኾን እንጅ ምልጃቸው ምንም አትጠቅምም።}** (ነጅም 26)

**አጠቃላይ** መልእክተኞች፣ ነብያቶች፣ መላኢኮች፣ የተውሒድ ሰዎች እንዲሁም ህፃናቶች የሚያደርጉት ምልጃ

- የተውሒድ ሰዎች ደረጃ ከፍ እንዲል የሚደረግ ሸፋዓህ
- ከተውሒድ ሰዎች ሆኖ [ስራው] እሳት ያስፈረደበት እሳት እንዳይገባ
- እሳት የገባ የተውሒድ ሰው ከእሳት እንዲወጣ

**ማንም ሳይጋራቸው ነብዩ ﷺ ብቻ የሚያደርጉት**

- ትልቋ ሸፋዓህ
- ለአጎታቸው ቅጣቱ እንደቀንስለት ያደረጉት ምልጃ
- የጀነት በሮች እንዲከፈቱ የሚያደርጉት ምልጃ

ውግዝ የሆነችዋ ሸፋዓህ: አላህ እንጅ ሌላ በማይችለው ጉዳይ ከሌላ መፈለግ፤ ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በርሱ ውስጥ ሽያጭ (መበዠት)፣ ወዳጅነትም፣ ምልጃም የሌለበት ቀን ከመምጣቱ በፊት ከሰጠናችሁ ነገር ለግሱ። ከሓዲዎችም በዳዮቹ እነርሱ ናቸው።} (አልበቀራህ 254)
የፀናችዋ ሸፋዓህ: ከአላህ የምትፈለገዋ ስትሆን ሸፋዓህ አድራጊውን በሚያደርገው ሸፋዓህ የሚከበር ነው። ሸፋዓ የሚደረግለትም ደግሞ ከአላህ ፍቃድ በኃላ እና አላህ ተግባሩንም ንግግሩንም ለወደደለት ነው የሚሆነው። ልክ ከፍ ያለው አላህ በቁርአን እንዳለው: {…ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ የሚያማልድ ማነው} (በቀራህ 255)

ሶስተኛው መሰረታዊ መርህ: (1) ነብዩ ﷺ የወጡት በዒባዳቸው የተለያዩ በሆኑ ሰዎች ነው። ከነሱ መካከል መላእክቶችን የሚያመልክ አለ፤ ከነሱም ነብያቶችንና ደጋግ ሰዎችን የሚያመልክ አለ፤ ከነሱም ዛፎችንና ድንጋዮችን የሚያመልክ አለ፤ ከነሱም ፀሃይና ጨረቃ የሚያመከክ አለ፤ ነብዩ ﷺ ግን ልዩነር ሳይፈጥሩ ሁሉንም ነው የተፋለሟቸው።

ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: { ﴿وَقاتِلوهُم حَتّى لا تَكونَ فِتنَةٌ وَيَكونَ الدّينُ كُلُّهُ لِلَّهِ...﴾[الأنفال: ٣٩] {ሁከትም እስከማትገኝ ሃይማኖትም ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሏቸው።...}(አል-አንፋል 39)

ለፀሃይና ጨረቃ(መመለክ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: { ﴿وَمِن آياتِهِ اللَّيلُ وَالنَّهارُ وَالشَّمسُ وَالقَمَرُ لا تَسجُدوا لِلشَّمسِ وَلا لِلقَمَرِ وَاسجُدوا لِلَّهِ الَّذي خَلَقَهُنَّ إِن كُنتُم إِيّاهُ تَعبُدونَ﴾[فصلت: ٣٧] {ሌሊትና ቀንም ፀሐይና ጨረቃም ከምልክቶቹ ናቸው። ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ፡ ፡ ለእዚያም ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ። እርሱን ብቻ የምትግገዙ እንደ ኾናችሁ (ለሌላ አትስገዱ)።}(ፉሲለት 40)

ለመላእክቶች (መመለክ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: { ﴿وَلا يَأمُرَكُم أَن تَتَّخِذُوا المَلائِكَةَ وَالنَّبِيّينَ أَربابًا...﴾[آل عمران: ٨٠] {መላእክትንና ነቢያትንም አማልክቶች አድርጋችሁ እንድትይዙ ሊያዛችሁ (አይገባውም)።...}(አሊ-ዒምራን 80)

(1) ይህች መርሆ ሽርክ የሚሆነው ግኡዝ ጣኦትን በማምለክ ብቻ ነው በሚሉት ላይ "ረድ" ለማድረግ ግልፅና ጉልህ ማስረጃ ነች። ከድሮውም ሸሪዓዊ ማስረጃዎች የመጡት በተለይ ግኡዝ ጣኦታትን ሌሎቹንም ከአላህ ውጭ የሚመለኩ ውዳቂዎችን አንድ ጉድጓድ ላይ ጨምሮ በማውገዝ ነው። የአላህ መልእክተኛ ﷺ በመካከል ልዩነት ሳይፈጥሩ ሁሉንም እንደጧጉት ቆጥረው አንድንም ሳያስቀሩ አምልኮ ሁሉ ለአላህ እንዲሆን ነው የተፋለሟቸው።

ለነብያቶች (መመለክ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: { ﴿وَإِذ قالَ اللَّهُ يا عيسَى ابنَ مَريَمَ أَأَنتَ قُلتَ لِلنّاسِ اتَّخِذوني وَأُمِّيَ إِلٰهَينِ مِن دونِ اللَّهِ قالَ سُبحانَكَ ما يَكونُ لي أَن أَقولَ ما لَيسَ لي بِحَقٍّ إِن كُنتُ قُلتُهُ فَقَد عَلِمتَهُ تَعلَمُ ما في نَفسي وَلا أَعلَمُ ما في نَفسِكَ إِنَّكَ أَنتَ عَلّامُ الغُيوبِ﴾[المائدة: ١١٦] {አላህም፡- «የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ፡- እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብላሃልን» በሚለው ጊዜ (አስታውስ)። «ጥራት ይገባህ፤ ለእኔ ተገቢዬ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም። ብዬው እንደ ኾነም በእርግጥ ዐውቀኸዋል። በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ። ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም። አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና» ይላል።} (አል-ማኢዳህ 116)

ለደጋጎች (መመለክ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {እነዚያ እነርሱ የሚግገዟቸው ማንኛቸውም (ወደ አላህ) በጣም ቀራቢያቸው ወደ ጌታቸው መቃረቢያን (ሥራ) ይፈልጋሉ። እዝነቱንም ይከጅላሉ። ቅጣቱንም ይፈራሉ።...} (አል-ኢስራእ 57) ለዛፍና ድንጋይ (መመለክ) ማስረጃው ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {አል-ላትንና አል-ዑዛን አያችሁን?(19) ሦስተኛይቱንም አነስተኛዋን መናትን (አያችሁን? የምትግገዟቸው ኃይል አላቸውን?)} (አል-ነጅም 19-20)

***በአቢ ዋቂዲን አለይሢይ ረድየሏሁ ዓንሁ ሓዲሥ እንዲህ የሚል ይገኛል "ለእስልምና (የእምነት) ቃል እንግዶች ሳለን ከነብዩ ﷺ ጋ ወደ ሑነይን ዘመቻ ወጣን። ለሙሽሪኮችም ደሞ እሷው ጋ የሚቀማመጡባትና ትጥቃቸውን የሚያንጠለጥሉባት የሆነች 'ዛቱ አንዋጥ (የመንጠልጠል ባለቤት)' የሚሏት የቁርቁራ ዛፍ አለቻቸው። በጉዟችን ሳለን የቁርቁራ ዛፍ በተመለከትን ጊዜ 'የአላህ መልዕከተኛ ሆይ! ለነሱ እንዳላቸው ለኛም የመንጠልጠል ባለቤት አድርጉልን' አልናቸው።..." (ሓዲሡ ሱነን ቲርሚዚይ አብዋቡል ፊተን ሓዲሥ ቁጥር 2180 ላይ ዘግበውታል)***

***አራተኛው መርሆ: የወቅቱ ሙሽሪኮች ሽርክ ከቀደምቶች ሽርክ የበረታ ነው። ምክንያቱም ቀደምቶቹ ሽርክ የሚፈፅሙት በተድላ ጊዜ እንጅ በጭንቅ ጊዜ አላህን ጥርት አድርገው ነው የሚገዙት። የወቅቱ ሙሽሪኮች ግን ሽርካቸው ዘወትር በተድላም በጭንቅም ጊዜ ነው። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {በመርከቦች ውስጥ በተሳፈሩ ጊዜም አላህን መገዛትን ለእርሱ ብቻ ያጠሩ ኾነው ይጠሩታል። ወደ የብስ (በማውጣት) ባዳናቸው ጊዜም ወዲያውኑ እነርሱ (ጣዖትን) ያጋራሉ።}(አል-ዐንከቡት 65) (1)***

***አሏህ ይበልጡን ያውቃል፤ የአሏህ ሶለዋትና ሰላም በሳቸው በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በባልደረቦቻቸውም ላይ ይስፈን።***

(1) ሽይኹ አላህ ይዘንለትና በዚሁ መርሆ የወቅቱ ሙሽሪኮች አቋም አደገኝነት ልክ ግልፅ ማድረጉ ነው። ሽርካቸው ከቀደምቶች ሽርክ የከፋ ነውና። ምክንያቱን የወቅቱ ሙሽሪኮች ሽርካቸው በጭንቅም በተድላም ጊዜ ነው። የድሮ ሙሽሪኮች ሽርክ ግን ሲመቻቸው ነውንጅ የሚያጋሩት በጭንቅ ጊዜ በአላህ ብቸኛ ተመላኪነት ያምናሉ።
እነዚያ ነብዩ ﷺ በመካከላቸው የተላኩባቸው ሰዎች ሽርካቸው ያነሰ ከመሆኑም ጋ አላህ ዘንድ ካፊር ከሆኑ እንዴት ነው ታድያ ሽርካቸው ዘወትር በተድላም በጭንቅም የሆኑ ሰዎች?! የነሱ ካፊር መሆን በቀዳሚነት ይሆናል ማለት ነው።

አራቱ መርሆዎች ፤ የ ” ከሸፉ ሹቡሃት” (ውዥንብሮችን ማጋለጥ) ኪታብ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ማለት ነች

መግቢያ፤ የስኬት ርእሶችን ይዘለት

የስኬት ርእሶች

ሲሰጥ አመስጋኝ

ፀጋ ፈተና ነው፤ ማስረጃውም {ለመፈተንም በክፉም በበጎም እንሞክራችኋለን:: ወደኛም ትመለሳላችሁ።}(አል አንቢያእ 35)

| | | |
|---|---|---|
| ፀጋን ማመስገን | ከተውሒዱል ሩቡቢያህ ጋ በተያያዘ | ✓ ባለቤቱ እሱ በመሆኑ ጀነት የምትፈለገው ከሱ እንደሆነው ሁሉ ሲሳይም ከአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ እንጅ ሊፈለግ አይገባውምና ከሱ ጋ መተሳሰሩ የግድ ነው |
| | ከተውሒዱል ኡሉሂያህ ጋ በተያያዘ | ✓ በልቦናው ያመሰግናል፡ እሱ ዘንድ ያለው ፀጋ ሁሉ ከአላህ እንጅ ከሌላ እንዳልሆነ በማመንና በማረጋገጥ |
| | | ✓ በአንደበቱ ያመሰግናል፡ {«ይህ ከጌታዬ ችሮታ ነው፡፡ የማመሰግን ወይም የምክድ መኾኔን ሊሞክረኝ (ቸረልኝ)።}(ነምል 40) |
| | | ✓ በአካሉ ያመሰግናል፡ ፀጋን ሁሉ ከምንነቱ አንፃር ሰጪ ዘንድ በሚያስመሰግን ቦታ ላይ ፀጋን ማዋል፤ የገንዘብ ፀጋ ሹክር አሏህን በመታዘዝ ላይ ማፍሰሱ ሲሆን የእውቀት ሹክር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለጠየቀ መስጠት ነው። |
| | መከራ ላይ ሲሆኑ ሰዎች ያሏቸው ሁኔታ | ✓ ብስጩ፡ ፍርዱ ከትላልቅ ወንጀል የሚመደብ ሲሆን ወደ ትንሹ ሽርክ የሚደርስበትም ሁኔታ አለ። ብስጭቱ በልቦና፣ በአንደበትም በአካልም ሊሆን የሚችል ነገር ነው። |
| | | ✓ ታጋሽ፡ የትእግስት ፍርዱ በኡመተል ኢስላም ሙሉ ስምምነት መሰረት ግዴታ ነው። ትእግስትም በልቦና፣ በአንደበትና በአካል የሚሆን ነው። ትእግስት መቅመሱ እንደስሙ መራራ ቢሆንም ፍሬው ግን ከማር የጣፈጠ ነው። |
| | | ✓ ወዶ የሚቀበል፡ ፍርዱ የተወደደ ነው። ለአላህ ካለው ዉዴታ አንፃር ያጋጠመው ነገር ሁሉ ከአሏህ መሆኑንና አሏህ በባሪያው ላይ የሚወስነው ሁሉ መልካም መሆኑንም ያውቃል። |
| | | ✓ አመስጋኝ፡ እጅግ በጣም ትልቁ ደረጃ ነው። ይበልጥ የተወደደና ከአመስጋኝ ባሪያዎች የሚሆንበትም ነው። |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ወንጀል በሰራም ጊዜ መሃርታን ይጠይቃል** | | | | | | | |
| ❖ አል-ሓኒፊያ፡ የኢብራሂም መንገድ፤ አሏህ የፈጠረህ እሱን ልታመልከው ነው። አምልኮ ደሞ ከተውሒድ ጋ ሆኖ ካልሆነ በቀር አምልኮ አይባልም። አምልኮ ላይ ሽርክ ከታከለበት ያበላሻታል ስራዋንም ዉድቅ ያደርጋታል፤ የድርጊቱ ባለቤትም ዘላለም እሳት ዉስጥ ከሚሆኑት ይመደባል። ስለዚህ አንተ ዘንድ ያለው ትልቁ ሃሳብ እሱኑ ማወቅ ነው። | ለምንድን ነው ተውሒድ የምንማረው? እና የሽርክ አደገኛነት | | | | | | |
| 1. አንደኛ መርሆ፡ እነዚያ የአሏህ መልእክተኛ የተላኩባቸው ሙሽሪኮች በተውሒዱል ሩቡቢያህ ቢያፀድቁም በተውሒዱል ኡሉሂያህ አያፀድቁም ነበር፤ ይህ ታዲያ ውደ ኢስላም አላስገባቸውም። | አራቱ መርሆዎች፡ | | | | | | |
| 2. ሁለተኛው መርሆ፡ ካፊሮች ጣኦታትን ሲያመልኩ ምክንያታቸው መቀራረብንና ምልጃን መፈለጋቸው ነው። | | | | | | | |
| 3. ሶስተኛው መርሆ፡ የአሏህ መልእክትኛ የተላኩባቸው ሰዎች በሚያመልኩት የተለያዩ ቢሆኑም በመካከላቸው ልዩነት ሳይፈጥሩ ነው የተፋለሟቸው። | | | | | | | |
| 4. አራተኛ መርሆ፡ የወቅቱ ሙሽሪኮች ሽርክ ከድሮዎቹ የባሰ ነው። | | | | | | | |

# የአራቱ መርሆዎች ፈተና

ስም.................................................................
ከኪታቡ ተውሒድ የሸመደድከው መጠን.........................
አራቱን መርሆዎች ሸምድደሃቸዋልን...........................

| ድርጊቱ | ከቁርአን ወይም ከሓዲሥ ማስረጃው |
|---|---|
| ፀጋ ፈተና ለመሆኑ | |
| ካፊሮች በሩቡቢያ እንደሚያፀድቁ | |
| መቀራረብን እንደሚፈልጉ | |
| የተወገዘችዋ ምልጃ | |
| ለፀሃይና ጨረቃ (መመለክ) ማስረጃው | |
| ለመላእክቶች (መመለክ) ማስረጃው | |
| ለነቢያቶች (መመለክ) ማስረጃው | |
| ለሷሊሆች (መመለክ) ማስረጃው | |
| ለድንጋይና ዛፎች (መመለክ) ማስረጃው | |
| ሙሽሪኮች በጭንቅ ጊዜ በኢኽላስ እንደሚያጠሩነ በተድላ ጊዜ እንደሚያጋሩ | |
| ስለ ሽርክ(ከፋት) ማስረጃው | |

ስለ ተከታዮቹ (ነጥቦች) የምታውቀውን ፃፍ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ለምንድን ነው ተውሒድ የምንማማረው? | 1. | 2. | 3. | 4. | |
| 1. | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| ለምንድን ነው አራቱን መርሆዎች የምንማማረው? | 1 | | 2 | | |
| | | | | | |
| አራቱ መርሆዎች ወደ ስንት ይከፈላሉ | 1 | 2 | | 3 | |
| መርሆዎቹ የምን ኪታብ(ይዘት) ጥቅል ናቸው? | | | | | |
| ለምንድን ነው ኪታብ ከሽፉ ሹቡሃትን የማንማረው? | | | | | |
| የስኬት ርእሶች | 1 | 2 | | 3 | |
| አል-ሓኒፊያ ማለት | | | | | |
| መርሆዎቹን የመማር ፍሬ | | | | | |
| የአሏህ ወዳጆች የሚባሉት | ሸይኹል ኢስላም እንዲህ ብለዋል፡ | | | | |
| ለዛም ማስረጃው | | | | | |
| ፀጋን ማመስገን በምን ይሆናል? ከምሳሌው ጋ | 1 | | | | |
| 2 | | | | | |
| 3 | | | | | |
| የአንድ ባርያ ትስስሩ እንዴት ነው የሚሆነው? | | | | | |
| በመከራ ጊዜ የሰዎች ሁኔታ ከኢስላማዊ ፍርዱ ጋ | 1. ፍርዱ የሚገለፅበት በ........ እና............ በ.................<br>2. ፍርዱ የሚገለፅበት በ........ እና............ በ................. | | | | |
| 3. | 4. | | | | |
| ሽፉዓህ(ምልጃ) በቋንቋ ደረጃ | ሽፉዓህ (ምልጃ) ከሸሪዓ አንፃር | | | | |
| ሽፉዓህ ወደ ስንት ይከፈላል? | 1 | | 2 | | |
| የፀናችዋ ሽፉዓህ ቅድመ መስፈርቶች | 1 | 2 | | 3 | |
| አይነቶቿ 1 | ክፍሎቿ፡.................. | ........................... እና | ........................... | | |
| 2 | ክፍሎቿ፡.................. | ...........................እና | ......................... | | |
| አንደኛ መርሆ | | | | | |
| | | | | | |
| ሁለተኛው መርሆ | | | | | |
| | | | | | |
| ሶስተኛ መርሆ | | | | | |

| | |
|---|---|
| አራተኛ መርሆ | |
| | |
| ስራን ሽርክ ከታከለበት | ማስረጃው፡ |

# ማውጫ ሰንጠረዥ


| | | |
|---|---|---|
| 1 | መግቢያ | 3 - 5 |
| 2 | አራቱ ቁምነገሮች | 6 - 10 |
| 3 | ሶስቱ ነጥቦች | 11 - 14 |
| 4 | ተውሒድን የመማር አሳሳቢነት | 15 |
| 5 | ሶስቱ መሰረታዊ መርሆዎች | 16 - 42 |
| 6 | መደምደሚያ | 43 - 45 |
| 7 | ማጠቃለያ በሰንጠረዥ | 46 - 49 |
| 8 | ፈተና | 50 - 54 |
| 9 | አራቱ መርሆዎች | 55-66 |
| 10 | የፈተና ጥያቄዎች | 67-69 |
| 11 | ማውጫ ሰንጠረዥ | 70 |

# የ «ኢስላምን አፍራሾች» ማብራሪያ

የዳዕዋው ኢማም ሸይኹል ኢስላም
ሙሓመድ ቢን ዓብዱል ወሃብ ቢን ሱለይማን አት-ተሚሚይ
አላህ ይዘንለት ፤ በሰፊው ጀነትም ያስገባውና

ማብራሪያው በክቡር ሸይኽ
ዶ/ር ሀይሠም ቢን ጀሚል ሰርሓን
በክቡሩ መስጅደ-ል-ነበውይ የትምህርት ተቋም ነባር አስተማሪ
የታእሲለል ዒልምይ ዌብሳይት ሹም
http://attasseel-alelmi.com

ለሱም፣ ለወላጆቹም እንዲሁም ይህ ኪታብ እንዲወጣ እገዛ ላደረጉ ሁሉ

አላህ መሃርታውን ይለግስ

የመጀመሪያ እትም

መብቱ ብህግ የተጠበቀ ነው።

ከሸይኹ ማረጋገጥ በኋላ በነፃ ለማደል መተርጎም ወይም ማተም ለፈለገ ካልሆነ በቀር

በዚህ ያግኙን:

islamtorrent@gmail.com

# ኢስላምን አፍራሾች

**ሸይኹል ኢስላም ሙሓመድ ቢን ዓብዱል ወሀ-ሃብ አላህ ይዘንለትና እንዲህ ይላል፡**

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው**

**እስልምናን አፍራሾች አስር መሆናቸውን እወቅ**

**የመጀመርያው**: በአምልኮ ከአላህ ጋር ተጋሪ ማድረግ: ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል {አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም። ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል፡፡...} (አን-ኒሳእ 48) እንዲህም ይላል {...እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ። መኖሪያውም እሳት ናት። ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም፡፡} (አል-ማኢዳህ 72) ለሌላ አካል ማረድም እዚሁ የሚካተት ነው። ለአጋንንት ወይም ለቀብር እንደማረድ ማለት ነው።

**ሁለተኛ**: በሱ እና በአላህ መካከል የሚማፀናቸው፣ ሸፋዓ/ምልጃ የሚለምናቸው፣ የሚመካባቸው አማካኝ ያደረገ የካደ ለመሆኑ ኢጅማዕ (ሙሉ ስምምነት) አለበት።

**ሶስተኛ**: የአጋሪዎችን ካፊርነት ያላፀና፣ ወይም ካፊር ለመሆናቸው ከተጠራጠረ ወይም ደሞ መንገዳቸውን ትክክል ነው ያለ ካፊር ሆኗል።

**አራተኛ**: የየትኛውም አካል መመርያ ከነብዩ ﷺ መመርያ ይልቅ የተሟላ ነው ብሎ ያመነ፣ ወይም የሌላ አካል ህግጋት ከሳቸው ህግጋት የተሻለ ነው ብሎ ያመነ - ሰው ሰራሽ ህግን ከሳቸው ህግ እንደሚያስበልጡት አይነቱ - ካፊር ነው።

**አምስተኛ**: ነብዩ ﷺ ይዘውት ከመጡት (መመርያ) አንዳች ነገርን የጠላ ቢሰራበት እንኳ ካፊር ነው።

**ስድስተኛ**: ከነብዩ ﷺ ሃይማኖት በአንዳች ነገር ወይም በአላህ ምንዳ ወይም ደሞ በቅጣቱ የተሳለቀ ክዷል። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {...«በአላህና በአንቀጾቹ፣ በመልክተኛውም ታላግጡ ነበራችሁን» በላቸው። (65) አታመካኙ፤ ከእምነታችሁ በኋላ በእርግጥ ካዳችሁ።...} (አት-ተውባህ 65-66)

**ሰባተኛ**: ድግምት -መስተፋቅርና መስተፃርርም እዚሁ የሚመደቡ ናቸው። - ወይ የሰራው አልያም የወደደ ካፊር ሆኗል። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {«እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ» እስከሚሉም ድረስ አንድንም አያስተምሩም።} (አል በቀራህ 102)

**ስምንተኛ**: አጋሪዎችን በሙስሊሞች ላይ ማገዝና መርዳት። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {...ከእናንተም ውስጥ ረዳቶች የሚያደርጋቸው ሰው እርሱ ከነርሱው ነው። አላህ አመጸኞችን ሕዝቦች አያቀናም።} (አል ማኢዳህ 51)

**ዘጠነኛ**: ልክ ኸዲር ከሙሳ ﷺ ሸሪዓ እንደወጣው ሁሉ ለአንዳንድ ሰዎች ከነብዩ ሙሓመድ ﷺ ሸሪዓ መውጣት ይችላሉ ብሎ የሚያምን ካፊር ነው።

**አስር**: ላይማረው ላይሰራበት ከአላህ ዲን ጀርባውን የሰጠ: ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {በጌታውም አንቀጾች ከተገሰጸና ከዚያም ከተዋት ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው? (የለም)፤ እኛ ከተንኮለኞቹ ተበቃዮች ነን።} (ሰጅዳህ 22)

በነዚህ አፍራሾች መካከል የቀልዱም ይሁን የምሩ አልያም ፈርቶም ልዩነት የለውም። ተገዶ ካልሆነ በቀር። ሁሉም አደገኛ ሊባል የሚችልና ብዙ ጊዜ የሚከሰትም ጭምር ነው። ሙስሊም ሊጠነቀቀውና በራሱ ላይ ሊሰጋ ይገባዋል። ቁጣውን ከሚያስከትልና ቅጣቱን ከሚያስፈርድብን ነገር በአላህ እንጠበቃለን። የአላህ ሶላዋት ከፍጥረቱ ምርጡ በሆኑት፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸውም ይስፈን።

# ማብራሪያ

## የሸይኹ መግቢያ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው እስልምናን አፍራሾች አስር መሆናቸውን እወቅ**

የኢስላም ሙሁራኖች ለምንድን ነው ኪታቦቻቸውን በቢስሚላህ የሚጀምሩት?

- በአላህ መፅሃፍና በነብያት (ዓለይሂሙ ሰላም) ከመመራት አንፃር
- *{ጣጣ እያለበት አላህን በማወደስ ያልተጀመረ ጉዳይ ሁሉ የተቆረጠ ነው}* የሚለው ሓዲሥ ዶዒፍ ቢሆንም ትርጉም ከመስጠት አንፃር
- ቀደምቶችን ከመከተል አንፃር
- በተከበረው የአላህ ስም በረካን ከመሻት አንፃር

በቁርአንና በሓዲሥ ቁጥር ከተጠቀሰ፡

- ከተጠቀሰው ቁጥር በቁርአንና በሓዲሥ ሌላ ተጨማሪ ብዛት ካላገኘን የተጠቀሰው ቁጥር ትርጉም ይይዛል። ማለትም: አይጨመርበትም። ለምሳሌ በጅብሪል ዓለይሂ ሰላም ሓዲሥ የተጠቀሰው የኢስላምና የኢማን ማእዘናት
- በቁርአንና በሓዲሥ ከተጠቀሰው ቁጥር በላይ ካገኘን ግን የተጠቀሰው ቁጥር ትርጉም አልባ ይሆናል። ማለትም: በቁርአንና በሓዲሥ በመጣው ልክ ይጨመርበታል። ለምሳሌ: "አምስት ነገራቶች ከተፈጥሮ ናቸው።..." እንዲሁም "ሰባት አውዳሚዎችን ተጠንቀቁ..." መሰል የነቢዩ ﷺ ንግግሮች።

**አንዳንድ ጊዜ ለምንድን ነው ቁጥር የሚወሰውና ትርጉምም ላይኖረው?**

ይህ ከነብዩ ﷺ ጥሩ የማስተማር ችሎታ ነው። ምክንያቱም እንዲህ የሚያደርጉት አድማጮቹ በዚሁ መድረክ ላይ የሚባለውን ከጊዝያቶች በኋላ ቶሎ ይመጣላቸው ዘንድ አስተካክለው እንዲይዙት ስለፈለጉ ነው። "ሶስት የምምልባቸው ነገራቶች አሉ። የምነግራችሁ ነገርም አለኝ ሸምድዱት፤ 'ምፅዋት የአንድን ባርያ ገንዘብ አይቀንስበትም…'"

**ለምንድን ነው (ኢስላምን) ስለሚያፈርሱት ነገራቶች የምንማረው?**

እንድንጠነቀቀውና እንዳያንዳልጠን የጎላ ጥቅም አለው። ኧረ እንደውም እጅግ በጣም ጠቃሚ ከሚባሉት ነው። ልክ ዉዱአችን እንዳይፈርስ ዉዱእ የሚፈርሱ ነገራቶችን እንደምንማረው፤ ሶላታችን ውድቅ እንዳይሆን ሶላትን ውድቅ የሚያደርጉ ነገራቶችን እንደምንማረው ነው። ሑዘይፋ ኢብኑል የማን ረድየላሁ ዓንሁ እንዲህ ይላል: "ሰዎች የአላህ መልዕክተኛን ﷺ ስለመልካም ነገር ይጠይቁ ነበር፤ እኔ ግን ስለመጥፎ ነገር ነበር የምጠይቃቸው፤ እንዳያገኘኝ ስጋት።"

**ኢስላምን የሚያፈርሱ ነገራቶች ምን ምን ናቸው?**

እነኝህ እስልምናውን ሊያፈርሱና ከኢስላም አውጥተው ወደ ትልቁ ኩፍር የሚያስገቡ ነገራቶች ናቸው። ኢስላም {ለ አላህ ራስን በተውሒድ ማስገዛት፤ በታዛዥነት ለሱ መጎተት፤ ከሽርክና ከሽርክ ሰዎች መጥራራት}

**ትርጉም:**
አንድን ሙስሊም ከኢስላም ወደ ትልቁ ኩፍር የሚያስወጡ ነገራቶች ማለት ነው። አላህ ሊጠብቀንና ነፃ ሊያድርገን ዘንድ እንለምነዋለን።

**ለምንድን ነው ዑለሞች አንዳንዴ አፍራሾች አንዳንዴም አበላሾች ሌላ ጊዜ ደሞ ዉድቅ የሚያደርጉ እያሉ የሚገልፁት?**
ይህም ተማሪ እንዳይሰላች አገላልፁን ከማስፋት አንፃር ነው እንጅ ትርጉሙ አንድ ነው። የዉዱእ/የኢስላም አፍራሾች፣ ሶላትን ዉድቅ የሚያደርጉ፣ ፆምን የሚያበላሹ እንደሚባለው።

**እነዚህን አፍራሾች በዑለሞች መካከል ሙሉ ስምምነት አለባቸውን?**
አዎ

**በቁጥርስ የተገደቡ ናቸውን?**
አይ በቁጥር የተገደቡ አይደሉም
**ለምን ታድያ አስር ናቸው አለ?**
አደገኞቹን ማለቱ ነው በቃል እንዲሸመደዱ።

ጥቅል በሆነ መልኩስ በቁጥር መገደብ ይቻላልን?

| | | | |
|---|---|---|---|
| (የሚያከፍር) ጥርጣሬ፡ የነቢዩ ﷺ ጥሪ ደርሷቸው ያላመኑ ክርስቲያንና አይሁዶች ካፊር ለመሆናቸው መጠራጠር | (የሚያከፍር) እምነት፡ ከአላህ ውጭ ባለ አካል ጥቅም ይመጣል የሚል እምነትን ይመስል | (የሚያከፍር) ድርጊት፡ ድግምትን ይመስል | (የሚያከፍር) ንግግር፡ አላህን ወይም መልዕክተኛውን ﷺ መስደብ ይመስል |

አስሩን አፍራሾች ነብዩ ﷺ አውስተዋቸዋልን? ማስረጃውስ?

አዎ እነኝህን አፍራሾች በሙሉ ነብዩ ﷺ አውስተዋቸዋል። ኸረ እንደውም (ኢስላምን) አፍራሽ ሁሉ ከቁራንና ሓዲሥ ማስረጃ አለው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል {እንደዚሁም (እውነቱ እንዲገለጽና) የወንጀለኞችም መንገድ ትብራራ ዘንድ አንቀጾችን እንገልጻለን።} (አል አንዓም 55)

አንድ አፍራሽ ነገርን ላደረገ ያየ ወይም ያወቀ ሁሉ የኩፍር ፍርድ ይሰጥበታልን?

አይ በግላዊነት ለይቶ ካፊር ለማለትማ በእውቀታቸው ሰሪዎች ወደሆኑ የሸሪዓ ዳኛ ዑለሞች መመለስ ግድ ነው። የአላህ መልዕክታኛ ﷺ እንዲህ ይላሉ፡ “የትኛውም ሰው ለወንድሙ ‘አንተ ካፊር’ ያለ አንዳቸው ላይ ታርፋለች።”

አፍራሾችን በማስመልከት የፃፈ ማን አለ?

በፊቅህ ዙርያ የፃፈ ሁሉ “የሙርተድን ብይን” ሲያሰፍር አፍራሾችን ጠቅሷል። ራሱን በቻለ መልኩ አንድ ኪታብ አድርጎ ለመፃፉ ግን (ሸይኹ) የመጀመርያ ነው።

### አፍራሾችን በማስመልከት በድርጊቱ እና በፈፃሚው መካከል ልዩነት ይደረጋልን?

አዎ እንዴታ። ምክንያቱም ኩፍር ላይ የወደቀ ሁሉ ኩፍር የሚያርፍበት አይደለምና። ግለሰብን በኩፍር ለመፈረጅ ማስረጃን ማቆምና ውዥንብር መነሳቱ የግድ ነው። አላህ ይዘንለትና የሸይኹ አላማም ግለሰቦችን ማክፈር አይደለም። ይልቅ አላማው አፍራሾችን ማስጠንቀቅ ነው። ይህም ደሞ ኡማው ጋ መመካከር ነው።

### አፍራሾችን በማስመልከት የተማረ ሰው ምን ማድረግ ይኖርበታል?

አንድ ሙስሊም ሊጠነቀቅበትና በራሱም ላይ ስጋት ሊያድርበት ሊያስጠነቅቅም ይገባዋል።  በግለሰቦች ላይ ፍርድ መስጠቱ ላይ ግን ወደ ታላላቅ ዑለሞችና ወደ የሸሪዓው ዳኞች መመለስ ይገባል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡

{ከጎሳችሁ የሆነ ችግራችሁ በእርሱ ላይ ጽኑ የሆነ፣ በእናንተ (እምነት) ላይ የሚጓጓ፣ በምእመናን (ላይ) ርኅሩኅ አዛኝ የኾነ መልዕክተኛ በእርግጥ መጣላችሁ። ቢያፈገፍጉም አላህ በቂዬ ነው። ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። በእርሱ ላይ ተጠጋሁ እርሱም የታላቁ ዐርሽ ጌታ ነው በላቸው።} (ተውባ 128)

## የመጀመርያው አፍራሽ

በአምልኮ ለአላህ ተጋሪ ማድረግ። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡ { አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም። ከዚህ ሌላ ያለውንም (ኀጢአት) ለሚሻው ሰው ይምራል። በአላህም የሚያጋራ ሰው ታላቅን ኀጢአት በእርግጥ ቀጠፈ።} (ኒሳእ 48) እንዲሁም { እነዚያ «አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው» ያሉ በእርግጥ ካዱ። አልመሲህም አለ፡- «የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ።» እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ።} (አልማኢዳህ 72) ከአላህ ዉጭ ላለ አካል እርድ ማቅረብም ከዚሁ ይመደባል። ለጅን እንደሚያርዱት ማለት ነው።

### የሽርክ አይነቶች

| ትልቁ | ትንሹ |
|---|---|
| (ሸይኹም የፈለጉት ይህ አይነቱን ነው) ተጨባጩ፡ ከአላህ ውጭ ላለ አካል በአስተናባሪነት በኩል ድብቅ ችሎታ እንዳለው ወይም ደዌ ጥቅምን ማምጣትና ክፋትን መመከት እጁ ላይ እንዳለ ማመን። | ተጨባጩ፡ አላህ ሰበብ ያላደረገውን ሰበብ ማድረግ እንዲሁም ወደ ትልቁ ሽርክ የሚያዳርስ ሁሉ። |
| • ከመንገዱ(ከኢስላም) ያስወጣል<br>• ስራን በሙሉ ያበላሻል<br>• ደምና ንብረቱን ለባለስልጣኑ ሓላል ያደረግበታል<br>• ጀሃነም ዉስጥ ለዘላለም ዘውታሪ ያደርገዋል<br>• (ከመለያዎቹ) በሸሪዓ “ትልቁ” በሚል ከተጠራ<br>• ትልቅነቱን በሚጠቁም ቋንቋዊ አገላለፅ ከመጣ | • ከመንገዱ(ከኢስላም) አያስወጣም<br>• ስራን በሙሉ አያበላሽም<br>• ደምና ንብረቱን ሓላል አያደርግበትም<br>• ጀሃነም ዉስጥ ለዘላለም ዘውታሪ አያደርግም<br>• (ከመለያዎቹ) በሸሪዓ “ትንሹ” በሚል ከተጠራ<br>• በሸሪዓ ሽርክ ቢባልም ትልቅነቱን በሚጠቁም አገላለፅ ካልሆነ |

### ትልቁ ሽርክ መሃርታ ይደረግበታልን?

እዛው ባለበት ለሞተ መሃርታ የለውም። ምክንያቱም አላህ እንዲህ ስላለ፡ { አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍጹም አይምርም።} (ኒሳእ 48) ከሱ ተውባ ካደረገ ግን ይማርለታል። አላህ እንዲህ ስላለ { በላቸው «እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ። አላህ ኃጢኣቶችን በመላ ይምራልና። እነሆ እርሱ መሓሪው አዛኙ ነውና።} (ዙመር 53) ይህም ፀሃይ በመግቢያዋ እስካለውጣች ነው። ነብዩ ﷺ እንዲህ ስላሉ{"ሂጅራ አትቋረጥም ተውባ እስክትቋረጥ ድረስ፤ ተውባም አትቋረጥም ፀሃይ በመግቢያዋ እስክትወጣ ድረስ።"} ወይም ሞት አፋፍ ላይ እስካልሆነ፤ ማለትም ጣዕረ ሞት ላይ እስካልሆነ። አላህ እንዲህ ይላል {ጸጸትንም መቀበል ለእነዚያ ኀጢአቶችን ለሚሠሩ አንዳቸውንም ሞት በመጣበት ጊዜ «እኔ አሁን ተጸጸትኩ» ለሚል… አይደለችም።…} (ኒሳእ 18)

## የተከለከሉ ነገራቶች አይነት

**ትልቁ ሽርክ**
ከባዱ ነው።

**ትንሹ ሽርክ**
ከትልቁ ሽርክ ያነሰ ከትልቁ ወንጀል በላይ

**ከባባድ ወንጀሎች**
ፈፃሚውን በማስመልከት እርግማን፣ (ከራሕመት) መባረር (ከሱ) መጥራራትን ከካፊሮች/ከሙሽሪኮች ነው በሚልና መሰል ልዩ መቀጣጫ የመጣበት፤ ወይም ከሙእሚኖች አይደለም የተባለበት አልያም ከአስቀያሚ እንስሳት የተመሳሰለበት

**ትናንሽ**
ሸሪዓ ልዩ መቀጣጫ ሳያስከትል የከለከለው ሁሉ

**(ኢስላማዊ) ፍርዱ**
ተውባ ማድረግ ግዴታ ነው። ነብዩ ﷺ (ሙሽ አውራጅ ተውባ ካላደረገች…) በሌላ ሓዲሥ (ከባባዶቹ ከተራቁ…) ስላሉ

**ደረጃዋ**
ይለያያል፤ ነብዩ "የከባዶች ሁሉ ከባድ (ወንጀል)…" እንዳሉት

**የሰሪው ፍርድ:**
ኢማኑ ያልተሟላ አማኝ ወይም በኢማኑ አማኝ በወንጀሉ አመፀኛ ነው። ባለው ኢማን ልክ ይወደዳል ባለው ወንጀል ልክ ይጠላል።ወንጀሉን በሚፈፅምበት ጊዜ አይቀማመጡትም

**ብዛቱ**
በቁጥር ባይገደበም ከፍ ብሎ በተጠቀሰ ው መርህ ይገደባል

## የእርድ አይነቶች

**የተፈቀደ**
ለስጋ፣ እንግዳን ለማክበር፣ ለንግድ ብሎ ማረድ

**ከአላህ ውጭ ላለ አካል በውዴታ እና በማላቅ**
(ሸይኹም የፈለገው ይህን ነው)
ትልቁ ሽርክ ነው። ለጅን ለቀብር ባለቤቶች ማረድ ብሎ እንደማረድ አይነቱ

**ለአላህ**
የተደነገገውም እሱው ነው፤ ሃድይ፣ ኡዱሒያና ሶደቃን ይመስል።

# ሁለተኛው አፍራሽ

በሱ እና በአላህ መካከል የሚማፀናቸው፣ ሸፋዓ (ምልጃ) የሚለምናቸው፣ የሚመካባቸው አማካኝ ያደረገ የካደ ለመሆኑ ኢጅማዕ (ሙሉ ስምምነት) አለበት።

## የሸፋዓ (ምልጃ) አይነቶች

### ከአላህ ውጭ ሌላ በማይችለው

**የተወገዘችው**

ሸይኹ የፈለጉትም ይህን ነው

ይህች ቁርአን ያወገዛትና አላህ እንጅ በማይችለው ጉዳይ ከአላህ ውጭ የምትፈለገዋ ነች፤ ከትልቁ ሽርክ ትመደባለች።

**የፀደቀችው**

አላህ ለራሱ ያፀደቃትና ከሱ እንጅ የማትፈለገዋ ናት፤ ተከታዮቹ መስፈርቶቿ ናቸው

(1) ለሸፈዓው አላህ መፍቀዱ

(2) ሸፋዓ ለሚያደርገው የአላህ ዉዴታ መኖሩ

(3) ሸፈዓ ለሚደረግለት የአላህ ዉዴታ መኖሩ

**አጠቃላይ የመልዕክተኞች፣ የነብያቶች፣ የመላዕክቶችና የጨቅላ ህፃናት ምልጃ**

(1) የተውሒድ ሰዎች ደረጃ ከፍ እንዲል የሚደረግ ምልጃ

(2) ለእሳት የተገባን የተውሒድ ሰው እንዳይገባት

(3) እሳት የገባን የተውሒድ ሰው ከሷ እንዲወጣ

**ለነብዩ ﷺ ብቻ የሆነ**

(1) ታላቁ ሸፋዓ

(2) የነብዩ ﷺ ለ አቡጣሊብ የቅጣት መቀነስ ምልጃ

(3) የጀነት በሮች እንዲከፈቱ የሚያደርጉት ምልጃ

### ፍጡራን በሚችሉት

አራት መስፈርቶች ከተሟሉ ይፈቀዳል

(1) ያለ/ቅርብ መሆን

(2) ህያው መሆን

(3) የሚችል

(4) ሰበብ ተደርጎ ሊያዝ ይገባል

**አንድ ሰው ለወንድሙ "ዱዓ አድርግልኝ" ማለቱ ትክክል ነውን?**

በዚሁ ፍላጎቱ የሆነ ያክል መተናነስ ካለበት ከትንሹ ሽርክ የሚመደብ አይነት ነው። የተፈለገው ከህያው፣ ቅርብና ከሚችል ሰው ሆኖ ሰበብ ተደርጎ የሚያዝ ከሆነ ግን የሚቻል ቢሆንም መተው ይሻላል።

**ተወኩል**

የተደነገገውን ሰበብ እያደረሱ እውነተኛ የሆነ በአላህ ላይ ተማምኖ መደገፍ ነው።

**የተፈቀደው**

መተናነስ ሳይታከልበት ነገራቶችን ሊያከናውን በሚችልበት ነገር ላይ መደገፍ፤ አንዳች ነገርን ለመግዛት ተወካይ ማድረግን ይመስል

**ትንሹ ሽርክ**

ከሙሉ መተናነስ ጋ ህያው በሆነ አካል ላይ መደገፍ፤ ህያው የሆነን አካል ከሰበብ በላይ አድርጎ ለሲሳይ መደገፍን ይመስል

**ከአላህ ውጭ ላለ አካል አሳልፎ ከሰጠው ትልቁ ሽርክ ነው**

ሽይኹም የፈለጉት ይህን ነው

የአምልኮና የመተናነስ ተወኩል። በእጁ ላይ የመጥቀምና መጉዳት ችሎታ አለ በሚል እምነት በተመኩበት ላይ ሙሉ በሙሉ መደገፍ። መተናነስን አይነት ነገር ያዘለና ሙታኖች ላይ መደገፍን አይነቱ።

**"በእገሌ ላይ እደገፋለሁ/እመካለሁ" ወይም "በአላህ ላይ እመካለሁ ከዚያም በእገሌ" ማለት ይፈቀዳልን? ትክክለኛውስ የትኛው ነው?**

"በእገሌ እመካለሁ" ማለትህም ሆነ "በአላህ እመካለሁ ከዚያም በእገሌ" ማለትህ ትክክል አይደለም። ምክንያቱም ይህ ከአላህ ውጭ ላለ አካል የማይገባ የልቦና ስራ ነው። ይልቅ "እገሌን ወክያለሁ" ማለትም ነገራቶችን ትችለታለሁ በል። ነብዩም ﷺ አንዳንድ ባልደረቦቻቸውን ለጥቅልም ሆነ ለልዩ ጉዳዮቻቸው ወክለዋቸዋል።

# ሶስተኛ አፍራሽ

**የአጋሪዎችን ካፊርነት ያላፀና፣ ወይም ካፊር ለመሆናቸው ከተጠራጠረ ወይም ደሞ መንገዳቸውን ትክክል ነው ያለ ካፊር ሆኗል።**

## አጋሪዎች በኢስላም ያላቸው ፍርድ

የነብዩ ﷺ ጥሪ ደርሶት አምኖ ያልተቀበለ ሁሉ ትልቁን ክህደት የፈፀመ ከሃዲ ነው። አላህ እንዲህ ስላለ፡ {ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም። እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው።} (አሊዒምራን 85)

## አህሉል ኪታብ(ክርስቲያንና አይሁዶች) አጋሪዎች ላይ ይመደባሉን?

አዎ በሳቸው ያላመኑት አህሉል ኪታቦች ከነሱ ይመደባሉ። አላህ እንዲህ ስላለ፡ {ከእነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን፣ አላህና መልክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትንና እውነተኛውንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ኾነው ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጉዋቸው፡ ፡} (ተውባ 29) ነብዩም ﷺ እንዲህ ስላሉ "ከዚህ ኡማ አንድም አይሁዳዊ ወይም ክርስቲያን ስለኔ አይሰማም ከዚያም በተላኩበት ሳያምን አይሞትም ክእሳት ጓዶች ቢሆን እንጅ"

## ይህ ማለት ቃል የገባንላቸውን አንወጣላቸውም ማለት ነውን?

ቃል የተግባባነውን የአላህን ዉዴታ እንድናገኝ ቃላችንን ልንፈፅምላት የግድ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡ {(እነዚህ) በቃል ኪዳናቸው ለእናንተ ቀጥ እስካሉላችሁ ድረስ ለነርሱም ቀጥ በሉላቸው።} (ተውባ 7) ሰዎች ከአጋሪዎች ጋ ባላቸው መስተጋብር ሶስት አይነት ናቸው፡

| | | |
|---|---|---|
| በበአላቶቻቸው፣ ብዝግጅቶቻቸውና በስነስርዓቶቻቸው የሚሳተፉ ፅንፎች | በግድያ፣ በዝርፊያ፣ በተንኮልና በመምታት ድንበር የሚያልፍ ፅንፍ | አህሉሱና ወልጀማዓህ ያሉበት ሚዛናዊ አቋም በበአላቶቻቸውም ሆነ በስነስርአቶቻቸው አለመሳተፍ፤ የተወጡትን ቃል እንፈፅምላቸዋለን፤ ድንበር አንተላለፍባቸውም፤ በግብይት እንጋራቻዋለን፤ ወደተውሒድም ጥሪ እናደርግላቸዋለን። |

# አራተኛው አፍራሽ

አራተኛ: የየትኛውም አካል መመርያ ከነብዩ ﷺ መመርያ ይልቅ የተሟላ ነው ብሎ ያመነ፣ ወይም የሌላ አካል ህግጋት ከሳቸው ህግጋት የተሻለ ነው ብሎ ያመነ - ሰው ሰራሽ ህግን ከሳቸው ህግ እንደሚያስበልጡት አይነቱ - ካፊር ነው።

## በሰው ሰራሽ ህግ የመፍረድ አይነቶች

የአላህ ህግ አይበጅም ብሎ ሰው ሰራሽ ህግን ከአላህ ህግ ሊያስበልጥ ነው። ይህ እምነት ካለው ከኢስላም የሚያስወጣውን ትልቁን ክህደት ፈፅሟል ካፊር ሆኗል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል {...ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸውን፣ የመርየምን ልጅ አልመሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ። ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው።} (ተውባ 31)

የአላህ ህግ አጥብቀው ሊይዙት የሚገባ ለሰውም ለአገሩም ሁሉ የሚበጀው እሱ ነው ብሎ እያመነ የሰው ሰራሽ ህግን በነፍስያው፣ ለስልጣን ፍለጋና መሰል ምክንያት ካስቀደመ ይህ ከባድ ያልሆነው ክህደት ነው። ትንሹ ክህደትና አመፅም ነው። በዚህ ፍርድ ሰቢያ የሙስሊምን ሓቅ ከጣሰበት ተጨማሪ በዳይነት እንዲሁም ከመንገዱ የሚያስወጣውን ትልቁን ክህደት ይሰጋበታልም።

# አምስተኛው አፍራሽ

ነብዩ ﷺ ይዘውት ከመጡት (መመርያ) አንዳች ነገርን የጠላ ቢሰራበት እንኳ ካፊር ነው።

## ለዚህ አፍራሽ ማስረጃው

ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡ {ይህ እነርሱ አላህ ያወረደውን ስለጠሉ ነው። ስለዚህ ሥራዎቻቸውን አበላሸባቸው።} (ሙሐመድ 9) እንዲሁም {በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም፤ (ምእመን አይኾኑም)።} (ኒሳእ 65) እንዲህም ይላል {አላህም ሊመራው የሚሻውን ሰው ደረቱን (ልቡን) ለኢስላም ይከፍትለታል። ሊያጠመውም የሚሻውን ሰው ደረቱን ጠባብ ቸጋራ ወደ ሰማይ ለመውጣት እንደሚታገል ያደርገዋል። እንደዚሁ አላህ በእነዚያ በማያምኑት ላይ ርክሰትን ያደርጋል።} (አልአንዓም125)

## ለአላህ ብሎ መውደድና መጥላት

ለአላህ ብሎ መውደድና መጥላት ከግዴታዎች ብሎም ከታማኝ የኢማን ዘለበቶች ነው።

**ለአላህ ብሎ መውደዱ ግዴታ የሆነው ምንድን ነው?**

- አላህ የሚወደውን ስራ በሙሉ፤ ያም እንደተውሒድ ያለውን ሸሪዓ ይዞት የመጣው ሁሉ ማለት ነው
- በሱ የሚሰሩትን እንደነቢያቶች፣ መልዕክተኞች፣ መላዕክቶች፣ ሱሓቦችና ሁሉንም የተውሒድ ጓዶችን
- ለይለቱል ቀድርንና የለሊቱን የመጨረሻ አንድ ሶስተኛ የመሰሉ አላህ የሚወዳቸውን ጊዜዎችን
- መካንና የነቢዩ መዲናን የመሰሉ አላህ የሚወዳቸው ቦታዎችን

**ለአላህ ብሎ መጥላቱ ግዴታ የሚሆነው ምንድን ነው?**

- አላህ የሚጠላውንና የማይፈልገውን ስራ፤ ያም እንድሽርክ ያለውን ሸሪዓ የከለከለው ሁሉ
- እንደሙሽሪኮች፣ ሙናፊቅና ሸያጢን አይነት ሰሪዎችን
- ፀሃይ እንደሚመለክበት አይነቱ አላህ የሚጠላቸው ጊዜዮችን
- ሽርክ እንደሚፈፀምባቸው ያሉ አላህ የሚጠላቸውን ቦታዎችን

**ሴት ልጅ (የሚስት) ብዛትን ብትጠላ ትከፍራለችን?**

ተጨባጭ ላይ ያለው ሸሪዓዊ ፍርዱን አትጠላም፤ ነገር ግን (ለራሷ) ባሏ በሷ ላይ ደርቦ ማግባቱን አትፈልግም፤ ይህ ደሞ የማትወቀስበት ጉዳይ ነው።

# ስድስተኛ አፍራሽ

ከነብዩ ﷺ ሃይማኖት በአንዳች ነገር ወይም በአላህ ምንዳ ወይም ደሞ በቅጣቱ የተሳለቀ ካፊር ሆኗል። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {…«በአላህና በአንቀጾቹ፣ በመልክተኛውም ታላግጡ ነበራችሁን» በላቸው።(65) አታመካኙ፤ ከእምነታችሁ በኋላ በእርግጥ ካዳችሁ።…}(አት-ተውበህ 65-66)

## ተሳላቂ

### ትርጉሙና (ኢስላማዊ) ፍርዱ

መሳለቅ ማለት ማፌዝ ማለት ነው። ተሳላቂ ሰው ፍርዱ ወይም ተሳዳቢ እውነትን የተወ ክህደትን የካደ ካፊር ነው። ያም ከመንገዱ የሚያወጣ ክህደት ነው። ባለቤቱም ጀሃነም ዉስጥ ዘውታሪ ነው።

ስድብ የሰማ ደሞ ሊያወግዝ አልያም ከአካባቢው ሊርቅ ይገባዋል፤ ሳያወግዝ ተመልካች ወይም ተራኪ አይነቱም ያው ነው። አላህ እንዲህ ስላለ {በእናንተም ላይ በመጽሐፉ ውስጥ የአላህን አንቀጾች በርሷ ሲካድባትና በርሷም ሲላገጥባት በሰማችሁ ጊዜ በሌላ ወሬ ውስጥ እስከሚገቡ ድረስ ከእነሱ ጋር አትቀመጡ፡፡ ማለትን በእርግጥ አወረደ፡፡ እናንተ ያንጊዜ ብጤያቸው ናችሁና፡፡ አላህ መናፍቃንን እና ከሓዲዎችን በሙሉ በገሀነም ውስጥ ሰብሳቢ ነውና፡፡} (ኒሳእ 140)

### ተውባው ተቀባይነት የሚያገኘው በተከታዮቹ መስፈርቶች ነው፡

- አላህን ተገቢ በሆነ መልኩ ሊያወድስ
- እየተሳለቀ ከተናገረው ራሱን ሊያጠራ
- እንድናምነው የፀፀቱ ምልክት ሊያሳኣ
- የአላህ መልዕክተኛን ﷺ የሰደበ ግን ተውባው ትክክለኛ ከሆነ አላህ ይቀበለዋል፤ ለድርጊቱ ግን (የሙስሊሞች) ባለስልጣን ይገለዋል

**ንግግሩ የኩፍር መልዕክት ካለውስ ካፊር ይባላልን?**

ግልፅ ይደረግለትና ተውባ ካደረገ እንተውዋለን፤ አለበለዚያ ግን ጉዳዩ ወደ ዳኞችና ወደ ታላላቅ ዑለሞች ይመለሳል።

# ሰባተኛ አፍራሽ

ድግምት - መስተፋቅርና መስተፃርርም እዚሁ የሚመደቡ ናቸው። - ወይ የሰራው አልያም የወደደ ካፊር ሆኗል። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {«እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ» እስከሚሉትም ድረስ አንድንም አያስተምሩም።} (አል በቀራህ 102)

## ድግምት

### የደጋሚ ምልክቶች

- ከመንገዱ(ከኢስላም) ያስወጣል
- ሸሪዓዊ ሩቃ የሚፈቀድባቸውን መስፈርቶች መጣስ እየቋጠሩ መትፋት
- የተቆራረጡ ፊደላቶችን መፃፍ፤ በማይገባ ቋንቋ ማነብነብ መስተፋቅርና መስተፃርር
- ከዋክብትን መመልከት፣ መዳፍንና ስኒን ማንበብ
- ህመምተኛን ሓራምን እንዲያደርግ፤ ወይም ሶላት እንዲተው አልያም በእርድ ጊዜ ቢስሚላህ ማለትን እንዲተው ማዘዝ
- የእናት ስም መጠየቅ
- የሩቅ ሚስጥር አውቃለሁ ብሎ መሞገት

### (ኢስላማዊ) ፍርዱ

ድግምት ትልቁ ኩፍር ነው፡ አላህ እንዲህ ስላለ {...«እኛ መፈተኛ ነንና አትካድ» እስከሚሉትም ድረስ አንድንም አያስተምሩም።...} (አልበቀራ 102)

### ደጋሚ ዘንድ መሄድ (ኢስላማዊ) ፍርዱ

መምጣት ሲባል እዚህ ላይ የተፈለገው መቀማመጡ፤ ወይም ሰው አልያም መልዕክት መላኩ ነው። እንዲሁም "ስነከዋክብት"፣ መዳፍና ስኒ ንባብ የሚተላለፍባቸውን ቲቪ፣ ዌብሳይት፣ መፅሄቶችን መመልከትም እንደዚሁ ነው። ወደ ጠንቋይ የሄደ በሓዲሥ እንደመጣው የአርባ ቀን ሶላቱ ተቀባይነት አያገኝም፤ በሚናገረው እውነት ብሎ ከተቀበለ ግን ነቢዩ እንዲህ ብለዋል {ወደ ጠንቋይ ሂዶ እውነት ብሎ የተቀበለው በሙሐመድ ላይ በወረደው ክዷል።} ለማውገዝ ብቁ ሆኖ የሄደ ሲቀር።

**ድግምትን ማክሸፍ**

ይህ ማለት በተደገመበት ሰው ላይ ድግምቱን ማክሸፍ ሲሆን ሁለት አይነት ነው

**የተከለከለ**

ከድግምት የሆነ ያክል ካለበት፤ ይህን በማስመልከት ነብዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል {ከሸይጧን ስራ ናት}

**የተደነገገ**

ሸሪዓዊ በሆነ ሩቃ፣ በተፈቀደ መድሃኒትና በዱዓ የሚደረገው ነው።

**ድግምትን በድግምት መሻር ይቻላል ለሚሉ ሰዎች ምላሹ**

1. ድግምትን በድግምት መሻር ቁርአንና ሓዲሥን እንዲሁም ቀደምት ሰለፎች የነበሩበትን የሚቃረን ነው።
2. በቁርአንና ከነቢያዊ ሱና በተገኙ ዱዓዎች የሚገኘው ፈውስን ማሳነስን ይዟል።
3. ድግምትንና ደጋሚዎችን ማጠናከርና እነሱን ብዙሃኑ ማህበረሰብ ዘንድ ማመቻቸትን አካቷል።
4. እርግጠኛ ከሆነው ቁርአናዊ እንዲሁም መሰረት በላቸው ዱዓዎች ከመተካከም ይልቅ ግምታዊ ወደሆነው ድግምታዊ መተካከም መዘንበልን ይዟል።
5. ከተደገመ ሰው ድግምትን በማክሸፍ ሂደት ላይ ድግምት ሻሪውም የሚሻርለትም ሸይጧን ድግምቱን እንዲፈታ በሚወደው መልኩ መቀራረብ ግድ ያስብላል
6. ከነብዩ ﷺ እንደመጣው አንድ የተደገመበት ሰው ትዕግስት ካደረገ ጀነት አለለት
7. ድግምትን በድግምት መሻር ለተደገመበት ሰው በድግምት ላይ ድግምትን ነው የሚጨምርበት
8. ነብዩም ﷺ ተደግመዋል፤ በሸሪዓዊ ሩቃ እንጅ በድግምት አልሻሩትም

## ስምንተኛ አፍራሽ

አጋሪዎችን በሙስሊሞች ላይ ማገዝና መርዳት። ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {…ከእናንተም ውስጥ ረዳቶች የሚያደርጋቸው ሰው እርሱ ከነርሱው ነው። አላህ አመጸኞችን ሕዝቦች አያቀናም።}(አል ማኢዳህ 51)

### አጋሪዎችን በሙስሊሞች ላይ ማገዝ

አንድ ሙስሊም ግድ የሚሆንበት ከአጋሪዎችና ከሃይማኖታቸው መጥራራትና በዚህም መካድ፤ የተውሒድ ሰዎችን መወዳጀትና ሃይማኖታቸውን መውደድ ነው። ኩፍርን የወደደ ወይም የተደሰተበት ወይም በዛ ላይ የተባበረና ሙሽሪኮችን ያገዘ ከመንገዱ የሚያስወጣውን አይነት ክህደት ፈፅሟል።

እኛ ዘንድ በተጨባጩ አጋሪዎችን ማገዝ ሁለት አይነት ነው፡

**ክህደትና መቀልበስ**
እነሱን ወዶ፣ ሙስሊሞችን ጠልቶ በሙስሊሞች ላይ የበላይ እንዲሆኑ ፈልጎ አጋሪዎችን በሙስሊሞች ላይ መርዳት

**ከመንገዱ የሚያወጣ ኩፍር ያልሆነ**
አጋሪዎችን ወዶ ሙስሊሞችን ጠልቶ ሳይሆን ለዱንያዊ ጥቅም ተብሎ

## ዘጠነኛ አፍራሽ

ልክ ኺዲር ከሙሳ ሸሪዓ ዓለይሂ ሰላቱ ወሰላም እንደወጣው ሁሉ ለአንዳንድ ሰዎች ከነብዩ ሙሓመድ ﷺ ሸሪዓ መውጣት ይችላሉ ብሎ የሚያምን ካፊር ነው።

### አንዳንድ ሰዎች ከነብዩ ሙሓመድ ﷺ ሸሪዓ መውጣት ይችላሉ ብሎ የሚያምን

በዑለሞች ሙሉ ስምምነት መሰረት ከመንገዱ የሚያወጣውን አይነት ትልቁን ክህደት የፈፀመ ካፊር ነው። የሚመለስ ከሆነ ተብራርቶለት ተውባ እንዲያደርግ ይጠየቃል አለበለዚያ ይገደላል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡ {(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው፡- «እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ።} (አል አዕራፍ 158) የአላህ መልዕክተኛም ﷺ እንዲህ ይላሉ "ሙሳ ወንድሜ በህይወት ቢሆን ኖሮ እኔን ከመከተል ውጭ አማራጭ አይኖረውም ነበር።"

የነቢዩ ጥሪ የደረሳቸው አህሉል ኪታቦችም እዚሁ ይካተታሉ፤ እንዳሳለፍነው አጋሪዎች ናቸውና። ኺዲርስ ከሙሳ መንገድ ወጥቷል እንዴ? እኛጋ የኺዲር ከሙሳ መንገድ መውጣት የፀና አይደለም። ቢፀድቅ እንኳ ምናልባት ከሙሳ ህዝብ ስላልሆነ ይሆናል። ነብይ ሲላክ ወደ ህዝቦቹ ብቻ ነው የነበረው፤ ነብያችን ﷺ የተላኩት ግን አጠቃላይ ወደ ሰው ልጆች ነውና አንድም ሰው ከመመሪያቸው ሊወጣ አይገባውም።

## አስረኛ አፍራሽ

ላይማር ላይሰራበት ከአላህ ዲን ጀርባውን የሰጠ: ማስረጃውም ተከታዩ የአላህ ቃል ነው: {በጌታውም አንቀጾች ከተገሰጸና ከዚያም ከተዋት ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው? (የለም)፤ እኛ ከተንኮለኞቹ ተበቃዮች ነን።}(ሰጅዳህ 22)

### ለአላህ ዲን ጀርባን መስጠት

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ይላሉ: "አላህ መልካም የሻለትን ሰው ዲኑን ያስገነዝበዋል"። አላህ መልካም ያልሻለት ደሞ ዲኑን ከመማር ይዘናጋል ጀርባውን ይሰጣል። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል፡ { በጌታውም አንቀጾች ከተገሰጸና ከዚያም ከተዋት ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው? (የለም)፤ እኛ ከተንኮለኞቹ ተበቃዮች ነን።} (ሰጅዳህ 22) የጀሃነም ሰዎችም ደሞ -አላህ ይጠብቀንና- ተንኮለኞቹ ናቸው።

## ጀርባ መስጠት ኢስላማዊ ፍርዱ

ጀርባ መስጠቱ በማዳመጥም ሆነ በልቦናው እውነትም ዉሸትም ሳይል ወዳጅ ጠላትነት ሳይፈጥር ይዘው ለመጡትም ቀና እንኳ የማይል ከሆነ ከመንገዱ የሚያስወጣው ትልቁን ክህደት የፈፀመ ከሃዲ ነው።

ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል: {ለእነርሱም፡- «አላህ ወደ አወረደው (ቁርኣን)ና ወደ መልክተኛው ኑ» በተባሉ ጊዜ መናፍቃን ከአንተ መሸሽን ሲሸሹ ታያቸዋለህ።} (ኒሳእ 61) እንዲህም ይላል: {ከጌታውም ማስታወሻ የሚያፈገፍግ ሰው አስቸጋሪን ቅጣት ያገባዋል።} (ጅን 17)

## የሸይኹ መደምደሚያ

በነዚህ አፍራሾች መካከል የቀልዱም ይሁን የምሩ አልያም ፈርቶም ልዩነት የለውም፤ ተገዶ ካልሆነ በቀር። ሁሉም አደገኛ ሊባል የሚችልና ብዙ ጊዜ የሚከሰትም ጭምር ነው። ሙስሊም ሊጠነቀቀውና በራሱ ላይ ሊሰጋ ይገባዋል። ቁጣውን ከሚያስከትልና ቅጣቱን ከሚያስፈርድብን ነገር በአላህ እንጠበቃለን። የአላህ ሰለዋት ከፍጥረቱ ምርጥ በሆኑት፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸውም ላይ ይስፈን።

በነዚህ አፍራሾች መካከል ልዩነት የለም:

**ፈሪ**

በአንዳች ነገር ሳይገደድ ዋሽቶ በገንዘቡ ወይም በደረጃው ለተቃጣ ችግር ስጋት እንዳደረገው የሚያመካኝ ነው። ከፍ ያለው አላህ እንዲህ ይላል: {ከሰዎችም በአላህ አመንን የሚል ሰው አልለ። በአላህም (በማመኑ) በተሰቃየ ጊዜ የሰዎችን ማሰቃየት እንደ አላህ ቅጣት ያደርጋል። ከጌታህም እርዳታ ቢመጣ እኛ በእርግጥ ከእናንተ ጋር ነበርን ይላሉ። አላህ በዓለማት ሕዝብ ልቦች ውስጥ ያለውን ሁሉ ዐዋቂ አይደለምን?} (አል ዓንከቡት 10)

**ያመረረ**

ያ ማለት አፍራሽን ፈልጎ አድርጎ በቂ ምክንያት የሌለው ነው

**እየቀለደ ለሆነ፡**

ያ ማለት አንድ አፍራሽ ነገርን ያደርግና ቀልድ እንደሆነ የሚሞግት ነው

## መገደድ

ከአፍራሾች መካከል አንዱንም ተገዶ ያደረገ ካፊር አይሆንም። በመገደዱ ዑዝር የሚያሰጡት

የመገደድ መስፈርቶችም ተከታዮቹ ናቸው፡

1. ፈሪ አልያም አስመሳይ ስለሆነ ሳይሆን በእውነት የተገደደ ሊሆን ይገባል
2. ድንበር ላያልፍ፤ ለምሳሌ በመስደቡ የሚከፍርበትን አንድ ሰው እንዲሰድብ ቢገደድ ተላልፎ ከአንድ በላይ መስደቡ ኩፍር ይሆንበታል፤ ምክንያቱም ተገዶ የነበረው አንድ ብቻ ነበርና ነው።
3. በቻለው ልክ ሊቃረነው፤ ኩፍርን እንዳይጋፈጥ
4. ልቦናው በኢማን የረጋ ሊሆን፤ ማለትም በአንደበቱ የሚለው ልቦናው በኢማን የረጋ ከመሆኑም ጋ ሊሆን
5. የተገደደበት ወደሌሎች የሚተላለፍ ብክለትና የሰዎች መጥመም ላይኖረው

## አስፈላጊ ማስታወሻዎች

**አንደኛ፡** ሸይኹ በዚህ ኪታብ ሰዎችን ማክፈር ፍላጎቱ አይደለም፤ ይልቅ ሰዎች እንዲያውቁ፣ ከሱም እንዲርቁና እንዲጠነቀቁ ነው። ከተጠነቀቋት ኢማናቸውም ትክክል ይሆናል ከአሳማሚው ቅጣትም ይድናሉ። ልክ ሌሎችንም ከሷ ሊያስጠነቅቁ እንደሚገባቸው ሁሉ። እሷም ልትታወቅና ሊጠነቀቋት ተገቢ የሆነች ከባድ አደጋ ነች።

**ሁለተኛ፡** የሙስሊም ከሽርክ መጠንቀቅ ሸሪዓዊ እውቀትን በማወቅ ነው። ነብዩ ﷺ እንዲህ ይላሉ "አላህ መልካም የሻለትን ሰው ዲኑን ያስገነዝበዋል" ዲንን መገንዘብ ከትላልቅና አሳሳቢ ግዴታዎች ነው። የሰው ልጅ በዚሁ ራሱን ከሽርክ፣ ከቢድዓና ከአመፅ ያቅብበታል። ሁሌም ጌታውን በማስመልከት እውቀቱ በጨመረ ቁጥር በድርጊቱም በሁኔታውም ሁሉ (አላህ) በሱ ላይ ላለው ተቆጣጣሪነት (ተገዥ መሆን) ይጨምራል። የሰው ልጅ በእውቀት ከፍ ባለ ቁጥር ኢኽላሱም ይጨምራል ኢማኑም ይሟላል። አንዳንድ የእውቀት ባለቤቶች እንዲህ ይላሉ "እውቀትን ለሌላ ብለን ፈለግን ለአላህ ካልሆነ ብሎ እምቢተኛ ሆነ እንጅ!"።

**ሶስተኛ፡** ግለሰብን ከነዚህ አፍራሾች መካከል በአንዱ አርፎ ማስረጃ እንደቆመለትና የመክፈሩን ፍርድ ከመስጠት የሚከለክለው ነገር አለመኖሩ ካልተረጋገጠ በቀር ካፊር ሊባል አይችልም። የኩፍር ፍርድ መስጠት ያለበትም በሙስሊሞች ጉዳይ የተሾመ ወይም ደሞ እንደ ቃዲ(ዳኛ) አይነቱ የሱ ተተኪ መሆን ይኖርበታል። ብዙሃኑ ማህበረሰብ `ማ በእንደዚህ አይነቱ ጉዳይ ላይ ለመዘፈቅ ሊደፍር አይገባውም።

**አራተኛ፡** ሸይኹ አላህ ይዘንለትና ኪታቡን እንዲህ ብሎ በዱዓ ደመደመ፤ "ቁጣውን ከሚያስከትልና ቅጣቱን ከሚያስፈርድብን ነገር በአላህ እንጠበቃለን።" ይህም ለተማሪው ካለው ቅን አሳቢነትና ርህራሄ አንፃር ነው። በሌሎቹ ኪታቦቹም ላይ ልምዱ ነው። አላህ መሃርታውን ይለግሰው፤ ምንዳውንም ያብዛለትና።

# ራስክን ፈትን

ለተከታዮቹ ጥያቄዎች በተሰጠው ቦታ ላይ መልሱን አስቀምጥ

1. ዑለሞች ለምንድን ነው በቢስሚላህ የሚጀምሩት?

    (1)........................................................................

    (`2)........................................................................

    (3)........................................................................

    (4)........................................................................

2. የኢስላም አፍራሾች ማለት ምን ማለት ነው?

    ..............................................................................

    ..............................................................................

3. ለምንድን ነው ዑለሞች አንዳንዴ አፍራሾች አንዳንዴም አበላሾች ሌላ ጊዜ ደሞ ኢስላሙን ዉድቅ የሚያደርጉ የሚሉት?

    ..............................................................................

    ..............................................................................

4. እነዚህ አፍራሾች በዑለሞች መካከል ሙሉ ስምምነት አለባቸውን?

    ..............................................................................

    ..............................................................................

5. እነዚህ አፍራሾች በቁጥር የተገደቡ ናቸውን?

-የተገደቡ ናቸው -የተገደቡ አይደሉም -በቁጥር ሳይሆን በጥቅሉ የተገደቡ ናቸው

6. ሸይኹ ለምንድን ነው አስር ናቸው ያለው?

.............................................................................

.............................................................................

7. በቁርአንና በሓዲሥ ቁጥር ከተወሳ ትርጉም ይሰጠዋልን? ማለትም አይጨመርበትም?

.............................................................................

.............................................................................

8. ለምንድን ነው አንዳንድ ጊዜ ቁጥር ተጠቅሶ ትርጉም የማይኖረው?

.............................................................................

.............................................................................

9. የተጠቀሰው ቁጥር ትርጉም የሚኖረውን ቦታ ምሳሌ ጥቀስ?

.............................................................................

.............................................................................

10. ቁጥር ተጠቅሶ ትርጉም የማይኖረውን ቦታ ምሳሌ ጥቀስ?

.............................................................................

.............................................................................

11. ሸይኹ ከአስር በላይ አፍራሽ እንዳለ ያስባልን?

.............................................................................

.............................................................................

12. የትኛው ንግግሩ ነው ይህን የሚያሲዘን?

.............................................................................

.............................................................................

13. አፍራሾችን መገደብ ይቻላልን?

.............................................................................

.............................................................................

14. አፍራሾችን እንዴት መገደብ ይቻላል?

(1)..................................................................................

(2)..................................................................................

(3)..................................................................................

(4)..................................................................................

15. ለምንድን ነው ስለ አፍራሾች የምንማረው?

..................................................................................

..................................................................................

16. ከሸይኹ ውጭ ስለ አፍራሾች የፃፈ አለን?

..................................................................................

..................................................................................

17. አፍራሾችን በማስመልከት በስራውና በሰሪው መካከል ልዩነት አለን?

..................................................................................

..................................................................................

18. ከምን አኳያ ይለያያሉ?

..................................................................................

..................................................................................

19. ሸይኹ አፍራሾችን በመጥቀስ የፈለገበት ግለሰቦችን ማክፈር ነውን?

..................................................................................

..................................................................................

20. ስለ አፍራሾች የተማረ ሰው ምን ይጠበቅበታል?

..................................................................................

..................................................................................

21. ሸይኹ ይበልጥ የፈለገው የትኛውን አይነት ሽርክ ነው?

.................................................................................

.................................................................................

22. በትልቁና በትንሹ ሽርክ መካከል ልዩነቱን እንዴት እንወቅ?

.................................................................................

.................................................................................

.................................................................................

.................................................................................

.................................................................................

.................................................................................

23. ትልቁን ሽርክ የፈፀመ ሙሽሪክ ሽርኩ ተቅባይነት ያገኛልን? ተቀባይነት የማያገኘውስ መቼ ነው?

.................................................................................

.................................................................................

24. የትኛው ነው የከፋው ትንሹ ሽርክ ወይስ ከባድ ወንጀል?

.................................................................................

.................................................................................

25. ለወንጀል ከባድ መሆን ሚዛኑ ምንድን ነው?

.................................................................................

.................................................................................

26. ከባባድ ወንጀሎች በቁጥር የተገደቡ ናቸውን?

.................................................................................

.................................................................................

27. ከባድ ወንጀል የሰራ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው? እንወደዋለን ወይስ እንጠላዋለን?

......................................................................................

......................................................................................

......................................................................................

......................................................................................

28. ከባድ ወንጀልን የሰራ ሰው ይቀማመጡታልን?

......................................................................................

......................................................................................

29. ከባባድ ወንጀሎች ይበላለጣሉን? ማስረጃውስ ምንድን ነው?

......................................................................................

......................................................................................

30. ከባባድ ወንጀሎች በመልካም ስራ ይሰረዛሉን? ወይስ ተውባ ግዴታ ነው?

......................................................................................

......................................................................................

31. የተከለከሉ ነገራቶች ስንት አይነት ናቸው?

......................................................................................

......................................................................................

32. የትልቁ ሽርክ አይነቶችን ጥቀስ

(1)..............................................................................

(2)..............................................................................

(3)..............................................................................

(4)..............................................................................

33. የእርድ አይነቶችን ጥቀስ

(1)..............................................................................

(2)..............................................................................

(3)..................................................................................

34. እርድ ከትልቁ ሽርክ የሚሆነው መቼ ነው?

..................................................................................

..................................................................................

35. የሽፋዓ (ምልጃ) አይነቶችን ጥቀስ

(1)..................................................................................

(2)..................................................................................

(3)..................................................................................

36. ተወኩል (መደገፍ) ምንድን ነው?

..................................................................................

..................................................................................

37. ተወኩል ለስንት ይከፈላል?

(1)..................................................................................

(2)..................................................................................

(3)..................................................................................

38. “በእገሌ ላይ ተደገፍኩ/ተመካሁ” ወይም “በአላህ ከዚያም በእገሌ...” ማለት ትክክል ነውን?

- ትክክል ነው - ትክክል አይደለም

39. ምንስ ነው ማለት ያለበት?

..................................................................................

..................................................................................

40. አጋሪዎች (ሙሽሪኮች) ከሃዲ ለመሆናቸው ማስረጃው ምንድን ነው? አህሉል ኪታብስ ከነሱ ይመደባሉን?

..........................................................................................

..........................................................................................

41. ይህ ማለት ቃላችንን እንፈፅምላቸውም ማለት ነውን?

..........................................................................................

..........................................................................................

42. ቃል ከመገባበት አንፃር ሰዎች ስንት አይነት ናቸው?

(1)....................................................................................

(2)....................................................................................

(3)....................................................................................

43. በሰው ሰራሽ ህግ መፍረድ ስንት አይነት ነው?

..........................................................................................

..........................................................................................

44. ለአላህ ብሎ መውደድ ፍርዱ ምንድን ነው?

..........................................................................................

..........................................................................................

45. ለአላህ ብለን የምንወደው ማንን ነው? ለአላህ ብለን የምንጠላውስ ማንን ነው?

..........................................................................................

..........................................................................................

46. ተሳላቂ ከየትኛው የኩፍር አይነት ነው?

..........................................................................................

..........................................................................................

47. ለተሳላቂ (ዳኞች ዘንድ) ተውባ አለውን? መስፈርቶችስ?

(1)....................................................................................

(2)....................................................................................

(3)........................................................................

48. ነብዩን ﷺ መስደብ ፍርዱ ምንድን ነው?

........................................................................

........................................................................

49. (የሚያከፍር) ስድብን የሚያዳምጥ ሰው ፍርዱ ምንድን ነው?

........................................................................

........................................................................

50. ደጋሚ ካፊር ለመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው?

........................................................................

........................................................................

51. የደጋሚ ምልክቱ ምንድን ነው?

........................................................................

........................................................................

52. ጠንቋይ ዘንድ መሄድ ፍርዱ ምንድን ነው?

........................................................................

........................................................................

53. እነሱ ዘንድ የሚኬደው እንዴት ነው?

........................................................................

........................................................................

54. ድግምትን በድግምት የማክሸፍ አይነቶችን ጥቀስ?

(1)........................................................................

(2)........................................................................

55. ድግምትን በድግምት ማክሸፍ ይቻላል ለሚል እንዴት እንመልስለት?

(1)........................................................................

(2)..........................................................................

(3)..........................................................................

(4)..........................................................................

(5)..........................................................................

(6)..........................................................................

(7)..........................................................................

(8)..........................................................................

56. አጋሪዎችን(ሙሽሪኮችን) ማገዝ ፍርዱ ምንድን ነው?

..........................................................................

..........................................................................

57. ከነብዩ መሐመድ ﷺ ሸሪዓ መውጣት ለማንም ቢሆን ይፈቀዳልን?

..........................................................................

..........................................................................

58. ኸድር ከሙሳ(መመሪያ) ወጥቷልን?

..........................................................................

..........................................................................

59. (ከዲነል ኢስላም)ጀርባ መስጠት ፍርዱ ምንድን ነው?

..........................................................................

..........................................................................

60. በሸይኹ ንግግር መሰረት ፈሪ ሲል ምን ማለቱ ነው? የተገደደውን ማለቱ ነውን?

..........................................................................

..........................................................................

61. የመገደድ መስፈርቶችን ጥቀስ

(1)..........................................................................

(2).................................................................

(3).................................................................

(4).................................................................

(5).................................................................

62. ከምን አንፃር ነው በዱዓ የደመደሙት?

........................................................................

........................................................................

63. አንድ ሙስሊም እንዴት ነው በራሱ ላይ ሽርክ የሚሰጋው?

........................................................................

........................................................................